www.abyssinialaw.com

# የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ሐተታ ዘምክንያት /ማብራሪያ/

www.abyssinialaw.com

## ምዕራፍ 1

## ጠቅላላ ስለ ጋብቻ አፈፃፀም

**አንቀጽ /1-4/ ልዩ ልዩ የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓቶች**

ይህ ምዕራፍ በ1952 ዓ.ም. በወጣው የፍ/ብ/ሕግ ሁለተኛ መጽሐፍ ስለጋብቻ አፈፃፀም በምዕራፍ 3 የተመለከተው ሲሆን ሶስት ዓይነት ጋብቻ መኖሩን ይደነግጋል፡፡ 'ጋብቻ' የሚለው ቃል በአንድ በኩል ጋብቻ ውስጥ ለመግባት የሚደረገውን ሥርዓት (celebration/conclusion of marriage) የሚመለከት ሲሆን በሌላ በኩል ጥምረቱን ለመመስረት የሚከናወነው ሥርዓት ከተፈፀመ በኃላ ወይም ጋብቻ ለመመስረት የሚያስፈልጉ ሥርዓቶች ከተሟሉ በኃላ የሚመሰረተውን ግንኙነት /ትብብሩን፣ትዳር/ የሚያመለክት ይሆናል፡፡

ከዚህ በመነሳት በዚህ ሕግ ጋብቻ የሚለው ቃል የአፈፃፀም ሥርዓቱን የሚያመለክት ሲሆን በሶስት ዓይነት ሥርዓቶች ሊፈፀም ይችላል፡፡ በመሆኑም በፍ/ብሔር ቁጥር /577-580/ ያሉት ድንጋጌዎች ጋብቻ ሊመሰረትባቸው የሚችሉ የአፈፃፀም ሥርዓቶችን የሚያመለክት በመሆኑ ከአንቀጽ /1-4/ ባሉት ድንጋጌዎች የአገላለጽና የቃላት ለውጥ ተደርጓል፡፡ 'ብሔራዊ' የሚለው ቃል በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገመንግስት ከተሰጠው ትርጓሜና አጠቃቀም አኳያ 'ብሔራዊ ጋብቻ' የሚለው አገለላጽ አግባብነት የሌለው ሆኖ በመገኘቱ በክብር መዝገብ ሹም ፊት የሚፈፀም ጋብቻ በሚል ርዕስና አጠቃቀም እንዲተካ ተደርጓል፡፡

በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 34/4/ በተደነገገው መሠረት በባህልም ሆነ በሀይማኖት ሥርዓት የሚፈፀሙ ጋብቻዎች በክብር መዝገብ ሹም ፊት ከሚፈፀመው ጋብቻ ጋር በእኩል ደረጃ የሚታዩ መሆናቸውን ለማመልከት ልዩነት በሚፈጥሩ አገላለጾች ላይ ለውጥ የተደረገ ሲሆን የሶስቱም ዓይነት ጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት ግልጽ በሆነ አነጋገር ሰፍሯል፡፡

'ልማድ' የሚለው ቃል ባህል የሚለውን በቀጥታ የሚያመለክት ከመሆኑም በተጨማሪ በእንግሊዘኛው ቅጂ "custom" የሚለው ቃል የሚወክለው ባህልን በመሆኑ፣ ልማዳዊ ጋብቻ የሚለው በባህል ሥርዓት መሠረት የሚፈፀም ጋብቻ በሚል ተተክቷል፡፡ ጐሣ የሚለው አነጋገርም እንዲሁ በሌላ ተስማሚ በሆነ ቃል እንዲተካ ተደርጓል፡፡

በባህላዊ የጋብቻ አፈፃፀም ነዋሪ የሆነ ግንኙነት /permanent union/ ለመፍጠር የሚያስችል ሁኔታ መኖር እንዳለበት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 580 ተመልክቷል፡፡ ዘላቂ ወይም ነዋሪ የሆነ ግንኙነት ለመፍጠር የሚያስችል ቅድመ ሁኔታ ማስቀመጥ ባህላዊ የሆነውን የጋብቻ አፈፃፀም ከሌሎች ሥርዓቶች የሚለይ አገላለጽ በመሆኑና በጋብቻ ውጤቶች ላይ መንፀባረቅ የሚገባው አስተሳሰብ በመሆኑ ተሰርዟል፡፡

ተጋቢዎች ከአካባቢያቸው ውጭ በሚኖሩበት አካባቢ ባህል መሠረት ጋብቻ ለመፈፀም የሚችሉበት ሁኔታ በመኖሩ አስተሳሰቡ በረቂቁ ተካትቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ 5 ከኢትዮጵያ ውጭ ስለሚፈፀም ጋብቻ

የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓትም ሆነ ሁኔታ በሀገሮች መካከል ልዩነት ሊኖረው የሚችል ቢሆንም በተፈፀመበት ሀገር ሕግ መሠረት የተደረገ ጋብቻ ተቀባይነት ሊኖረው የሚገባ በመሆኑ የኢትዮጵያ ሕግ እውቅና የሚሰጥበት ድንጋጌ እንዲኖር ተደርጓል፡፡ በተለይም አሁን ባለንበት ሁኔታ ብዙ ኢትዮጵያዊያን ከረዥም ዓመታት የስደት ኑሮ በኋላ ወደ አገር ቤት እየተመለሱ ኑሮአቸውን በመምራት ላይ ስለሚገኙ በስደት በነበሩበት ጊዜና ቦታ የፈፀሙዋቸው ጋብቻዎች በነበሩበት አገር የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት መሠረት እስከተፈፀሙ ድረስ እውቅናና ህጋዊ ፋይዳ ለመስጠት ስለታሰበ ነው፡፡ የዚህ ድንጋጌ ተፈፃሚነት የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓቱን ብቻ በሚመለከት ይሆናል፡፡ ይህም ማለት ይዘቱን በተመለከት በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ይታያል ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ በተጋቡበት አገር በሁለት ወንዶች መካከል ጋብቻ የሚፈቀድ ቢሆንና ተጋብተው ቢመጡ የኢትዮጵያ ሕግ አይቀበለውም ምክንያቱም በኢትዮጵያ ጋብቻ በወንድና በሴት መካከል ብቻ መሆን ስላለበት ነው፡፡ ባጠቃላይ ከኢትዮጵያ ውጭ የተፈጸመ ጋብቻ በኢትዮጵያ ውስጥ ተቀባይነትና ዕውቅና ሊኖረው የሚችለው ሕግንና የሕዝብን ሞራል የማይቃረን ከሆነ ብቻ ነው፡፡

## ክፍል 1

## ጋብቻ ለመፈፀም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

አፈፃፀሙ ሊለያይ የሚችል ቢሆንም ጋብቻ ለመፈፀም መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች በሁሉም ሥርዓቶች ተፈፃሚ ሊሆኑ ስለሚገባ ርዕሱ በክፍል 1 ሥር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ለማካተተት በሚችል ቋንቋ ተስተካክሏል፡፡

አንቀጽ 6 ፈቃድ

የጋብቻን አመሰራረት በተመለከተ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 34/2/ የተቀመጠው መርህ በዝርዝር ሕጉ ሊንፀባረቅ የሚገባው መሠረታዊ መብት በመሆኑ በጋብቻ አፈፃፀም የሶስተኛ ወገኖች /ወላጆች፣ አሳዳሪዎች/ ተፅእኖ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ለማመልከት በአንቀጽ 6 የተጋቢዎች ፈቃድና ፍላጐት በአስፈላጊ ሁኔታዎች ሥር እንዲሰፍር ተደርጓል፡፡ ዋናው አስፈላጊ ሁኔታ የወደፊት ተጋቢዎች ፈቃድ መሆኑን ለማሳየትም በክፍሉ ውስጥ የመጀመሪያው አንቀጽ ሆኖ እንዲቀረጽ ተደርጓል፡፡

አንቀጽ 7 ዕድሜ

ወንዶችና ሴቶች በጋብቻ አፈፃፀም ጊዜ እኩል መብት ያላቸው መሆኑ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 34/1/ በመደንገጉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 581 ወንዶች ጋብቻ ለመፈፀም የሚችሉበት ዕድሜ 18 በመሆኑ ለወንድም ሆነ ለሴቷ የጋብቻ መፈፀሚያ ዝቅተኛ ዕድሜ 18 እንዲሆን ተደርጓል፡፡

ይህ መነሻ የጋብቻ ዕድሜ በተለይም ሴቶች አካላቸው በሚገባ ሳይጠነክር፣ ትምህርታቸውን ሳይገፉ፣ በጨቅላ ዕድሜያቸው ለእርግዝና በመዳረጋቸውና የቤተሰብ ኃላፊነትን እንዲሸፍኑ በመደረጋቸው ምክንያት ይደርስ የነበረውን ተደራራቢ ችግር ሊያስወግድ እንደሚችል የሚታመን ሲሆን በማህበራዊ ሣይንስም ሆነ በዓለም አቀፍ

www.abyssinialaw.com

ደረጃ ቤተሰባዊ ሀላፊነትን ለመወጣት ብቁ የሚያደርግ 18 ዓመት ዝቅተኛ ዕድሜ በመሆኑ ተቀባይነት እንዳለው ይታመናል:: ከዝቅተኛው ዕድሜ እስከ ሁለት ዓመት ቀንሶ ጋብቻ ለመፈፀም የሚያስችል ከባድ ምክንያት ባጋጠመ ጊዜ ፈቃድ እንዲሰጥ አግባብ የሚኖረው አካል የፍትሕ ሚኒስቴር መሆኑን በማመን ሚኒስትሩ ይህ ሥልጣን እንዲኖረው ተደርጓል:: አባትና እናት አካለመጠን ላልደረሱ ልጆቻቸው የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት ሥልጣን የሚኖራቸው በመሆኑ ጋብቻው እንዲፈቀድ የሚቀርበው ጥያቄ በተጋቢዎች ወይም በአሳዳሪዎቻቸው በኩል ሊቀርብ የሚችል መሆኑን የሚገልጽ ድንጋጌ እንዲካተት ተደርጓል::

<u>አንቀጽ 8</u> <u>የሥጋ ዝምድና</u>

በሥጋ ዝምድና በተሳሰሩ ሰዎች መካከል ጋብቻ የተከለከለ መሆኑን የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 550፣ 551 እና 582 ሲደነግግ የዝምድና ደረጃ አቆጣጠር ስልት ግልጽ ባለመሆኑ አንዳንዴም ስለሚያወዛግብ ማሻሻያ ማድረግ አስፈልጓል::

ይህንኑ ችግር ለማቃለል ክልከላ የሚደረግባቸው ዝምድናዎች ተዘርዝረው እንዲቀመጡ ተደርጓል:: በመሆኑም በቀጥታ የሥጋ ዘመዳሞች መካከል ክልከላው ፍፁም ሲሆን ወደ ጐን በሚቆጠረው ላይ ገደብ ተበጅቶለታል::

በዚህ መሠረት ወደ ጐን በሚቆጠር የሥጋ ዝምድና አንድ ሰው ጋብቻ እንዳይፈጽም የሚከለከለው፣
ከወንድሙ/ ከእህቱ
ከወንድሙ ልጅ/ከእህቱ ልጅ
ከአጐቱ/ከአክስቱ
ከአጐቱ ልጅ/ ከአክስቱ ልጅ ጋር ነው::

በጋብቻ ዝምድና በተሳሰሩ ሰዎች መካከል የጋብቻ ክልከላ መኖሩ በፍ/ብ/ሕግ ቁ.552 እና 553፣ 583 የተመለከተ ሲሆን ወደጐን በሚቆጠሩ ዘመዳሞች መካከል ክልከላው እስከ ሶስተኛ ደረጃ ድረስ እንደሆነ ተደንግጓል:: ይህም ቢሆን በአቆጣጠር ረገድ ግልጽነት የጐደለው በመሆኑና ደረጃ በደረጃ ወደላይም ቢሆን የተለያየ አመለካከት በመኖሩ ምክንያት ክልከላው የሚመለከታቸውን ክፍሎች ማመልከቱ አስፈላጊ ሆኗል::

ስለሆነም የጋብቻ ክልከላ በቀጥታ ከሚቆጠሩ የጋብቻ ዘመዶች በተጨማሪ ወደጐን በሚቆጠር የጋብቻ ዝምድናም እንዲሁ ባል ከሚስቱ እህት ጋር፣ ሚስት ከባሏ ወንድም ጋር ጋብቻ መፈፀም የተከለከለ እንዲሆን ተደርጓል::

<u>አንቀጽ 10</u> <u>በሕግ ያልተረጋገጠ ልጅነት</u>

በሕግ የተረጋገጠ ወይም ያልተደጋገጠ ልጅነት ለጋብቻ ክልከላ ልዩነት የሚፈጥር ባለመሆኑ በማህበረሰቡ ዘንድ ተወላጅነቱ የሚታወቅ እስከሆነ ድረስ ጋብቻ ለማስከልከል የሚችል ሁኔታ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 584 የሰፈረው ክልከላ የአገላለጽ ለውጥ ተደርጎበት እንዲቀጥል ተደርጓል::

www.abyssinialaw.com

<u>አንቀጽ 11 በጋብቻ ላይ ጋብቻ</u>

በአንዳንድ ባህሎችና በእስልምና ሀይማኖት ተከታይ የሕብረተሰብ ክፍሎች ዘንድ ከአንድ በላይ ጋብቻ የሚፈፀምበት ሁኔታ በመኖሩ ከአንደ በላይ ጋብቻ መከልከሉ ሁሉንም የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓቶች ሊመለከት ይገባል ወይ በሚለው አስተሳሰብ ላይ ለውጥ ማምጣት ያልተቻለ ቢሆንም በጋብቻ ዘመን ተጋቢዎች እኩል መሆናቸውን ለማረጋገጥ፣ የቤተሰብንና የልጆችን ደህንነትና ጥቅም ለማስጠበቅ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 34/1/ ሥር በሰፈረው ድንጋጌ መሠረት በጋብቻ ላይ ጋብቻ መፈፀም እንደማይቻል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 585 የተመለከተው ክልከላ መጠነኛ የቃላት ለውጥ ተደርጐ እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡ በርግጥ አንዳንድ ባህሎችን ወይም ሀይማኖቶችን አስመልክቶ የሚወጡ ልዩ ሕጐች በአጠቃላይ ሕግ ላይ የበላይነት ስለሚኖራቸው የአንዳንድ ባህሎች ወይም ሀይማኖቶች ጉዳይ በዚያው መሠረት የሚገዛ ይሆናል፡፡

<u>አንቀጽ 12 ጋብቻ በእንደራሴ መፈፀም የማይቻል ስለመሆኑ</u>

ጋብቻ በነፃና ሙሉ ፈቃደኝነት ሊመሰረት የሚገባ በመሆኑ በእንደራሴ መፈፀም ሊከለክል ይገባል፡፡ የተጋቢዎችን ፈቃድና ፍላጐት ለማረጋገጥ ጋብቻው በሚፈፀምበት ጊዜና ቦታ/በአካል መገኘት ይጠበቅባቸዋል በሌላ በኩል ሁለቱም ተጋቢዎች ፈቃድና ፍላጐታቸውን ገልፀው በአንድነት መገኘት የማይችሉበት ከባድ ሁኔታ ሊያጋጥም ይችላል፡፡ በእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ አንደኛው ተጋቢ በአካል ለመገኘት ያላስቻለው ከባድ ምክንያት አጋጥሞት በእንደራሴ ለመፈፀም ጥያቄ ሊቀርብ የሚችልበት መንገድ መኖር እንዳለበት ታምኖበት እንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች በጥንቃቄ የሚታዩበትና የሚመረመሩበት ሥርዓት ሊኖር ስለሚገባው በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 586 የሰፈረው ድንጋጌ ማሻሻያ ተደርጓበታል፡፡ በዚህም መሠረት ከታጋቢዎች አንደኛው ጋብቻ ለመፈፀም ፈቃዱን በማያሻማ ሁኔታ በመግለጽ በግንባር ለመገኘት የማያስችለው ከባድ ምክንያት ሲያጋጥመው ጉዳዩ ለፍትሕ ሚኒስትሩ ቀርቦ ሲረጋገጥ ጋብቻውን በእንደራሴ አማካኝነት ለመፈፀም የሚያስችል ድንጋጌ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

<u>አንቀጽ 13 መሠረታዊ ስህተት</u>

ይህ ድንጋጌ በፍ/ብ/ሕጉ አንቀጽ /590-591/ ሥር የሰፈረውን የሚያጠቃልል ሲሆን ለአፈፃፀም ምቹ በሚሆን አገላለጽ እንዲጠቃለል ተደርጓል፡፡

በማንኛውም ዓይነት ስህተት ምክንያት የተፈፀመ ጋብቻ የፈቃድ ጉድለት መኖሩን አመልካች ሊሆን እንደማይገባው ታምኖበታል፡፡ ሆኖም ጋብቻው ሲፈፀም መሠረታዊ የሆነ ስህተት መኖሩ ከታወቀ ጋብቻው ሊፀና አይገባም፡፡ በመሠረታዊ ስህተትነት ሊዘረዘሩ የሚችሉ ምክንያቶችን ገድቦ /restrictive enumeration/ ማስቀመጥ የሚቻል ሆኖ ባለመገኘቱና ሕጉ ገላጭ /illustrative/ በሆነ መልኩ ቢቀመጥ ወደፊት ሊነሱ የሚችሉ ክፍተቶችንና ክርክሮችን መልስ መስጠት ይችላል፡፡

ስለሆነም በፍ/ብ/ሕጉ አንቀጽ 591 ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ውስጥ በሚያገባው ሰው ማንነት ላይ ስህተት ተፈጽሞ ከሆነ መሠረታዊ ስህተት ሊሆን እንደሚችል ታምኖበታል፡፡ የሚያገባውን ሰው ሀይማኖት ጋብቻውን ከመፈፀሙ በፊት አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ ማወቅ የሚቻል ጉዳይ በመሆኑ የፈቃድ ጉድለት ሊያስከትል የሚችል ምክንያት ሆኖ አልተገኘም፡፡ አንድ ሰው ሊድን የማይችል ወይም ለተወላጆች ሊተላለፍ የሚችል ከባድ በሽታ ሌላኛው ተጋቢ ያለበት መሆኑን ሳያውቅ ጋብቻ ቢፈጽም የፈቃድ ጉድለት መኖሩን የሚያመለክት መሠረታዊ ስህተት በመሆኑ

www.abyssinialaw.com

የበሽታውን ዓይነት ምንነት ከመግለጽ ይልቅ አጠቃላይ በሆነ አገላለጽ እንዲፃፍ ተደርጓል፡፡ አብሮ መኖር፣ የግብረሥጋ ግንኙነት መፈፀም ጋብቻ በተጋቢዎች ላይ ከሚያስከትላቸው ውጤቶች በዋነኛነት የሚጠቀሱ በመሆናቸው የግብረሥጋ ግንኙነት መፈፀም ያለመቻል በመሠረታዊ ስህተትነት ተወስዷል፡፡

የሥጋ ደዌ ሊድን የሚችልና ወደፊር ሊጠፋ የሚችል ስለመሆኑ በዘመናዊ ሳይንስ የተረጋገጠ በመሆኑ የፈቃድ ጉድለት ሊያስከትል እንደሚችል የተወሰደው ምክንያት ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ከሕጉ ተሠርዟል፡፡

<u>አንቀጽ 14 በኃይል ሥራ የተገኘ ፈቃድ</u>

በኃይል ሥራ የተገኘ ፈቃድ ጋብቻን ለማፍረስ ስለሚቻልበት ሁኔታ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 589 ሥር የተካተቱ ነጥቦች አግባብነት ያላቸው ቢሆንም ሊደርስ የተቃጣው አደጋ የታሰበው በራሱና በወላጆቹ ወይም ተወላጆች መገደብ እንደሌለበት ታምኖበታል፡፡

አንድ ሰው ሊቀበለው የማይፈልግ በራሱም ሆነ በሌላ የቅርብ ዘመድ ላይ አደጋ ሊደርስ እንደሚችል ካረጋገጠ ጋብቻ እንዲፈፀም ፈቃድ የሚሰጥበት ሁኔታ ይኖራል፡፡

ተጋቢው ወደ ጋብቻ ሊገባ የቻለው ሊደርስ የታሰበን አደጋ ለማስወገድ መሆኑን ማረጋገጥ እስከቻለ ድረስ ለጋብቻው መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ ወገኖች ማንነት ሰፋ ባለ መልኩ ሊታይ ይገባል፡፡

ተጋቢው ከወላጆች በላቀ ደረጃ ካለው ቅርበትና ትስስር በመነሳት በሌሎች ሰዎች ላይ ሊቀበለው የማይፈልገውን አደጋ ለማስወገድ ጋብቻውን ለማድረግ የሚገደድበት ወይም የሚመርጥበት አጋጣሚ የመኖሩን ያህል ወላጆች ወይም ተወላጆች በመሆናቸው ብቻ የተቆርቋሪነት ስሜት ሊያድርበት የማይችልበት አጋጣሚ ሊኖር እንደሚችል መገንዘብ ይችላል፡፡

ከዚህ አኳያ ሲታይ ቀደም ሲል የነበረውን ድንጋጌ በማሻሻል ለተጋቢው ቅርብ በሆነ ሰው ላይ ሊፈፀም የተቃረበን አደጋ ለማስወገድ ወይም ለማዳን በማቀድ የሚደረግ ጋብቻ ፈራሽ ሊሆን የሚችልበት ተጨማሪ ሁኔታ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

<u>አንቀጽ 15 በፍርድ የተከለከለ ሰው ጋብቻ</u>

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 588 የተመለከተው ድንጋጌ መሠረታዊ ለውጥ የሚያስፈልገው ሆኖ አልተገኘም ሆኖም በክፍል 1 ሥር ሊካተቱ የሚገባቸው በፍርድ የተከለከለ ሰው ፈቃድ ማግኘት የሚገባው ስለመሆኑና የፈቃድ ጥያቄውን ማን ማቅረብ እንዳለበት የሚደነግገው ክፍል ብቻ በመሆኑ የጋብቻ ውል ስምምነት የሚፈጽምበትን ሁኔታ ሥርዓት የሚመለከተው ክፍል እንዲወጣ ተደርጓል፡፡ የፈቃድ ጥያቄው ሊቀርብ የሚገባ ለፍ/ቤት እንጂ ለዳኛ ባለመሆኑ በዚህ ረገድ የአገላለጽ ለውጥ ተደርጓል፡፡

<u>አንቀጽ 16 በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነ ጊዜ</u>

ይህ ድንጋጌ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 596 የተመለከተ ሲሆን የጽንስ ሀሳብ ለውጥ የሚያስፈልገው እንዳልሆነ የታመነ ቢሆንም አንዲት ሴት አስቀድሞ የነበራት ጋብቻ ከቀረ በኃላ የወለደች እንደሆነ ወይም እርግዝና የሌላት ስለመሆኑ በሕክምና ከተረጋገጠ

www.abyssinialaw.com

በመርህ ደረጃ የተቀመጠውን የጊዜ ገደብ መጠበቅ የማይገባት በመሆኑ ይኸው ሁኔታ በተጨማሪ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

በፍ/ብ/ሕጉ ለዳኞች የተሰጠው ሥልጣን ፍ/ቤቶችን የሚመለከት በመሆኑ በዚህ መልክ ተሻሽሏል፡፡ ይህ ድንጋጌ ምንም እንኳ በሴቲቱ ላይ አላስፈላጊ ጫና የሚፈጥር ቢመስልም ከሚለወደው ልጅ መብት አንፃር ማለትም ወላጆቹን የማወቅና ከወላጆቹ እንክብካቤ የማግኘት ሕገ መንግስታዊ መብት አኳያ ሴቲቱ እርግዝናውን የምትሸከም በመሆዋ በልጁ አባት ማንነት ላይ አከራካሪ ሁኔታ እንዳይፈጥር ለማድረግ የተቀመጠ ድንጋጌ እንደሆነ ታምኖበታል፡፡

## ክፍል 2

## ጋብቻ እንዳይፈፀም ስለመቃወም

በዚህ ክፍል የተመለከቱት ድንጋጌዎች በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 592-595 ያሉትን የሚመለከቱ ሲሆን ጋብቻ ለመፈፀም መሟላት ስለሚኖርባቸው ጉዳዮች ከሰፈሩት ድንጋጌዎች ጋር አብሮ ሊታይ የማይገባ በመሆኑ የተለየ ክፍል እንዲኖር ተደርጓል፡፡

በክፍል 2 ሥር የሰፈሩት ድንጋጌዎች ጋብቻ እንዳይፈፀም የሚቀርብ ተቃውሞ የት እንዴትና በማን መቅረብ እንዳለበትና በተቃውሞው ላይ ውሳኔ የሚሰጥበትን ሥርዓት የሚያመለክቱ በመሆናቸው ርዕሱ 'ጋብቻ እንዳይፈፀም ስለመቃወም' በሚል አገላለጽ እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡

### አንቀጽ 17 ስለመቃወም

ለጋብቻ አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎች ሳይሟሉ የተፈፀመን ጋብቻ መቃወም እንደሚቻል በግልጽ ማመልከት ስለሚገባ ይህ ድንጋጌ በተለይ እንዲቀጥ ተደርጓል፡፡

### አንቀጽ 18 መቃወም ስለሚችሉ ወገኖች

በሕግ የሚፀና ጋብቻ ለመፈፀም የተደነገጉት ሁኔታዎች የተለያዩ እንደመሆናቸው መጠን ተቃውሞ ሊያቀርቡ የሚገባቸውን ወገኖች በተመሣሣይ አኳኃን መመልከቱ አግባብነት የሌለው ሆኖ በመገኘቱ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 592 ለሁሉም ምክንያቶች በጥቅሉ የተቀመጠው ድንጋጌ ማሻሻያ ተደርጓበታል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት በአንድ በኩል በሁኔታነት ለተቀመጡት ጉዳዮች አግባብነት የሚኖረውን ወገን ለይቶ ለማስቀመጥ ሲሆን በሌላ በኩል ጋብቻ በታቀደለት ጊዜ እንዳይፈፀም መሰናክል ሊፈጥሩ የሚችሉ ሌሎች ተቃውሞ አቅራቢዎች ጥያቄ ሊታገድ የማይገባው መሆኑን ለማመልከት ነው በሕግ የተወሰነው የጋብቻ መፈፀሚያ ዝቅተኛ ዕድሜ ሳይደርስ ሊፈፀም የታቀደን ጋብቻ ወላጆች ወይም ዐቃቤ ሕግ ወይም ሌላ ማንኛውም ያገባኛል የሚል ሰው ተቃውሞ እንዲያቀርብ ተደርጓል፡፡ በተለያዩ ጊዜያት የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ከሴቶች ጤና እንዲሁም ቤተሰብአዊ አኗኗር ጋር በተያያዙ የሚያጋጥሙ ችግሮች ያለዕድሜ ጋብቻ በሚፈጽሙ ወጣቶች ላይ እንደሆነ በመረጋገጡ ያለዕድሜ የሚፈፀምን ጋብቻ ለመቃወም የማንኛውም ተቆርቋሪ የሕብረተሰብ ክፍል ኃላፊነትና ግዴታ በመሆኑ ያገባኛል የሚል ሰው ሁሉ ተቃውሞ እንዲያቀርብ መፍቀድ አግባብነት ያለው መሆኑ ታምኖበታል፡፡ ያገባኛል የሚል ሰው ግን እንዲሁ አላፊ አግዳሚው ለማለት ሳይሆን በእንግሊዘኛው interested party የሚለውን የሚተካ ሲሆን የጉዳዩ ባንድ

www.abyssinialaw.com

ወይም በሌላ መልኩ መወሰን ጥቅሙን የሚነካበት ሊሆን ይገባል:: የሴቶች ወይም የህፃናት መብት ተከራካሪ ድርጅቶች በዚህ ጉዳይ አግባብነት ሊኖራቸው ይችላል::

ተጋቢዎች በሕግ በተገደበው ጋብቻ ወይም የሥጋ ዝምድና ደረጃ ውስጥ የሚገኙ መሆናቸውን ለመቃወም የሚችሉት ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ወይም 18 ዓመት የሞላቸው ወንድም/እህቶች ወይም ዐቃቢ ሕግ እንዲሆን ተደርጓል::

በጋብቻ ላይ ጋብቻ በሚል መቃወሚያ ሊቀርብ የሚገባው የቀድሞ ጋብቻ አለኝ በሚል ወገን ወይም ዐቃቢ ሕግ እንዲሆን የተደረገ ሲሆን በፍርድ የተከለከለ ሰው በሕግ የሚጠየቀውን የፈቃድ ጥያቄ ሳያሟላ ሊፈፅም ያቀደውን ጋብቻ መቃወም የሚገባቸው አሳዳሪው ወይም ዐቃቢ ሕግ ሊሆኑ እንደሚገባ ታምኖበታል::

<u>አንቀጽ 19</u> <u>መቃወሚያ ስለሚቀርብበት ሥነ ሥርዓት</u>

በጋብቻ ላይ የሚቀርቡ ተቃውሞዎችን መርምሮ አግባብነታቸውን ለመወሰን የተወሰነ ጊዜ እንደሚጠይቅ በማመን ተቃውሞ የሚቀርብበትን የጊዜ ገደብና ሥርዓት ማስቀመጥ በማስፈለጉ ተቃውሞው በጽሁፍ እንዲሆንና ጋብቻው ከሚፈፀምበት ከ15 ቀን በፊት ለጋብቻ አስፈፃሚው ባለሥልጣን ሊቀርብ እንደሚገባ ተደንግጓል::

<u>አንቀጽ 20 እና 21</u> <u>በመቃወሚያ ላይ ስለሚሰጠው ውሳኔ</u>

ጋብቻ እንዳይፈፀም የሚቀርብ ተቃውሞ በአጭር ጊዜ ውስጥ ታይቶ ውሳኔ ሊያገኝ የሚገባ በመሆኑ በአምስት ቀን ውስጥ ውሳኔ እንዲያገኝ በማንኛውም ጉዳይ ተፈፃሚ የሚሆኑ የክርክር ሥርዓቶችን እንዲከተል ማድረጉ አግባብነት የሌለው በመሆኑ ተቃውሞውን ባለመቀበል በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ እንዲኖር አልተደረገም::

በሌላ በኩል የጋብቻ አስፈፃሚው ባለሥልጣን የቀረበውን ተቃውሞ በመቀበል ጋብቻ እንዳይፈጸም የሚሰጠው ውሳኔ ክርክር ሊያስነሳ የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር የሚችል በመሆኑ ውሳኔውን ለመደበኛ ፍ/ቤት በይግባኝ የሚቻልበት ሥርዓት እንዲኖር ተደርጓል::

## <u>ክፍል 3</u>

## <u>በክብር መዝገብ ሹም ፊት ስለሚፈፀም ጋብቻ</u>

በክፍል 3 ሥር የተካተቱት ጉዳዩች በፍ/ብ/ሕግ ከቁጥር 597-604 የተዘረዘሩትን ድንጋጌዎች ይመለከታል በክብር መዝገብ ሹም ጽ/ቤት ስለሚፈፀም ጋብቻ የሚኖረውን ሥርዓት ከአንቀጽ 22-25 የተመለከቱት ድንጋጌዎች በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 597፣599፣ 602፣ 603፣ እና 604 ላይ በዝርዝር የሰፈሩትን የሚያጠቃልል ሲሆን በክብር መዝገብ ሹም ፊት የሚፈፀም ጋብቻ እንዴት ሊቀርብ እንደሚገባ ተጋቢዎችም ሆኑ ጋብቻ የሚፈፀምበት ጽ/ቤት ሊያከናውኑ የሚገባቸው ሥራዎች ምን እንደሆኑ በቅደም ተከተል ያስቀምጣል::

በአንቀጽ 22 የሰፈረው ጉዳይ መጠነኛ የቃላት ለውጥ ከማድረ በስተቀር በፍ/ብ/ሕጉ አንቀጽ 597 የሰፈረውን ድንጋጌ አንዳለ የሚያካትት ነው::

www.abyssinialaw.com

በአንቀጽ 23 ተቃውሞ ሊቀርብ የሚችልበትን ጊዜ ከግምት ውስጥ በማስገባት ጋብቻ ለመፈፀም ጥያቄ የሚቀርብበት ጊዜ በፍ/ብ/ሕጉ የነበረውን በማሻሻል ከ 5 ወደ 15 ቀን ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡

በአንቀጽ 24 መሠረት የጋብቻ ሁኔታዎች አለመጣሳቸውን ለማረጋገጥ ተቃውሞ የሚያቀርብ መሆንና ያለመሆኑን ለማወቅ እንዲቻል የክብር መዝገብ ሹሙ ሊፈፀም የታቀደውን ጋብቻ አመቺ በሆነ መንገድ ማስታወቅ እንደሚኖርበት በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 602 ከሰፈረው በተጨማሪ ግዴታ የሚጥል ድንጋጌ እንዲኖር ተደርጓል፡፡

በፍ/ብ/ሕጉ ቁጥር 603 እና 604 የጋብቻውን አፈፃፀም ሥርዓት የሚመለከቱ ሁኔታዎች ሲሆኑ መጠነኛ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡ በአንቀጽ 25 ሥር እንዲጠቃለሉ ተደርጓል፡፡ ተሻሽሎ በተቀረፀው ድንጋጌ በተጋቢዎችና ምስክሮቻቸው የጋብቻ ሁኔታዎች በመጣሳቸው የሚያስከትለውን ኃላፊነት እንዲረዱ ለማድረግ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን እንዲያንፀባርቁ ተደርጓል፡፡

## ክፍል 4

## ሌሎች የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓቶች

በዚህ ክፍል ሥር በአንቀጽ 26 እና 27 የተመለከቱት ጉዳዮች በፍ/ብ/ሕግ በክፍል 3 በአንቀጽ 605 እና 606 ኃይማኖታዊና ባህላዊ ጋብቻዎችን በተመለከተ የሰፈሩት ድንጋጌዎች ሲሆኑ የቤተሰብ ሕጉ ራሱን ችሎ የሚወጣ በመሆኑ ከሌሎች የፍ/ብሔር ሕጉ ክፍሎች በመጣቀስ የሰፈሩት ሁኔታዎች እንዲወጡና መጠነኛ የቃላት ለውጥ ከመደረጉ በስተቀር የጽንሰ ሀሳብ ችግር የሌለባቸው በመሆኑ መሠረታዊ ለውጥ ሳያስፈልጋቸው እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

## ክፍል 5

## ስለ ጋብቻ ምዝገባ

በዚህ ክፍል ሥር የተመለከቱት ድንጋጌዎች በፍ/ብ/ሕግ አንደኛ መጽሀፍ ስለ ሰዎች በምዕራፍ 2 ክፍል 3 ንዑስ ክፍል 4 በአንቀጽ 117-120 ያሉትን የሚያጠቃልል ነው፡፡

በማናቸውም ዓይነት የአፈፃፀም ሥርዓት የሚፈፀም ጋብቻ አንድወጥ በሆነ የምዝገባ ሥርዓት ተመዝግቦ ሊቀመጥ የሚገባው በመሆኑና በተለይም በባህላዊና በሀይማኖታዊ ጋብቻ የሚፈፀሙ ጋብቻዎች ብዙውን ጊዜ ስለማይመዘገቡ መመዝገባቸውን ለማረጋገጥ ያስችላል ተብሎ ስለታመነበት በአንቀጽ 28 ሥር ጋብቻን ማስመዝገብ ግዴታ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡

ጋብቻ መፈፀሙ እስከታወቀ ድረስ የክብር መዝገብ ሹም የጋብቻ መዝገብ ማደራጀት እንደሚኖርበት የሚጠይቅ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 120 የተመለከተውን በማሻሻል በአንቀጽ 29 አስገዳጅነት እንዲኖረው ተደርጓል፡፡

www.abyssinialaw.com

በአንቀጽ 30 በጋብቻ መዝገብ ላይ ሊጠቀሱ ስለሚገባቸው ዝርዝሮች በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 117 ሥር የተመለከተውን የሚያጠቃልል ሲሆን በጋብቻ መዝገብ እንዲሰፍሩ የጠየቁት የቤተዘመድና የግል ስሞች በሃገራችን ተፈፃሚነት የሌላቸው በመሆኑ እንዲወጡ የተደረገ ሲሆን ጋብቻው የተፈፀመበት ሥርዓትና ቦታ በጋብቻው መዝገብ ውስጥ እንዲሰፍሩ ማድረግ እንደሚገባ ተመልክቷል።

## ምዕራፍ 2

## የጋብቻ ሁኔታዎች አለመሟላታቸው የሚያስከትለው ውጤት

በምዕራፍ 2 ሥር ከአንቀጽ /31-39/ የተመለከቱት ድንጋጌዎች በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር /607-620/ ያሉትን ይመለከታል። የጋብቻ ሁኔታዎች ሳይጠበቁ የሚፈፀም ጋብቻ የፍትሐብሔርም ሆነ የወንጀል ኃላፊነት የሚያስከትል ውጤት ይኖረዋል። የፍ/ብሔር ሕጉ ሁለቱንም ኃላፊነቶች የሚያመለክቱ ድንጋጌዎች ይዟል።

የጋብቻ ሁኔታዎች በማንኛውም ተጋቢ ሆነ ከጋብቻው ጋር አግባብነት የሚኖራቸው ወገኖች ሊከበሩ የሚገባ ወይም ሊጣሱ የማይገባ መሠረታዊ ጉዳዮች በመሆናቸው በቤተሰብ ሕጉ የሰፈሩትን የጋብቻ ሁኔታዎች ባለማክበር የሚፈፀም ጋብቻ የሚያስከትለው የወንጀል ኃላፊነት በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ሊካተት የሚገባ በመሆኑ በጋብቻው ላይ የሚኖረው ውጤት ብቻ ተለይቶ እንዲሰፍር ተደርጓል።

ይህ ድንጋጌ የፍ/ብ/ሕግ አንቀጽ 608ን የሚመለከት ሲሆን መጠነኛ የአገላለጽ ለውጥ የተደረገበት ሲሆን የተጠየቀው ዕድሜ ሳይሟላ የተፈፀመን ጋብቻ እንዲፈርስ ጥያቄ ማቅረብ እንደሚቻል ጥያቄውም በማንኛውም ባለጉዳይ ወይም በዐቃቢ ሕግ ሊቀርብ የሚችል እንደሆነ ተመልክቷል። ሆኖም ጋብቻ እንዲፈርስ ጥያቄ ሲቀርብ የተጋቢዎቹ ዕድሜ ሕጉ የሚጠይቀው ዝቀተኛ ዕድሜ ከደረሰ ጋብቻ እንዲፈርስ ጥያቄ ሊቀርብ አይችልም ቢቀርብም ጋብቻው እንዲፈርስ ሊወስን አይገባውም።

### አንቀጽ 32 የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና

ይህ አንቀጽ በፍ/ብሔር ሕግ ቁጥር 609 የሰፈረውን የሚመለከት ሲሆን ከርዕሱ ጋር ለማጣጣም የክልከላውን ምክንያት ከመግለጽ በስተቀር ማሻሻያ ሳያስፈልገው እንዲቀጥል ተደርጓል።

### አንቀጽ 33 በጋብቻ ላይ ጋብቻ

በጋብቻ ላይ ጋብቻ ተፈጽሞ ሲገኝ ጋብቻው ስለሚፈርስበት ሁኔታ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 612 እና 613 ሥር የሰፈሩትን ድንጋጌዎች በማጠቃለል ጋብቻው እንዲፈርስ ጥያቄ የሚቀርበው የመጀመሪያ ጋብቻ አለኝ ከሚለው ተጋቢ በተጨማሪ በሁለተኛው ተጋቢም ጭምር እንዲሆን ተደርጓል።

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 612/2/ የሰፈረው ድንጋጌ የአገላለጽ ለውጥ የሚያስፈልገው ሲሆን የመጀመሪያው ተጋቢ መሞቱ ከታወቀ በጋብቻ ላይ ጋብቻ ተፈጽሟል በማለት

www.abyssinialaw.com

ጋብቻው እንዲፈርስ ጥያቄ ማቅረብ የማይቻል በመሆኑ ድንጋጌው ይህንኑ ሁኔታ እንዲያካትት ተደርጓል፡፡

<u>አንቀጽ 34 በፍርድ ክልከላ ምክንያት ጋብቻን ስለማፍረስ</u>

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 614 መሠረት ችሎታ በሌለው ሰው የተፈፀመ ጋብቻ እንደሆነ የተገለፀው በአዕምሮ መናወጽ የተከለከለ ወይም አካለመጠን ያላደረሰ ሰው የሚፈጽመውን ጋብቻ ነው፡፡ አካለመጠን ባላደረሰው ሰው የሚፈፀም ጋብቻ ስለሚፈርስበት ሁኔታ በዚሁ ምዕራፍ አንቀጽ 31 በግልጽ የተቀመጠ በመሆኑ ድንጋጌው በአዕምሮ መናወጽ ምክንያት ክልከላ የተደረገባቸውን ሰዎች የሚመለከተውን ክፍል ብቻ እንዲይዝ ተደርጓል፡፡

በዚህ መሠረት በፍ/ብ/ ሕግ ቁጥር 614 እና 615 ሥር የሰፈረውን ድንጋጌ በማሻሻል በፍርድ የተከለከለ ሰው ጋብቻ ለመፈፀም የፍ/ቤት ፈቃድ የሚያስፈልገው በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 614 እና 615 የተካተቱትን ከዚህ ምዕራፍ ጋር በሚስማማ አኳኃን መደንገግ በማስፈለጉ መጠነኛ የአገላለጽ ለውጥ ተደርጓል፡፡

<u>አንቀጽ 35 በኃይል የተፈፀመን ጋብቻ ስለማፍረስ</u>

ይህ አንቀጽ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 616-617 የሰፈሩትን ድንጋጌዎች የሚመለከት ሲሆን በርዕሱና በአገላለፁ ላይ መጠነኛ ለውጥ ከማድረግ በቀር በጽንሰ ሃሳብ ደረጃ ማሻሻያ የማያስፈልገው በመሆኑ እንዳለ እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡

<u>አንቀጽ 36 በስህተት ምክንያት የተፈፀመን ጋብቻ ስለማፍረስ</u>

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 618 የተመለከተው ድንጋጌ የአገላለጽ ለውጥ ተደርጐበት በዚህ ድንጋጌ እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡

<u>አንቀጽ 37 በብቸኝነት የተወሰነውን ጊዜ ስለመጠበቅ</u>

ይህ ድንጋጌ ከፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 620 የተወሰደ ሲሆን ማሻሻያ ሳያስፈልገው እንዲወሰድ ተደርጓል፡፡

<u>አንቀጽ 38 የክብር መዝገብ ሹም ሥልጣን የሌለው ስለመሆኑ</u>

በአንቀጽ 22 መሠረት ጋብቻውን የማስፈፀም ሥልጣን ያለው የክብር መዝገብ ሹም ከተጋቢዎቹ አንዱ ወይም ከተጋቢዎቹ ወላጆች ወይም የቅርብ ዘመዶች አንዱ ለስድስት ወራት ሳያቋርጡ የኖሩበት ቦታ ያለው የክብር መዝገብ ሹም ቢሆንም በሌላ የክብር መዝገብ ሹም ፊት መፈፀሙ ጋብቻውን የማፍረስ ውጤት እንደሌለው ለማስገንዘብ ታስቦ የተቀረፀ አንቀጽ ነው፡፡

<u>አንቀጽ 39 የሥነ ሥርዓት አለመጠበቅ</u>

መለስተኛ የሥነ ሥርዓት ግድፈቶች መፈፀማቸው ጋብቻ እንዲፈርስ ለማስወሰን በቂ እንዳልሆኑ የተቀመጠ ድንጋጌ ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

## ምዕራፍ 3

## የጋብቻ ውጤት

## ክፍል 1

## ጠቅላላ ደንቦች

በዚህ ምዕራፍ ሥር የተመለከቱት በፍ/ብ/ሕጉ ከቁጥር 625-634 ያሉትን ድንጋጌዎች የሚመለከት ሲሆን በአገላለጽና በጽንሰ ሐሳብ ደረጃ ለውጥ በሚያስፈልጋቸው ላይ ማሻሻያ ተደርጐባቸው እንዲቀጥሉ ተደርጓል፡፡

### አንቀጽ 40 ሁሉም የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓቶች ተመሣሣይ ውጤት ያላቸው ስለመሆኑ

ይህ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 625 የተመለከተው ድንጋጌ ሲሆን አፈፃፀሙ ሊለያይ የሚችል ቢሆንም ሁሉም የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓቶች ተመሣሣይ ውጤት የሚኖራቸው መሆኑን በሚያመክት አገላለጽ ከእንግሊዘኛው ቅጂ ጋር በሚስማማ አኳኃን ተሻሽሎ እንዲቀረፅ ተደርጓል፡፡ የባህል ወይም የሃይማኖት ሕግጋትንና ደንቦች የተለየ ውጤት ሊኖራቸው እንደማይችል ለማመልከት ንዑስ ቁጥር /2/ ልማድ የሚለው ባህል በሚል ተተክቶ ባለበት እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡

### አንቀጽ 41 የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት መፈፀም

በአንዳንድ ባህላዊና ሀይማኖት ሕጐችና ደንቦች ጋብቻ ውጤትን የሚያስከትለው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከተፈፀመ በኃላ እንደሆነ የሚገልጹ አመለካከቶች እንዳሉ መገንዘብ የሚቻል ቢሆንም በየትኛውም የአፈፃፀም ሥርዓት የተፈፀመ ጋብቻ ውጤት የሚያስከትለው ጋብቻ በመፈፀሙ ምክንያት እንደሆነ ማመልከቱ አስፈላጊ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 626 የሰፈረው ድንጋጌ ማሻሻያ ሳያስፈልገው ባለበት እንዲወሰድ ተደርጓል፡፡

### አንቀጽ 42 የጋብቻ ውል

ይህ ድንጋጌ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 627 ን የሚመለከት ሲሆን የጋብቻ ውል ከጋብቻው የተለየ መሆኑን በግልጽ ያመለክታል፡፡ በዚህም መሠረት በንዑስ ቁጥር 1 'የተጋቢዎችን ገንዘብ' በተመለከተ የሰፈረው አገላለጽ የተሟላ ሆኖ ባለመገኘቱ ተጋቢዎች የሚያደርጉት ውል አጠቃላይ የንብረት ግንኙነታቸውን በተመለከተ ሊሆን እንደሚገባ ታምኖበታል፡፡

የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 627/2/ በእንግሊዘኛው ቅጂ ላይ የተመለከተው ተጋቢዎች በመካከላቸው ያለው ግንኙነት የሚኖራቸውን መብትና ግዴታ በሚመለከት በውሉ መወሰን እንደሚችሉ የሚያመለክት በመሆኑና አግባብነት የሚኖረው ይኸው አገላለጽ ሆኖ በመገኘቱ ይኸው ማሻሻያ ተደርጓል፡፡

በዚህም ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር 3 የሰፈረው ግልጽ በሆነ አገላለጽ ሊሰፍር የሚገባው በመሆኑ ተጋቢዎች የሚያደርጓቸው ውሎች በሕግ የተቀመጡ ድንጋጌዎችን የሚቃረን መሆን እንደሌለበት ተመልክቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ 43 የተጋቢዎች ችሎታ ማጣት

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 628 ችሎታ የሌለው ተጋቢ የሚያደርገውን ውል በተመለከተ በሶስት ንዑሳን አንቀጾች የተቀመጠ ሲሆን የጋብቻ ዕድሜ ለሁሉም 18 እንዲሆን የተደረገ በመሆኑ አካለመጠን ያላደረሱ ልጆች የሚያደርጉትን የጋብቻ ውል በተመለከተ የሰፈረው ድንጋጌ አላስፈላጊ በመሆኑ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

በዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 2 እና 3 የሰፈሩት ሁኔታዎች ቀጣይነት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ መጠነኛ የቃላት ለውጥ በማድረግ እንዲጸለ ተወስደዋል፡፡

አንቀጽ 44 የውሉ ፎርም

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 629 ስለጋብቻ ውል ፎርም በሰፈረው ድንጋጌ መጠነኛ ለውጥ ተደርጓል፡፡

አንቀጽ 45 የውሉ ሰነድ ስለሚቀመጥበት ቦታ

በዚህ ድንጋጌ ሥር የተመለከተው ጉዳይ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 630 የውሉ ጽሁፍ ስለሚቀመጥበት ቦታ የሰፈረውን ይመለከታል፡፡

የውሉ ቅጂ የሚቀመጥበት ቦታ በቤተሰብ ሕጉ አግባብ ያላቸው ክፍሎች ፍ/ቤት ወይም የክብር መዝገብ ሹም በመሆናቸው በዚህ አኳኃን ተሻሽሎ እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡

በሌላ በኩል የሶስተኛ ወገኖችን ጥቅም ከማስጠበቅ አኳያ እንዲሁም ተጋቢዎች ሰነድን በፈለጉ ጊዜ ማየት የሚችሉበት ሥርዐት ሊኖር ስለሚገባ የጋብቻ ውሉን ለማየት የሚፈቀድላቸው ሰዎች ተጋቢዎቹ ወይንም ከተጋቢዎቹ አንዱ እንዲሁም ፍ/ቤት ወይም ከተጋቢዎቹ አንዱ የፈቀደላቸው ሰዎች እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የክብር መዝገብ ሹም ጽ/ቤት ካልተቋቋመ በዚህ ሕግም ሆነ በሌሎች ሕጎች ዕውቅናና ጥበቃ የሚደረግላቸው ጉዳዩች ዋጋ ስለሚያጡ የጽ/ቤቱ መቋቋም የግድ መሆን አለበት፡፡

አንቀጽ 46 ውል ለመዋዋል ስላለው የነፃነት ወሰን

ይህ ድንጋጌ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 631 የተመለከተው ሲሆን የጋብቻ ውሉ ሶስተኛ ወገኖችን የማይመለከታቸው መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡ እንደ ድንጋጌው አገላለጽ ከሆነ የውሉን ሰነድ ሶስተኛ ወገኖች ማየት እንደማይጠበቅባቸው ያመለክታል፡፡

በመሆኑም ይህ ድንጋጌ ማሻሻያ የሚያስፈልገው በመሆኑ ተጋቢዎች በሌሎች ሶስተኛ ወገኖች ላይ ማንኛውም ግዴታ የሚያስከትሉ ስምምነቶችን ማድረግ እንደማይችሉ በሚገልጽ አገላለጽ እንዲሰፍር ተደርጓል፡፡ በንዑስ ቁጥር 2 የሰፈረው ጠቅላላ አነጋገር ግልጽ በሆነ አገላለጽ ማሻሻያ ተደርጐበታል፡፡

አንቀጽ 47 የጋብቻ ውልን ስለማሻሻል

በፍ/ብ/ ሕጉ ለቤተዘመድ ሽምግልና ጉባኤ ተሰጥቶ የነበረው ሰፊ ስልጣን ተገድቦ በማስታረቅ ላይ ብቻ እንዲያተኩር በመወሰኑ የጋብቻ ውል ለማሻሻል የሚቀርብ ጥያቄ

www.abyssinialaw.com

የቤተሰቡን ጥቅም የሚያስጠብቅ መሆን አለመሆኑ እየታየ በፍ/ቤት በኩል እንዲፀድቅ ተደንግጓል፡፡ የጋብቻ ውል በማናቸውም ምክንያት የሚለዋወጥ ከሆነ በጋብቻው ላይ ከሚፈጥረው ችግር በተጨማሪ በአንደኛው ተጋቢና በሶስተኛ ወገኖች ጥቅም ላይ ጉዳት ሊያስከትል እንደሚችል ይታመናል፡፡

በመሆኑም የጋብቻ ውልን ለማሻሻል የሚቻለው የቤተሰቡን ጥቅም የሚጠብቅ ሆኖ ሲገኝና ሁለቱም ተጋቢዎች ሲስማሙ ብቻ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 632/1//2/ የተመለከተው ድንጋጌ ማሻሻያ ተደርጎበታል፡፡

የተሻሻለው የጋብቻ ውል ሰነድ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 45 መሠረት የመጀመሪያው ውል በተቀመጠበት በፍ/ቤት ወይም በክብር መዝገብ ሹም ጽ/ቤት ሊቀመጥ የሚገባ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 632 ንዑስ ቁጥር 3 የሰፈረው ድንጋጌ ተሻሽሏል፡፡

<u>አንቀጽ 48 የሕግ ተፈፃሚነት</u>

ጋብቻው በንብረታቸው በኩልም ሆነ ግላዊ ግንኙነታቸውን በተመለከተ ስለሚያስከትለው ውጤት ተጋቢዎች የጋብቻ ውል ባለማድረጋቸው ወይም ያደረጉት የጋብቻ ውል ሳይፀና የቀረ ከሆነ ይህንኑ በተመለከተ በቤተሰብ ሕጉ የፈሰሩት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ መሆናቸውን ለመግለጽ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 634 ሕጋዊ አስተዳደር የሚለው የሕግ ተፈፃሚነት በሚል የተሻሻለ ሲሆን በድንጋጌው ላይ አስፈላጊ የቃላት ለውጥ ተደርጓል፡፡

በሌላ በኩል ተጋቢዎቹ በመካከላቸው ስለሚያደርጉት ውል በፍ/ሕጉ በቁጥር 633 የተደነገገውን በዚህ ክፍል ሥር ማስቀመጥ ከላይ በአንቀጽ 42 ከተደነገገው ጋር ሊሳከር ስለሚችል ከዚህ በታች በክፍል 3 ሥር ተሻሽሎ ተቀምጧል፡፡ /አንቀጽ 73/

<u>ክፍል 2</u>

<u>ጋብቻ በተጋቢዎች ግላዊ ግንኙነት ላይ ስለሚኖረው ውጤት</u>

በክፍል 2 ሥር የተመለከቱት ጉዳዩች በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 635-643 ያሉትን ድንጋጌዎች የሚያጠቃልሉ ናቸው፡፡

በፍ/ብሔር ሕጉ ጋብቻ በሰዎች ላይ ያለው ውጤት በሚል የሰፈረው አገላለጽ በሥሩ ከተቀመጡ ዝርዝር ጉዳዩች ጋር ተስማሚ ካለመሆኑ በተጨማሪ ግልጽ ትርጉም ስለማይሰጥ ’ጋብቻ በተጋቢዎች ግላዊ ግንኙነት ላይ ስለሚኖረው ውጤት’ በሚል ተሻሽሎ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 25፣ 34/1/ እና 35/1/፣/2/ እንዲሁም ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት ተጋቢዎች እኩል መሆናቸው የተደነገገ በመሆኑ በተጋቢዎች መካከል ልዩነትን የሚፈጥሩና አስፈላጊ ያልሆኑ ድንጋጌዎች እንዲወጡ ወይም ተሻሽለው እንዲቀረጹ ተደርጓል፡፡ ከዚህ አንፃር በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 635 የተደነገገው እንዳለ ተሠርዟል፡፡

www.abyssinialaw.com

<u>አንቀጽ 49 መከባበር፣ መተጋገዝ፣ መደጋገፍ፣</u>

ይህ ድንጋጌ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 636 የተመለከተው ሲሆን የእንግሊዘኛው ቅጂ ይበልጥ ግልጽ በመሆኑና በተለይም "support" የሚለው ቃል የሚያመለክትው መደጋገፍን እንጂ መረዳዳትን እንዳልሆነ ለመገንዘብ በመቻሉ በዚህ ላይ ማሻሻያ ተደረጐበት የድንጋጌው መኖር አስፈላጊ በመሆኑ ባለበት ተወስዷል፡፡ ስለሆነም /respect/ ከከባበርን /support/ አንዱ ሌላውን መርዳትን /assistance/ አንዱ ሌላውን ማገዝን የሚያመለክቱ ግዴታዎች መሆናቸውን ያመለክታሉ፡፡

<u>አንቀጽ 50 የቤተሰብ የጋራ አመራር /1/ ጠቅላላ</u>

በፍ/ብ/ ሕግ ቁጥር 637 የሰፈረው ድንጋጌ ከርዕሱ ጀምሮ የጽንሰ ሀሳብና የአገላለጽ ችግር የሚታይበት በመሆኑ ተገቢው ማሻሻያ ተደርጐበታል፡፡ የቤተሰብን ጥቅም ማስጠበቅ እንዲቻል አመራር በእኩልነት ደረጃ በጋራ መከናወን እንደሚገባውና በልጆች አስተዳደግና አያያዝ ረገድ የቤተሰብ አመራር ምን መምስል እንዳለበት በሚገልጽ ሁኔታ ተደንግጓል፡፡

ተጋቢዎች ግላዊ ግንኙነታቸውን በሚመለከት አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌዎችን በማይቃረን አኳኃን በጋብቻ ውላቸው መወሰን እንደሚችሉ በአንቀጽ 42 /2/ የተደነገገ በመሆኑና የቤተሰብ አመራርም የዚሁ አካል በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 637/2/ የተቀመጠው ድንጋጌ ቀጣይነት ታምኖበት እንዲካተት ተደርጓል፡፡

<u>አንቀጽ 51 ከተጋዎቹ የአንዱ ቤተሰቡን ለመምራት አለመቻል</u>

ይህ ድንጋጌ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 638ትን ይመለከታል፡፡ የቤተሰብን አመራር በጋራ ማከናወን የማይቻልበት ሁኔታ ሲያጋጥም በአንደኛው ተጋቢ መከናወን የሚቻል መሆኑን የሚገልጽ ሲሆን ይህም የሚሆነው በአንደኛው ተጋቢ ችሎታ ማጣት፣ በስፍራው አለመገኘት እና ቤተሰቡን በመተው የጠፋ እንደሆነ ነው፡፡ ርዕሱ የአንድን ተጋቢ መታወክ ብቻ የሚያመለክት ከመሆኑ በቀር በድንጋጌው ሥር የሰፈሩትን ሁኔታዎች በተሟላ ደረጃ የሚያመለክት ባለመሆኑ አንደኛው ተጋቢ ቤተሰብን ለመምራት የማይችልባቸው ሁኔታዎች ምን እንደሆኑ በግልጽ ተመልክቷል፡፡

በሌላ በኩል በስፍራው የማይገኝ የሚለው አገላለጽ በእንግሊዝኛው "absent" የሚለውን ለማመልከት እንደሆነ ለመገንዘብ በመቻሉና የመጥፋት ውሳኔ የተላለፈበትን ሰው የማያመለክት በመሆኑ 'የጠፋ' በሚል ቃል ተተክቷል፡፡ ስለሆነም ለዚህ አንቀጽ ዓላማ የመጥፋት ውሳኔ መስጠቱ የግድ አስፈላጊ አይሆንም፡፡ የቤተሰብ አመራሩን አንደኛው ተጋቢ ማከናወንም ሆነ ሀሳቡን መግለጽ የማያስችለው ምክንያት መኖሩ ከታወቀ ሌላኛው ተጋቢ የሚያከናውንበትን ሁኔታ እንዲያካትት ተደርጓል፡፡ አንደኛው ተጋቢ በትምህርት ወይም በሥራ ምክንያት በስፍራው የማይገኝበት ሁኔታ ሲያጋጥም፣ በከባድ ሕመም ምክንያት ሀሳቡን መግለጽ የማይችል ሲሆን፣ ወይም ለጊዜው ሊጠቀሱ የማይችሉ ሌሎች ተመሣሣይ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት ስለሚገባ ገላጭ በሆነ አገላለጽ ፈቃድን መስጠት የማያስችል ሁኔታ ሲያጋጥም የቤተሰቡን አመራር ሌላኛው ተጋቢ ለማከናወን እንደሚችል ሆኖ ተቀርጿል፡፡

የጋብቻ ውል እነዚህን ሁኔታዎች የሚቃረን ሊሆን የማይገባው በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 638/3/ መጠነኛ የሆነ ማሻሻያ ተደርጐበት እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡

<u>አንቀጽ 52 ከጋብቻ በፊት ከሌላ ስለተወለደ ልጅ</u>

www.abyssinialaw.com

በልጆች አስተዳደግ ላይ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን የወላጅ እንዲሆን ማድረግ በልጆች አስተዳደግና አያያዝ ላይ የሚነሱ ክርክሮችንና አላስፈላጊ ውዝግቦችን የሚያስቀር እንደሚሆን ታምኖበታል፡፡ በአንፃሩም ወላጅ ለልጁ የሚኖረውን ልዩ አተያየትና ተፈጥሮአዊ ትስስር የሚያመለክት በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 639 የሰፈረው ድንጋጌ ባለበት ተወስዷል፡፡

<u>አንቀጽ 53 አብሮ መኖር</u>

ተጋቢዎች አብረው እንዲኖሩ የሚገደዱ ከሆነ የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደሚፈጽሙ የሚታወቅ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 640 የተመከለተው ድንጋጌ ሊቀጥል እንደሚገባ ታምኖበት መጠነኛ የአገላለጽ ለውጥ በማድረግ ተወስዷል፡፡

<u>አንቀጽ 54 የመኖሪያ ሥፍራን ስለመወሰን</u>

ተጋቢዎች የመኖሪያ ሥፍራቸውን በጋራ መወሰን የሚገባቸው በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 641 የሰፈረው ድንጋጌ ይህንኑ የእኩልነት መብት በሚያንፀባርቅ ሁኔታ ማሻሻያ ተደርጐበታል፡፡

ተጋቢዎች በጋራ መወሰን የማይችሉበት ሁኔታ ሲያጋጥም ችግሩ በክርክር ወይም በፍትሕ መድረክ እንዲወገድ ማድረግ በመካከላቸው ይበልጥ አለመተማመን እንዲሁም መራራቅን የሚፈጥር ሁኔታ በመሆኑ በንዑስ ቁጥር /2/ በቤተዘመድ ሽምግልና ጉባኤ እንዲታይ ማድረግም ሆነ በፍ/ቤት ታይቶ ውሳኔ እንዲሰጥ ማድረግ አግባብነት እንደሌለው ታምኖበት ይህንኑ የሚመለከተው ክፍል እንዲወጣ ተደርጓል፡፡ ይህም ሆኖ ተጋቢዎች ስለመኖሪያ ስፍራቸው ካልተስማሙ ምን መደረግ አለበት? የሚለው ጥያቄ እንዳለ የሚቀጥል ነው፡፡

<u>አንቀጽ 55 በስምምነት ተለያይቶ ስለመኖር</u>

የዚህ ድንጋጌ ርዕስ አብሮ ስለመኖር በተመለከተው ድንጋጌ የተቀመጠውን አጠቃላይ መርህ በቀጥታ የማይከተል በመሆኑ 'በስምምነት ተለይቶ ስለመኖር' በሚል ርዕስ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 642 ድንጋጌ እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡

<u>አንቀጽ 56 የመተማመን ግዴታ</u>

ይህ ድንጋጌ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 643 የተመለከተው ሲሆን ተጋቢዎች በመካከላቸው የሚጠበቅባቸውን የመከባበርም ሆነ የመደጋገፍ ግንኙነት ሊመሰርቱ የሚችሉት የመተማመን ሁኔታ በሚኖርበት ጊዜ እንደሆነ የሚታመን በመሆኑ ድንጋጌው ባለበት እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡

የሞያ ሥራን በተመለከተ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 645/4/ የሰፈረው ድንጋጌ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 41/2/ የተረጋገጠ የማንኛውም ዜጋ መብት በመሆኑ፣ በንዑስ ቁጥር /2/ የሞያ ሥራን ለመቃወም የተመለከተው ሁኔታ የሕገ መንግስቱን ድንጋጌ የሚፃረር በመሆኑ እንዲካተት አልተደረገም፡፡ ይህ አመለካከት የተወሰነ ሞያን ወይም ሥራን ለመቃወም እንዲቻል በንግድ ሕጉ የተመለከተውን መብት የማይነካ መሆኑ ታመኖበታል፡፡

ተጋቢዎች መተባበር፣ መከባበር፣ መደጋገፍ እንደሚኖርባቸው የሰፈረው ድንጋጌ የቤት አያያዝንም ሆነ ሌሎች አስፈላጊ ሁኔታዎችን በሥሩ የሚያጠቃልል በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 647 የሰፈረው ድንጋጌ እንዲካተት አልተደረገም፡፡

www.abyssinialaw.com

## ክፍል 3

## ጋብቻ በንብረት በኩል ስለሚኖረው ውጤት

ይህ ክፍል በፍ/ብሔር ሕጉ ከቁጥር 647-661 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች የሚመለከት ሲሆን ጋብቻው በገንዘብ በኩል የሚኖረውን ውጤት ያጠቃልላል፡፡

'ገንዘብ' የሚለው ቃል ጠበብ ያለ ትርጉም የሚሰጥ በመሆኑና ከገንዘብ ውጭ ያሉትን ሀብቶችና በቀጥታ በገንዘብ ተሰልተው ሊታወቁ የማይችሉ ንብረቶችን የማያጠቃልል በመሆኑ 'ንብረት' በሚለው ቃል እንዲተካ ተደርጓል፡፡

ተጋቢዎች የንብረታቸውን ጉዳይ ለመወሰን የጋብቻ ውል ሳያደርጉ የሚቀሩ ቢሆን የቤተሰብ ሕጉ ሕጋዊ አስተዳደር /Legal regime/ ሊኖረው የሚገባ በመሆኑ በዚህ ክፍል ሥር የተመለከቱት ድንጋጌዎች ለየትኛውም የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

ተጋቢዎች ከጋብቻ በፊት የነበራቸውን የግል ንብረት የጋራ ሀብት አንዲሆን መደንገጉ ጋብቻን ከንብረት ጋር የማየት ሁኔታና አስተሳሰብ የሚፈጥር ሲሆን በውጤቱም ጋብቻ ሀብት ለመካፈል የሚፈፀምበትና የሚፈርስበት ዕድል ይከፍታል፡፡ ምንም ያልነበረው ተጋቢ ንብረት ያለውን ሰው በማግባት ጋብቻው ሲፈርስ የሚካፈልበትን ሁኔታ በሕጋዊ አስተዳደር ሥር ማስቀመጡ በሕሊናም ሆነ በፍትሕ ረገድ ተቀባይነት የሚኖረው አይደለም፡፡

በዚህም ምክንያት የፍ/ብሔር ሕጉን ድንጋጌ በመከተል የተጋቢዎች የጋራ ሀብት የባልና ሚስቱ ደመወዝና ገቢ ሊሆን ይገባል፡፡ ተጋቢዎች ጋብቻውን በሚፈጽሙበት ጊዜ ለየግላቸው ያሏቸውን ንብረቶች ወይንም በየግላቸው በስጦታ ወይንም በውርስ ያገኟቸው ንብረቶች የግል ንብረቶች ሆነው እንዲቀጥሉ ተደርጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 34 የተረጋገጠውን የንብረት ባለቤትነት መብት የሚያስጠብቅ ነው፡፡ ሆኖም ተጋቢዎች ጋብቻውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በከፊል ከግል ሀብት ክፍያ በመፈፀም የገዟቸውና ቀሪው ክፍያ ከጋብቻው በኃላ ተፈጽሞ በእጃቸው የገቡ ሀብቶች ሊኖሩ የሚችሉበት አጋጣሚ እንደሚኖር ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ እንዲህ ዓይነት ሁኔታዎችን መፍትሔ ለመስጠት ሌሎች ሀገሮች የሚጠቀሙበትን ዘዴና ተሞክሮ መመልከቱ ጠቃሚነት እንደሚኖረው ታምኖበት ታይቷል፡፡

አንድ ንብረት የተገኘው የግል እና በተጨማሪም የጋራ ከሆነ ገንዘብ ወይንም ንብረት የሆነ እንደሆነ የጋራ የሆነው ንብረት መጠን የግል ከሆነው አንፃር ታይቶ በጣም ትንሽ ከሆነ ንብረቱ እንደግል ንብረት በሚቆጠርበት ጊዜ ሌላኛው ተጋቢ ለዚሁ ንብረት ከተዋጣው የጋራ ንብረት ዋጋ /መጠን/ አንድ ሁለተኛው እንዲከፈለው የሚፈቀድበት ሁኔታ በመኖሩ ይኸው አሰተሳሰብ በሀገራችን ተፈፃማነት ሊኖረው እንደሚገባ ግንዛቤ ተወስዷል፡፡

የባልና የሚስትን የግል ሀብት በተመለከተ በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 647 እና 648 ሥር በሰፈሩት ድንጋጌዎች 'ያለ ገንዘብ' እና 'በገንዘብ' የተገኙ ሀብቶች በሚል ተከፍሏል፡፡ ይኸው አገላለጽ ጠበብ ያለ ትርጉም የሚያስከትል ሆኖ በመገኘቱ የፍ/ብሔር ሕጉን እንግሊዘኛ ቅጂ በማዛመድ 'ገንዘብ' የሚለው ቃል "onerous" የሚለው ትርጉም እንደተሰጠው በእንግሊዘኛው ቅጂ "onerous" የሚለው ቃል የሚሸፍነው ገንዘብን ብቻ

www.abyssinialaw.com

እንዳልሆነ በልውውጥ ወይም በጉልበት ዋጋ መልክ የተገኙትንም እንደሚያጠቃልል ለቃሉ ከተሰጠው ትርጓሜ ለመገንዘብ የተቻለ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 647 የሰፈረው ርዕስ 'ያለግብይት የተገኙ ሀብቶች' በሚል አገላለጽ እንዲተካ የተደረገ ሲሆን ድንጋጌው በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ ለውጥ የማያስፈልገው በመሆኑ በአንቀጽ 57 እንዲካተት ተደርጓል፡፡

በአንቀጽ 648 የነበረው ርዕስ እንዲሁ ማሻሻያ ተደርጐበት 'በግብይት የተገኙ ሀብቶች' በሚል አገላለጽ በአንቀጽ 58 የሰፈረ ሲሆን ድንጋጌውን የበለጠ ግልጽ ለማድረግ የአገላለጽ ለውጥ ተደርጎበታል፡፡

በሌላ በኩል ከጋብቻ በኃላ በግብይት የተገኙ ንብረቶችን የግል ሆነው እንዲቀጥሉ ለማድረግ የቤተዘመድ ሽምግልና እንዲያፀድቀው የሚጠይቀው የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 648 ንዑስ ቁጥር /2/ ድንጋጌ በቤተሰብ ሕጉ ተፈፃሚነት የሌለው በመሆኑና ይኸው ሥልጣን ለመበደኛ ፍ/ቤቶች የተላለፈ በመሆኑ በዚህ ሁኔታ ተሻሽሎ ተቀርጿል፡፡

በጋብቻ ጊዜ የተገዛ የግል ንብረት የግል ሆኖ እንደሚቀጥል ለመገመት የሚቻል ቢሆንም በፍ/ቤት እንዲፀድቅ ካልተደረገ የጋራ ሀብትንም ጭምር በግብይት የተገዛ የግል ንብረት ነው የሚል መከራከሪያ በማቅረብ የጋራ ሀብቱ ከኃላፊነት የሚያመልጥበትና ሶስተኛ ወገኖችን የሚጐዳ ሁኔታ ሊፈጥር እንደሚችል ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በመሆኑም በግብይት የተገኘ የግል ሀብት ፍ/ቤት ቀርቦ መጽደቅ እንደሚኖርበት በአንቀጽ 58 ንዑስ ቁጥር 2 አሰገዳጅ ድንጋጌ እንዲኖር ተደርጓል፡፡

<u>አንቀጽ 59 የግል ሀብትን ስለመስተዳደር 1. መሠረቱ</u>

ይህ ድንጋጌ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 649 የተመለከተ ሲሆን አንደኛው ተጋቢ የግል ሀብቱን ገቢ ራሱ ሊያዝበት እንደሚገባ የተገለፀ ሲሆን የባልና ሚስት ገቢዎች የጋራ ሀብቶች እንደሚሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 652/1/ ሥር ከተመለከተው ድንጋጌ ጋር የሚጣጣም ባለመሆኑ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡

በዚህም መሠረት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 649/2/ አንደኛው ተጋቢ ሊያዝበት የሚችለው በንብረቱ ላይ እንጂ በገቢው ላይ እንዳልሆነ በሚገልጽ መልኩ በእንግሊዝኛው ቅጂ በተመለከተው አኳኃን ተስተካክሏል፡፡

<u>አንቀጽ 60 የግል ሀብት አስተዳደርን በጋብቻ ውል ስለመወሰን</u>

ይህ ድንጋጌ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 650 የተመለከተው ሲሆን በርዕሱ የሰፈረው 'የጋብቻ ውል' የሚለው አገላለጽ በድንጋጌው ውስጥ የሰፈረውን ዝርዝር ሁኔታ በቀጥታ የሚያንፀባርቅ አይደለም፡፡
እያንዳንዱ ተጋቢ የግል ንብረቱን ማስተዳደር እንደሚችል ከላይ በአንቀጽ 59 የተመለከተ ቢሆንም በጋብቻ ውላቸው አንደኛው ተጋቢ እንዲያስተዳድር ወይም እንዲያዝበት መወሰን እንደሚችሉ በግልጽ በሚያመለክት አገላለጽ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡

<u>አንቀጽ 61 ስለውክልና ሥልጣን</u>

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 651 የእንደራሴነት ስልጣን አንደኛው ለሌላኛው ለመስጠት በተጋቢዎች መካከል ያለውን ነፃነት የሚያመለክት ሲሆን በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ ለውጥ

www.abyssinialaw.com

የሚያስፈልገው ባለመሆኑ የውክልና ሥልጠን በሚል ማሻሻያ ታክሎበት ድንጋጌው እንዲቀጥል ተደርጓል።

አንቀጽ 62 የባልና የሚስት የጋራ ሀብት

ጋብቻ መንፈሳዊ፣ አካላዊና የንብረት ውህደት ሊፈጥር የሚችል ግንኙነት እንደመሆኑ መጠን ተጋቢዎች ስለግል ግንኙነታቸውም ሆነ ስለንብረታቸው በጋብቻ ውል መስማማት እንዲችሉ ተደርጓል።

ይህንኑ ግንኙነታቸውን ለመወሰን የተደረገ ውል ከሌለ እንዲህ ዓይነት መሠረታዊ ጉዳዮች በሕጋዊ አስተዳደሩ /Legal regime/ ሥር ተወስነው መቀመጥ ይኖርባቸዋል።

የተጋቢዎች የጋራ ሀብቶች የባልና የሚስት ደመወዝና ገቢዎች እንደሆኑ የፍ/ብሔር ሕግ ቁጥር 652 ይደነግጋል ባልና ሚስት በቅጥርም ሆነ አገልግሎት በመስጠት የሚያገኙት ገቢ የጋራ ሀብት /ንብረት/ ሆኖ ይቆጠራል በመሆኑም 'ገቢ' የሚለው ደመወዝን ጨምሮ ሌሎችንም የሚያጠቃልል ገላጭ ቃል በመሆኑ ይህንኑ የሚዘረዝር ማሻሻያ በማድረግ ድንጋጌው እንዲቀጥል ተደርጓል።

ከግል ንብረት የሚገኙ ገቢዎች የተጋቢዎች የጋራ ሀብት ስለመሆናቸው በግልጽ ተመልክቷል ተጋቢዎች ከግል ንብረታቸው በሚገኝ ገቢ ላይ እንዳያዝዙ የተደረገበት ምክንያት ይህንኑ መነሻ በማደረግ ነው።

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 652/2/ የሰፈረው ድንጋጌ የግል ንብረትን ለመወሰን በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 58/2/ በተደነገገው አኳኃን በግብይነት የተገኘ የግል ሀብት በፍርድ ቤት አስካልፀደቀ ድረስ የጋራ ሀብት እንደሆነ የሚገመት መሆኑን እንዲገልጽ ሆኖ እንዲቀጥል ተደርጓል። በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ የሰፈረው ሁኔታ ለተጋቢዎች በስጦታ ወይም በኑዛዜ የተሰጠውን ንብረት ለአንደኛው ተጋቢ የተሰጠ ስለመሆኑ በግልጽ ካልተመለከተ በቀር የጋራ ሀብት መሆኑን እንዲያመለክት ተደርጓል።

አንቀጽ 63 የሕግ ግምት

ይህ ድንጋጌ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 653 የተመለከተው ሲሆን ከጋብቻ በኃላም ይሁን በፊት ያለ ወይም የነበረ ንብረት የግል መሆኑ በሚገባ የማይረጋገጥበት ሁኔታ ሲኖር በሕግ ረገድ የጋራ እንደሆነ ይገመታል። ከጋብቻ በኃላ በአንደኛው ተጋቢ ስም በመሆኑ ብቻ የግል ንብረት ነው የሚል መከራከሪያ ሊቀርብ እንደማይችል ያመለክታል በመሆኑም የሕሊና ግምት የሚለው አገላለጽ ይህንኑ ሁኔታ የማይወክል በመሆኑ የሕግ ግምት በሚል ማሻሻያ ድንጋጌው እንዲቀጥል ተደርጓል።

አንቀጽ 64 ስለባልና ሚስት ገቢ መደበኛ አስተዳደር

ይህ ድንጋጌ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 654 የተመለከተው ሲሆን በእንግሊዘኛ ቅጂ "Normal management" በሚል የሰፈረው 'መደበኛ' የገቢ አስተዳደር የሚል ትርጉም ይኖረዋል በዚሁ ድንጋጌ ሥር የሰፈረው ሁኔታ የገቢ አስተዳደርን የሚመለከት በመሆኑ ቃሉ አግባብነት እንደሚኖረው ታምኖበት እንዲወሰድ ተደርጓል።

ገቢ የሚለው ቃል ደመወዝንም የሚያጠቃልል በመሆኑ፣ የባንክ ሂሣብ በግልም በጋራም ሊወጣ የሚችል በመሆኑ በዚህ ረገድ መጠነኛ ማሻሻያ በማድረግ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 654 የጽንሰ ሀሳብ ለውጥ ሳያስፈልገው ተወስዷል።

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ 65 ልዩ ሁኔታ

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 655 የሰፈረው ደንጋጌ ከላይ በአንቀጽ 64 የተመለከተውና አንደኛው ተጋቢ ገቢውን ራሱ እንዲቀበል የሚፈቅደው አጠቃላይ ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ አንደኛው ወገን ሌላኛው እንዲቀበል የሚሰጠው ፈቃድና በፍ/ቤት ውሳኔ መሠረት በልዩ ሁኔታ ሌላኛው ተጋቢ እንዲቀበል ማድረግ የሚቻል በመሆኑ 'የባልና የሚስት መብት' የሚለው ርዕስ አግባብነት የሌለው አገላለጽ በመሆኑ እንዲሁም የቤተዘመድ ሽማግሌ ሥልጣን በፍ/ቤት የተተካ በመሆኑ በዚህ ረገድ ማሻሻያ ተደርጐበት ድንጋጌው እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡

አንቀጽ 66 የጋራ ሀብትን ስለማስተዳደር

የጋራ ሀብትን፣ አስተዳደር በተመለከተ ተጋቢዎች በጋብቻ ውል ወይም በውክልና በሚያደርጉት የተለዩ ስምምነቶች መሠረት ለአንደኛው ተጋቢ የሚሰጥበት ሁኔታ ከሌለ የተጋቢዎችን የጋራ ሀብት የሚያስተዳድሩት ሁለቱም በአንድነት ይሆናል፡፡

በዚህ ረገድ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 656/1/ የሰፈረው ድንጋጌ የተጋቢዎችን የእኩልነት መብት የሚቃረን ሲሆን በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት 34 ድንጋጌ ጋር የማይጣጣም በመሆኑ የጽንሰ ሀሳብ ለውጥ ተደርጐበታል፡፡

ተጋቢዎች የጋራ ሀብታቸውን በጋራ ሊያስተዳድሩ እንደሚገባ የሚያረጋግጥ ድንጋጌ እንዲሰፍር ሲደረግ በአንፃሩ በጋራ ማስተዳደር የማያስችሉ ምክንያቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ታምኖበታል አንደኛው ወገን ችሎታ የለውም የሚል ውሳኔ ሲተላለፍ ወይም ንብረት የማስተዳደር መብቱን ሲገፈፍ ወይም በሌላ ምክንያት የጋራ ሀብታቸውን ለማስተዳደር የማያስችል ሁኔታ ሲያጋጥም ሌላኛው ተጋቢ የማስተዳደሩን ተግባር እንዲያከናውን ሊፈቀድ የሚገባ በመሆኑ ይኸው ድንጋጌ እንዲሰፍር ተደርጓል፡፡ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 656/3/ የሰፈረው ሁኔታ ከላይ በተቀረፀው ድንጋጌ እንዲተካ በመደረጉ ተሰርዟል፡፡

አንቀጽ 67 የማስታወቅ ግዴታ

አንደኛው ተጋቢ የጋራ ሀብታቸውን እንዲያስተዳድር በሚደረግበት ጊዜ ስለንብረቱ አስተዳደር ለሌላኛው ወገን በየጊዜው እንዲያስታውቅ ማድረጉ ሥልጣኑን በአግባቡ እየተወጣ መሆኑንና ያለመሆኑን ለመፈተሽም ሆነ ለማረጋገጥ የሚረዳ በመሆኑ ይኸው ድንጋጌ እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡

አንቀጽ 68 የጋራ ንብረትን ለሌላ ለማስተላለፍ የባልና ሚስት ስምምነት አስፈላጊ ስለመሆኑ

የተጋቢዎችንና የቤተሰቡን ደህነትና ጥቅም ከማስጠበቅ አንፃር በጋራ አስተዳደር ሥር የሚገኘውን ንብረት ለሶስተኛ ወገን አሳልፎ ለመስጠት፣ በዕዳና በዋስትና ለማስያዝ ለማበደርና የመሳሰሉትን ጉዳዮች ለማከናወን የባልና የሚስቱን የጋራ ፈቃድ ማግኘት እንደሚገባ የፍ/ብ/ሕጉ ቁጥር 658 ይደነግጋል፡፡

በሌላ በኩል የቤተሰቡን ዕለት ተዕለት ኑሮ ለመሸፈን ባልም ሆነ ሚስት ለኑሮ አስፈላጊ ነገሮችን ለማሟላት የሚያከናውኗቸው ጥቃቅን ግዥዎችና ተመሣሣይ ክንውኖችን ለመፈፀም አንዱ የሌላኛውን ፈቃድ መጠየቁ አስፈላጊነት አይኖረውም።

በመሆኑም የጋራ ፈቃድ ሊያስፈልጉ የሚገባቸው ጉዳዩች ተጨማሪ ማሻሻያ ተደርጐባቸው እንዲካተቱ ተደርጓል። በዚህም መሠረት የጋራ የሆነውን ንብረት ለመሸጥ የተጋቢዎች የጋራ ፈቃድ ያስፈልጋል። ከዚሁ ንብረት ጋር በተያያዘ ከሽያጭ በተጨማሪ ሌሎች ክንውንኖች ሊደረጉ እንደሚችሉ በመገንዘብ ለመለወጥ፣ ለማከራየት፣ በመያዥ ወይም በዋስትና ለመስጠት አንዱ የሌላኛውን ፈቃድ ማግኘት እንዳለበት የተመለከተ ሲሆን ለጊዜው ሊጠቀሱ የማይችሉ ክንውኖች ሊኖሩ በመቻላቸው ሌሎች ሰዎች መብት እንዲኖራቸው ለማድረግ ፈቃድ የሚያስፈልግ መሆኑን በሚገልጽ መልኩ እንዲሰፍር ተደርጓል። ዋጋው ከብር 500 በላይ የሆነውን የጋራ ንብረት ወይም የገንዘብ ሰነድ ለመሸጥ ከመቶ ብር በላይ የሆነ ግምት ያለውን ንብረት በስጦታ ለማስተላለፍ ፈቃድ የሚጠይቀው ድንጋጌ ባለበት እንድቀጥል የተደረገ ሲሆን ለማበደር ወይም ለመበደር ወይም ለሌላ ሰው ዕዳ ዋስ ለመሆን የጋራ ፈቃድ የሚጠይቀው የገንዘብ መጠን ከብር 100 ወደ 500 ከፍ እንዲል ተደርጓል።

<u>አንቀጽ 69 የስምምነት አለመኖር ስለሚያስከትለው ውጤት</u>

የተጋቢዎች የጋራ ስምምነት እንዲኖር የሰፈረውን ድንጋጌ በመተላለፍ አንደኛው ወገን የሚያደርጋቸው ተግባራት የሚያስከትሉት ውጤት ምን እንደሆነ ባለመቀመጡ ተፈፃሚነቱ ሲያከራክር ቆይቶል። በመሆኑም ከላይ በአንቀጽ 68 የተመለከተውን ድንጋጌ የተሟላ ለማድረግ እንዲቻል የጋራ ስምምነት ሳይኖር የተገቡ ግዴታዎች በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ፈራሽ ሊሆኑ የሚችሉ መሆናቸውን የሚደነግግ አንቀጽ እንዲኖር ተደርጓል።

<u>አንቀጽ 70 የባልና ሚስት ዕዳ</u>

ከባል ወይም ከሚስት ከአንደኛው ወገን የሚጠየቅ ዕዳ ከግል ወይም ከጋራ ንብረቱ ሊጠየቅ እንደሚችል የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 659 ይደነግጋል። ይህ ድንጋጌ በአፈፃፀም ረገድ ችግር ሲያስከትል ቆይቷል። በዕዳ አጠያየቅ ረገድ በአማራጭ የተቀመጠው ሁኔታ የግል ዕዳ በቀጥታ ከጋራ ንብረት እንዲከፈል የሚገፋፋ በመሆኑ ማሻሻያ ተደርጐበታል።

ባልና ሚስት በጋብቻ ውስጥ በሚኖሩበት ጊዜ የጋራ ሀብታቸው ሊከፋፈል ወይም በድርሻ ተለይቶ ሊቀመጥ የሚገባ ባለመሆኑ የግል ዕዳ ከጋራ ሀብት የግል ድርሻ ሊጠ የቅ የሚችል አይደለም። የባል ወይም የሚስት የግል ዕዳ ከባለዕዳው የግል ንብረት መጠየቅና መከፈል ይኖርበታል። ባለዕዳው የግል ንብረት ከሌለው ወይም ዕዳውን ለመሸፈን የሚችል በቂ ንብረት በማይኖርበት ጊዜ ከተጋቢዎች የጋራ ንብረት ሊከፈል እንደሚገባ ታምኖበታል።

ጋብቻ በፍቺ የሚፈርስበት ሁኔታ ሲያጋጥመም ለግል ዕዳ ከጋራ ሀብት የተከፈለ መጠን የሌላኛው ወገን ድርሻ እንዲከፈለው ካሣ መጠየቅ የሚቻልበት ሁኔታ ይኖራል።

<u>አንቀጽ 71 ለትዳር ጥቅም እንደተደረገ የሚቆጠር ዕዳ</u>

ይህ ድንጋጌ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 660 የተመለከተው ሲሆን በቃላት አጠቃቀም ላይ ከተደረገው ለውጥ በስተቀር በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ ለውጥ ሳያስፈልገው እንዲካተት ተደርጓል።

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ 72 የትዳር ወጪዎችን ስለመሸፈን

ይህ አንቀጽ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 661 የተመለከተው ድንጋጌ ሲሆን መጠነኛ የአገላለጽ ለውጥ ከማድረግ በስተቀር ባለበት እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡

አንቀጽ 73 በተጋቢዎች መካከል ስለሚደረጉ ውሎች

ባልና ሚስት በጋብቻ በሚኖሩበት ጊዜ ስለግላዊም ሆነ ንብረት ግንኙነታቸው ስምምነት ማድረግ የሚችሉበት ድንጋጌ የተካተተ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 633/1/ ሥር የጋብቻ ውጤቶችን በተመለከተ በክፍል አንድ ሥር የተመለከተው ድንጋጌ በቤተሰብ ሕጉ በክፍል ሶስት ጋብቻ በንብረት በኩል ስለሚኖረው ውጤት በሚደነግገው ክፍል እንዲጠቃለል ተደርጓል፡፡

በመሆኑም በባልና ሚስት መካከል የሚደረጉ ውሎች በፍ/ቤት በኩል ካልፀደቁ ተፈፃሚነት እንደሌላቸው ማሻሻያ ታክሎበት በዚህ አንቀጽ ሥር ሰፍሯል፡፡

ምዕራፍ 4

ስለጋብቻ መፍረስ

ጋብቻ በተጋቢዎች ፈቃድና ፍላጎት የሚመሰረት ግንኙነት እንደመሆኑ ሁሉ በተመሣሣይ አካኃን ሊፈርስ የሚችል ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል በአንደኛው ተጋቢ ጠ ያቂነት የጋብቻ መፍረስ ጥያቄ ያለምክንያት ሊቀርብ ይችላል፡፡

የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓቶች የተለያዩ በመሆናቸው መፍረስም ሆነ ውጤታቸው ላይ የሚያስከትለው ልዩነት እንደሌለ በፍ/ብ/ሕጉ ምዕራፍ 6 አንቀጽ 662 ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡

ጋብቻ ከተጋቢዎቹ አንዱ ሲሞት፣ ወይም ለጋብቻ የተቀመጡ አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌዎች ሳይሟሉ በመቅረታቸው ወይም በመጣሳቸው ምክንያት ሊፈርስ የሚገባ መሆኑን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 663 ሥር በዝርዝር ሰፍሯል፡፡ ይኸው ሁኔታ ቀጣይነት ሊኖረው የሚገባ በመሆኑ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

ጋብቻ ከላይ ከተጠቀሱት ምክንያቶች ውጭ በፍቺ ምክንያት ሊፈርስ ይችላል፡፡ ፍቺ የሚጠየቅበትና የሚፈፀምባቸው ምክንያቶችና አፈፃፀም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር /665-682/ ባሉት ድንጋጌዎች በዝርዝር ተመልክቶአል፡፡ የፍትሐብሔር ሕጉ ለፍቺ ጥያቄ ምክንያት ሆነው የሚቀርቡትን ፍሬ ነገሮች ከባድና ሌሎች ምክንያቶች በሚል ለሁለት በመክፈል ደንግጐ እናገኘዋልን /ቁ 667/፡፡

ከባድ የፍቺ ምክንያቶች በአንደኛው ወገን ጥፋት ወይም ጥፋት ባልሆነ ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል በዝርዝር የተቀመጠ ሲሆን ከዚህ ውጭ በአንደኛው ተጋቢ ጠ ያቂነት ፍቺ የሚፈፀም ሲሆን በጥፋት ላይ የተመሰረቱ ከባድ ምክንያቶችም ሆነ ከባድ ባልሆነ ምክንያቶች የሚቀርቡ የፍቺ ጥያቄዎች የንብረት ቅጣት /በሀብት ድልድል ላይ ልዩነት/ የሚያስከትሉ ናቸው፡፡ በከባድ ምክንያት የሚፈፀሙ ፍቺዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊደረጉ የሚችሉበት ሥርዓት የተቀመጠ ቢሆንም በንብረት ተቀጪ ላለመሆን

www.abyssinialaw.com

ለተንዛዛ ረዥም ክርክር ምክንያት ሆኖ ቆይቷል፡፡ በዚህም ምክንያት በተጋቢዎች መካከል አላስፈላጊ ውጣውረድና መጉላላት ተስተውሏል፡፡

ጋብቻ ለተጋቢዎችም ሆነ ለልጆች/ለቤተሰቡ/ አጠቃላይ ደህንነትና ጥቅም ሲባል የሚጠበቅበትና በቀላሉ እንዳይፈርስ የሚደረግበት ሁኔታ መኖሩ በመርህ ደረጃ የሚታመንበት ጉዳይ ቢሆንም ሊፈርስ የሚችልን ጋብቻ በቅጣት ምክንያት መከልከሉ የሚያመጣው ፋይዳ እንደማይኖር በተጨባጭ ከታዩት ችግሮች መገንዘብ ተችሏል፡፡

በመሆኑም ፍቺን በከባድና በሌሎች ምክንያቶች ክፋፍሎ ማስቀመጥ ከሚያስገኘው ጥቅም ይልቅ የሚያስከትለው መጉላላትና ጉዳት የሚያመዝን በመሆኑ የጽንሰ ሐሳብ ለውጥ ማድረግ እንደሚገባ በቤተሰብ ሕጉ ዙሪያ ከተካሄዱ የአስተያየት ማሰባሰቢያ መድረኮችም ሆነ ከሌሎች ሀገሮች ተሞክሮ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል ጥያቄ በመቅረቡ ብቻ ፍቺ እንዲደረግ የሚፈቀድ ከሆነ ስሜታዊ በሆኑ አለመግባባቶች ወይም ሊወገዱ በሚችሉ ምክንያቶች ጋብቻ በቀላሉ እንዲፈርስ የሚያበረታታ ሊሆን የሚችል በመሆኑ ተጋቢዎች በጋብቻው ለመቀጠል የማያስችላቸው ሁኔታ መኖሩን በመረዳትና ለማረጋገጥ እንዲችሉ የማሰላሰያ/የመብረጃ ጊዜ /cooling period/ በመስጠት ሊፈርስ የተቃረበን ጋብቻ ማዳን ወይም ማስቀረት ይቻላል፡፡

ጋብቻ የሚፈፀመው በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃድ እንደሆነ ሁሉ ፍቺ እንደመብት ተቆጥሮ በተጋቢዎቹ ፈቃድ የሚፈፀመ መሆን ይኖርበታል፡፡ ተጋቢዎች ኑሮዋቸውን ለመቀጠል እና ሊታረቁ የማይችሉበት ሁኔታ ከተፈጠረ ጋብቻው በፍቺ ሲፈርስ በፍ/ብ/ሕጉ እንደነበረው በጥፋት ላይ የተመሠረተና ቅጣትን የሚያስከትል ውስብስብ ስርዓት መከተሉ ፍትሀዊ ባለመሆኑ የጋራ ሀብታቸውን በእኩል በመካፈል የሚለያዩበት መንገድ ሊኖር እንደማይገባ ታምኖበት ሕጉ በዚህ መልክ እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡

<u>አንቀጽ 74 በማናቸውም ዓይነት የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት የተቋቋሙ ጋብቻዎች እኩል ስለመሆናቸው</u>

ይህ ድንጋጌ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 662 የሰፈረ ሲሆን በርዕሱና በድንጋጌው መጠነኛ የቃላት ለውጥ በማድረግ በአዲሱ ሕግ እንዲካተት ተደርጎአል፡፡

<u>አንቀጽ 75 ጋብቻ ስለሚፈርስባቸው ምክንያቶች</u>

በአንደኛው ተጋቢ ላይ የመጥፋት ውሳኔ እንዲሰጥ አቤቱታ ቀርቦ መሞቱ በፍርድ ውሳኔ ሲተላለፍ የፍቺ ምክንያት እንደሚሆንና የፍቺ ውሳኔ በሕግ እንደሚደረግ በተጨማሪ በማስቀመጥ የፍ/ብ/ሕጉ ቁጥር 663 ድንጋጌ እንዳለ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

<u>አንቀጽ 76 ፍቺ ስለሚወሰንበት ሁኔታ</u>

www.abyssinialaw.com

በባልና በሚስት ስምምነት ፍቺ በፍርድ ቤት ውሳኔ ማድረግ እንደሚቻል እንዲሁም አንደኛው ወገን ለፍ/ቤት በሚያቀርበው ጥያቄ መነሻነትም ሊደረግ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 665 እና 666 የሰፈሩትን ድንጋጌዎች በማጠቃለል ከባድና ሌሎች በሚል የሰፈሩትንና ይህንኑ መሠረት የሚያደርጉ ወይም የሚያጣቅሱ እንዲወጡ የተደረገ ሲሆን በፍ/ብ/ሕጉ ያልነበሩ አዳዲስ ድንጋጌዎች እንዲኖሩ ተደርጓል፡፡

በሌላ በኩል ጋብቻ በፍቺ የሚፈርስበትን ምክንያት ከላይ በተቀመጠው አኳኃን እንዲደነገግ በመደረጉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 664 የተመለከተው አንደኛው ተጋቢ ሌላኛውን አልፈልግም ማለት የሚከለክለው ድንጋጌ አስፈላጊ ባለመሆኑ ተሰርዟል፡፡

## ክፍል 1

## በስምምነት ስለመፋታት

የፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 665/1/ የአማርኛና የእንግሊዘኛ ቅጂዎች በስምምነት መፋታትን በሚመከት ተቃራኒ ድንጋጌዎችን ያንፀባርቃሉ፡፡ የእንግሊዘኛው ቅጂ በስምምነት መፋታትን ሲከለክል የአማርኛው ቅጂ ደግሞ በሕጋዊ መንገድ እስከተፈፀመ ድረስ ፍቺ በስምምነት ለመፈፀም የሚቻል መሆኑን የሚደነግግ ይመስላል፡፡ ይሁን እንጂ ፍቺ በስምምነት የሚፈፀምበትን ሥርዓት ባለመዘርጋቱ ጉዳዩ አወዛጋቢ ሆኖ ቆይቷል፡፡

ስለዚህ የሌሎች አገሮችን በተለይም የፈረንሳይን ተሞክሮ በመውሰድ በቤተሰብ ሕጉ በክፍል 1 ከአንቀጽ /77-80/ ባሉት ድንጋጌዎች በስምምነት ለመፋታት የሚቀርብ ጥያቄ የሚታይበት የአፈፃፀም ሥርዓት በዝርዝር እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡

ፍቺ ለማድረግ የሚቀርብ ስምምነት በግብታዊ አስተሳሰብ እንዳይቀርብ ለመከላከል እንዲሁም በሚገባ የታሰበበት ስለመሆኑ ለመገንዘብ እንዲቻል ባልና ሚስት የፍቺ ስምምነታቸውን ከሚያስከትለው ውጤት ጋር በጽሁፍ እንዲቀርቡ፣ አዲስ ተጋቢዎች የሀሳብ ወይም የፀባይ ልዩነቶቻቸውን በሚገባ እስከሚተዋወቁ ድረስ የተወሰነ ጊዜ ሊያስፈልጋቸው እንደሚችል ስለሚታመን ከተጋቡ ስድስት ወር ያልሞላቸው ተጋቢዎች በስምምነት ለመፋታት ጥያቄ ማቅረብ የማይችሉ መሆናቸውን ሁለቱም ተጋቢዎች ጋብቻውን ለማቋረጥ መስማማታቸውን በይፋ ካሳወቁ ምክንያታቸው ምን እንደሆነ መጠየቁ ፋይዳ ስለማይኖረው የፍቺ ምክንያት እንዲገለጽ መገደድ የሌለባቸው መሆኑ በአንቀጽ 77 ሥር በዝርዝር እንዲመለከት ተደርጓል፡፡

የፍቺ ስምምነቱ የቀረበለት ፍ/ቤትም በበኩሉ በተጋቢዎች የቀረበውን የፍቺ ስምምነት ትክክለኛነት ለማረጋገጥና ምናልባት አመልካቾች ሀሳባቸውን የሚለውጡበት ሁኔታ መኖር ያለመኖሩን ለማጣራትና ለማረጋገጥ ባልና ሚስቱን ማነጋገር እንደሚገባ በጥያቄያቸው የሚገፋበት መሆንና አለመሆናቸውን የሚያስቡበት ጊዜ እንደሚያስፈልጋቸው በማመን የሶስት ወር የማሰቢያ ጊዜ እንደሚሰጣቸው በአንቀጽ 78 ተደንግጓል፡፡

የፍቺ ስምምነቱን ከማጽደቁ በፊት ፍ/ቤቱ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ የሚገባ መሆኑን ፍቺው የባልና የሚስቱ ትክክለኛ ፍላጐት ስለመሆኑ፣ ፍላጐታቸውን በራሳቸው ፈቃድ የተሰጡ ስለመሆኑ፣ የፍቺ ጥያቄው ከሕግና ከሞራል ጋር የማይቃረን ስለመሆኑ፣ የፍቺው ውጤትም የሁለቱንም ተጋቢዎች ጥቅምና የልጆቻቸውን ጥቅም

www.abyssinialaw.com

የሚያስጠብቅ ስለመሆኑ በማጣራትና በማረጋገጥ የሚያፀድቅ መሆኑና እንዲሁም በፍቺው ውጤት ጉድለት ያለበት መሆኑ ከታመነበት ፍ/ቤቱ ተገቢውን ማስተካከያ እንደሚያደርግ በአንቀጽ 80 ሥር ተመልክቷል፡፡

## ክፍል 2

## ጥያቄ በመቅረቡ ምክንያት ስለሚወሰን ፍቺ

ይህ ድንጋጌ በክፍል 1 በተመለከቱት ድንጋጌዎች አኳኃን የፍቺ ስምምነት እንዲፀድቅ ከሚቀርቡ ጥያቄዎች ውጭ በማናቸውም ምክንያት ተጋቢዎች ፍቺ እንዲደረግ ለፍ/ቤት የሚያቀርቡት ጥያቄ የሚታይበትን የአፈፃፀም ሥርዓት የሚያመለክት አዲስ ክፍል ሲሆን በሥሩ አራት አንቀጾችን /ከአንቀጽ 81-84/ ይዟል፡፡

በዚሁ ክፍል በአንቀጽ 81 መሠረት ኃብቻው በፍቺ እንዲፈርስ የሚቀርብ ጥያቄ በፍ/ቤት በኩል ብቻ የሚታይ መሆኑና ለጥያቄው ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ማቅረብ የማይገደዱ መሆናቸውንና አስፈላጊ መስሎ ከታያቸው መግለጽ እንደሚችሉ ተደንግጓል፡፡

የፍቺ ጥያቄ የቀረበለት ፍ/ቤት አለመግባባቱን በስምምነት በመፍታት የፍቺ ጥያቄውን ለማንሳት እንዲችሉ ለማግባባት ጥረት ማድረግ እንደሚኖርበት፣ ካልተሳካ ጉዳዩ በሽምግልና እንዲታይ ለማድረግ በእርቅ እንዲያልቅ ማመቻቸትና የሶስት ወር የማሰላሰያ ጊዜ እንዲያገኙ ማድረግ እንደሚኖርበት በአንቀጽ 82 ሥር የተመለከተ ሲሆን ይህ ከመሆኑ በፊት ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 674 ለቤተዘመድ ሽምግልና ዳኞች ተሰጥቶ በነበረው ሥልጣን አኳኃን የባልና ሚስቱንና የልጆቻቸውን አጠባበቅ መተዳደሪያና ንብረት አስተዳደር አኗኗር የሚመለከት ትዕዛዝ ባለመዘግየት መስጠት እንደሚኖርበት ይደነግጋል፡፡

የፍቺ ክርክር በአጭር ጊዜ ታይቶ ውሳኔ የሚያገኝ ባለመሆኑና በአንድ ላይ ለመኖር የማያስችል ሁኔታ ሊኖር የሚችል በመሆኑ በአብዛኛው ሴቶች ሕፃናትን በመያዝ ከመኖሪያ ቤታቸው የሚፈናቀሉበት ሁኔታ የሚስተዋል በመሆኑ ይህንኑ ችግር ለመከላከል እንዲቻል በአንቀጽ 82/6/ ሥር አዲስ ድንጋጌ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

ፍ/ቤቱ ስለተጋቢዎች አኗኗር ትዕዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ የልጆቻቸውን ጥቅም የሚያስጠብቅና የጋራ መኖርያ ለቆ ቢወጣ ጉዳት የሚደርስበት ወገን የትኛው መሆኑን ማመዛዘን እንደሚኖርበት ተመልክቷል፡፡

የእርቅ ጥረቱ ውጤት ባለማስገኘቱ ምክንያት አማራጮችን መጠቀም የፍቺውን ውጤት የሚወስን መሆኑን እንደአስፈላጊነቱ ጉዳዩ በፍ/ቤት ወይም በሽምግሌዎች፣ ወይም በባለሞያዎች አማካይነት ታይቶ እንዲወሰን የሚደረግ መሆኑን፣ ከፍ/ቤት ውጭ ተወስኖ በሚመጣበት ጊዜ ተፈፃሚነት የሚያገኘው በፍ/ቤቱ በኩል ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ እንደሆነ በአንቀጽ 680 የሰፈረውን ድንጋጌ በማሻሻል ፍ/ቤቱ ከስድስት ወር ላልበለጠ ጊዜ ሊያዘገየው እንደሚችል ተመልክቷል፡፡

በቤተሰብ ሕጉ በአንቀጽ 84 አንደኛው ተጋቢ ለሌላኛው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ካሣ እንዲከፍል የሚደረግበት ድንጋጌ እንዲኖር ተደርጓል፡፡

www.abyssinialaw.com

ይህ ድንጋጌ የፍ/ብ/ሕጉ የፍቺ ምክንያቶችን መሠረት በማድረግ በሕጉ የተቀመጠውን ሥርዓትና አስተሳሰብ የተከተለ ሳይሆን ለትክክለኛው ፍትሕ ሲባል ፍ/ቤቱ አይቶ እንዲወስን ሥልጣን ተሰጥቶታል በድንጋጌው መሠረት ካሣ ሊከፈል የሚችለው አንደኛው ወገን በሌላኛው ላይ ያደረሰው በደል መኖሩ ሲረጋገጥ መሆኑን፣ የካሣውም መጠን በንብረት በማበላለጥ ወይም ፍቺ በመጠየቅ የሚወሰን ሳይሆን የፍቺ ውሳኔ ሲሰጥ ለደረሰው ጉዳት ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ እንደሆነ በዚህ ድንጋጌ በግልጽ እንዲሰፍር ተደርጓል፡፡

## ምዕራፍ 5

## የባልና ሚስቱን ሀብት ስለማጣራት

በዚህ ምዕራፍ ሥር ከአንቀጽ /85-93/ የተካተቱት ድንጋጌዎች ጋብቻ በሚፈርስበት ጊዜ የንብረት ክፍፍል ሥርዓቱ በምን ሁኔታ ሊከናወን እንደሚገባ የሚያመለክቱ ሲሆኑ በፍ/ብ/ሕጉ በክፍል 2 በተጋቢዎች መካከል ያለውን የገንዘብ ግንኙነት ጉዳይ ለማጣራት የተዘረዘሩትን ይመለከታል፡፡

በምዕራፍ 5 በአንቀጽ 85፣86፣87፣ 88 እና 90 የተመለከቱት ሁኔታዎች በፍ/ብ/ሕጉ ከቁጥር /683-689/ ያሉትን የንብረት ክፍፍል ሥርዓቶች ያጠቃልላል፡፡ ተጋቢዎች ስለንብረታቸው ግንኙነት ያደረጉት ውል ወይም ስምምነት ከሌለ በፍ/ብ/ሕጉ የሰፈሩት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት እንደሚኖራቸውና የንብረት ክፍፍል እንዴትና በምን ሁኔታ መፈፀም እንደሚኖርበት የሚያመለክቱ በመሆናቸው አስፈላጊ የሆኑ የአገላለጽ ለውጦችንና መጠነኛ ማሻሻያ በማድረግ እንዲወስድ ተደርጓል፡፡ አንደኛው ተጋቢ በንብረት አስተዳደር ከተሰጠው ስልጣን ውጪ በሚፈፅማቸው ድርጊቶች ምክንያት ካሣ የሚጠየቅበት የጊዜ ገደብ ተጐጂውን ወገን ለመጠበቅ ሲባል በፍ/ብ/ሕጉ ሥርዓት ከተቀመጠው ሶስት ዓመት ወደ አምስት ከፍ ብሏል፡፡

የተጋቢዎች የጋራ ሀብት አከፋፈል ሁኔታ በፍ/ብ/ሕጉ ስለውርስ አስተላለፍና አከፋፈል በተደነገገው አኳኋን ሊፈፀም የሚገባው መሆኑን የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 689 በጥቅሉ ያመለክታል፡፡

የቤተሰብ ሕግ ከፍ/ብሔር ሕጉ ተነጥሎ በሚወጣበት ጊዜ እንዲህ ዓይነት ድንጋጌዎች አስቀምጦ ማለፍ ለአፈፃፀም ምቹ ባለመሆኑ የንብረት አከፋፈልን በተመለከተ በውርስ ሕግ አግባብነት የሚኖራቸውን ድንጋጌዎች በዚህ ምዕራፍ ሥር እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

በአንቀጽ 89 የዕዳ ጠያቂዎችን መብት ስለማስከበር የሰፈረው ድንጋጌ በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 1081 የሰፈረውን የሚመለከት ሲሆን ለዕዳ ጠያቂዎች የተደረገው ጥበቃ በግልጽ ያልተመለከተ በመሆኑ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ክፍፍል ከመደረጉ በፊት በፍርድ የተረጋገጠ ወይም የታመነ ዕዳ አስቀድሞ ሊቀነስ የሚገባው መሆኑ በግልጽ ተሻሽሎ እንዲገባ ተደርጓል፡፡

በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 1086 መሠረት የንብረት ክፍፍል በዓይነት ሊፈፀም እንደሚገባ የሚያመለክተው ድንጋጌ አንቀጽ 91 ንዑስ ቁጥር /1/ እና /2/ ሆኖ እንዳለ ተወስዷል፡፡

www.abyssinialaw.com

በሌላ በኩል በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 91 ንዑስ ቁጥር /3/ የተካተተው ድንጋጌ በፍ/ብ/ሕጉ 1087/2/ የተመለከተው ነው፡፡

የንብረት ክፍፍሉን ለማድረግ አዳጋች ሆኖ ሲገኝ  ንብረቱ ተሸጦ ገንዘቡን እንዲከፋፈሉት የሚደረግ ስለመሆኑ በአንቀጽ 92 የሰፈረው ሁኔታ በፍ/ብ/ሕጉ ቁጥር 1092 እና 1093 ከሰፈሩት ድንጋጌዎች እንዲወስድ የተደረገ ነው፡፡

በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 93 የሰፈረው ድንጋጌ ከፍ/ብ/ሕጉ ከቁጥር 1087 የተወሰደ ቢሆንም ማሻሻያ ተደርጐበት የጋራ ሀብት ከተከፋፈለ በኃላ መከፈል የነበረበት ዕዳ በሚጠየቅበት ጊዜ ሁለቱም በየድርሻ መጠናቸው  ተጠያቂ  እንደሚሆኑ  በግልጽ እንዲሰፍር ተደርጓል፡፡

<u>ምዕራፍ 6</u>

<u>ጋብቻ ለመፈፀም ስለሚቀርብ ማስረጃ</u>

ቀደም ሲል በፍትሐብሔር ሕጉ አሠራር የጋብቻ ውል እና የጋብቻ ጽሁፍ የሚሉ ፅንሰ ሐሳቦች በፍርድ ቤቶች አካባቢ የሚምታቱበት አጋጣሚ እየተከሰተ ስለነበር ይህንኑ ለማስወገድ ይረዳ ዘንድ የጋብቻ ጽሁፍ የሚለው የጋብቻ ምስክር ወረቀት በሚል እንዲተካ በማድረግ ግልጽ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

በአዲሱ ሕግ የጋብቻ ምዝገባ እንደግዴታ የተጠቀመጠ በመሆኑ ጋብቻው በየትኛውም የማስፈፀሚያ ስርዓት ይከናወን ጋብቻ መፈፀሙ የሚረጋገጠው የጋብቻ ምስክር ወረቀት በማቅረብ እንደሆነ በአንቀጽ 84 ተገልጿል፡፡

ሆኖም የፈለገውን ያህል ጠንካራ የምዝገባ ሕግ ቢኖርም አንዳንዴ ምዝገባ የማይከናወንባቸው ልዩ ሁኔታዎች ሊያጋጥሙ ስለሚችሉና ምዝገባ የተከናወነ ቢሆንም ሰነዱ በመጥፋቱ፣ በመቃጠሉ ወይም በመቀደዱ ወይም በሌላ ማናቸውም ሁኔታ ማቅረብ የማይቻልበት ሁኔታ ሲያጋጥም የዜጐችን መብት ላለማጥበብ በማሰብ የትዳር ሁኔታን በማስረዳት ጋብቻ ለመፈፀሙ ማረጋገጥ እንደሚቻል ተመልክቷል፡፡ ቢሆንም ይህ ዓይነቱ ማስረጃ የዋናው መርህ ልዩ ሁኔታ በመሆኑ ጠበብ ብሎ ሊተረጐምና በሥራ ላይ ሊውል ይገባዋል፡፡ ካልሆነ ግን የምዝገባ ሥርዓቱን ሊሸረሽረውና ፋይዳ ሊያሳጣው ስለሚችል በአፈጻጸም ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

ጋብቻ የተፈፀመ ለመሆኑ ማስረዳት የሚቻለው የጋብቻ ምስክር ወረቀት በማቅረብ መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ሆኖም ሕጉ ተፈፃሚነት ከማግኘቱ በፊት የተደረጉ ጋብቻዎች በመሆናቸው ወይም በክብር መዝገብ ማቋቋሚያው አዋጅ ለሚነገሩ ምክንያቶች የምስክር ወረቀት ለማቅረብ የማይችሉ ሲሆኑ በሁኔታ መኖር ጋብቻ መኖሩን ለማስረዳት እንዲቻል ተደርጓል፡፡ እዚህ ላይ አሠራሩን ቀላል ለማድረግ እንዲቻል ተጋቢው ወገን የጋብቻ ሆኔታ መኖሩን ለፍርድ ቤቱ ጋብቻ ስለመኖር ግምት መውሰድ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ይህ ግምት ግን በተቃራኒው ወገን ሊፈርስ ይችላል፡፡ ሊያፈርሰው የሚችለው ግን የተባለው ጋብቻ አለመፈፀሙን  በማያጠራጥር ሁኔታ ለማስረዳት ሲችል ብቻ ነው፡፡ የዚህ ድንጋጌ ዓላማ ቀደም ሲል በፍርድ ቤቶች አካባቢ ሲከሰት የነበረውን ውዝግብ ለማስቀረት የታሰበ ከመሆኑም በላይ የምዝገባ ሥርዓት ከተቋቋመ በኃላ እርግጥ ጋብቻ አለ የለም የሚለውን በደንበኛው ሙግት /contentious proceedings/ እንዲኖር ማድረጉ የምዝገባውን ዓላማ ከሥሩ የሚንድ ስለሚሆን ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

በፍትሐብሔር ሕጉ መሠረት የትዳር ሁኔታ መኖሩ ያልተረጋገጠ እንደሆነ ስስተኛ የማስረጃ ዓይነት ማቅረብ እንደሚቻል ተገልጿል፡፡ ይኸውም ዳኞች ያፀደቁት ግልጽ ጽሁፍ /Acts of notority/ ነው፡፡ ሆኖም ይህ አሰራር እስካሁን ድረስ በተግባር ያልዋለ ከመሆኑም ባሻገር የክብር መዝገብ ሹም በስሩት የሚዋቀርበት ሁኔታ በአዲሱ ሕግ የተመለከተ በመሆኑ በፍርሐብሔር ሕጉ የተጠቀሰው ሶስተኛው የማስረጃ ዓይነት አስፈላጊ እንዳልሆነ ታምኖበታል በአዲሱ ሕግ እንዳኖር ተደርጓል፡፡

## ምዕራፍ 7

## ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር

ይህ ምዕራፍ በፍ/ብ/ሕጉ በምዕራፍ 8 ’ ከጋብቻ ውጭ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ስለመኖር አብሮ ’ በሚል ርዕስ ከቁጥር 708-720 ባሉት ድንጋጌዎች ተመልክቶ ይገኛል፡፡

የቤተሰብ ሕጉን የተሻሻለ ረቂቅ ለማዘጋጀት እንዲረዳ በማሰብ የሕብረተሰቡን አስተያየት ለማሰባሰብ በተዘጋጁ መድረኮች ላይ አከራካሪ ከነበሩት ጉዳዩች በዋነኛነት የሚጠቀስ ሲሆን ሁለት ጠንካራ አመለካከቶች ተንፀባርቀዋል፡፡

ከጋብቻ ውጭ የግብረ ሥጋ ግንኙነት አብሮ መኖር በሃይማኖት ተቀባይነት የሌለው ሕብረተሰቡ ለጋብቻ ያለውን ቀኖናዊ አስተሳሰብ ዝቅ የሚያደርግና ጤናማ ያልሆነ ቤተሰብ ምንጭ በመሆኑ፣ በውጤቱም ሕፃናትና ሴቶች ተጠቂ የሚሆኑበት ግንኙነት በመሆኑ፣ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት በግልጽ ዕውቅና ያልተሰጠው በመሆኑ ይኸው ሕገወጥ ድርጊት በቤተሰብ ሕጉ ሊካተት አይገባም የሚል አመለካከት በአንድ ወገን ቀርቧል፡፡

በሌላ በኩል ግንኙነቱ የፍ/ብ/ሕጉ ከመውጣቱ በፊት በመላ ሀገሪቱ በስፋት የነበረ በመሆኑ፣ በኢኮኖሚ ዝቅተኛነት ወይም በቤተሰብ ፈቃድ ጉድለት ወይም በአጋጣሚ በሚፈጥሩ ግንኙነቶች ወይም ጥሎሽና ሌሎች ባህላዊ ግዴታዎችን ለመወጣት ባለመቻልና ለጊዜው ሊጠቁሱ በማይችሉ በርካታ ምክንያቶች የጋብቻ ሥርዓቶች ሳይፈፀሙ በእንዲህ ዓይነት ግንኙነት የሚመሰረት በርካታ ትዳር አሁንም ድረስ መኖሩንና ወደፊትም ሊቀጥል እንደሚችል በሀገር ውስጥና በሌሎች ሀገሮች የተካሄዱ ጥናቶች የሚያስገነዝቡ በመሆናቸው ግንኙነቱን እውቅና ማሳጣትም ሆነ በቤተሰብ ሕጉ እንዳይካተት ማድረግ እውነታን ላለማየት አይን እንደመጨፈን ይህል እንደሆነ በጥናታዊ ጽሁፎች የተደገፈ የተጠናቀረ የሕዝብ አሰተያየት በመቅረቡ በፍ/ብ/ሕጉ እንዲካተት የተደረገው ይኸው ክፍል በቤተሰብ ሕጉ ቀጣይነት እንዲኖረው ተደርጓል፡፡

’ከጋብቻ ውጭ ከግብረ ሥጋ ግንኙነት አብሮ መኖር’ የሚለው ስያሜ ተስማሚ በሆነ አገላለጽ ማሻሻያ የሚያስፈልገው ሆኖ በመገኘቱ ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር በሚል ገላጭ ቋንቋ ተተክቷል፡፡

በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 708 የሰፈረው ትርጓሚ የትዳር ሁኔታን የሚያንፀባርቅ በመሆኑ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 98 በትዳር መልክ የተመሰረተ ግንኙነት መኖሩ መረጋገጥ እንዳለበት የሚል አገላለጽ እንዲጨመር ተደርጐ እንዲወሰድ ተደርጓል፡፡

www.abyssinialaw.com

በፍ/ብ/ሕጉ አንቀጽ 709 ማጠናቀቂያ በሚል የሰፈረው ርዕስ በድንጋጌው ውስጥ የተካተተውን ዝርዝር ሁኔታ የሚገልጽ ባለመሆኑና ለግንኙነቱ የተሰጠ ማብራሪያ በመሆኑ መጠነኛ የቃላት ለውጦች ተደርጐበት በዚህ መልክ ተሻሽሎ ተካትቷል፡፡

ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር የጋብቻ ዝምድና የማያስከትል ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕጉ አንቀጽ 710 የሰፈረው ድንጋጌ እንዳለ እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡

ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት በቤተሰብ ሕጉ በምን ሁኔታና ደረጃ እውቅና እንደሚኖረው ለመወሰን የሌሎች አገሮችን ልምድ፣ እንዲሁም በሀገር አቀፍ ደረጃ በቤተሰብ ሕግ ዙሪያ በተደረጉ አውደጥናቶች የተሰነዘሩ አስተያየቶች፣ እንዲሁም በፍ/ብሔር ሕጉ በሰፈረው አኳኃን የነበረው የአፈፃፀም ሁኔታ ታይቷል፡፡

በዚህም መሠረት በአንድ በኩል ግንኙነቱን ከጋብቻ የሚለየው ዓይነተኛው ባህርይ ጋብቻ ለመፈፀመ የሚጠየቁ የአፈፃፀም ሥርዓቶች የሚጠይቁትን ፎርማሊቲዎች አለማሟላት ሲሆን በሌላ በኩል በጋራ ጥረት ንብረት ማፍራት፣ ልጅ ወልዶ በጋራ ማሳደግ የመሳሰሉ በጋብቻ የሚፈጠሩ ውጤቶች በተመሣሣይ ሁኔታ ሊኖሩ እንደሚችሉ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በቤተሰብ ሕጉ በተመለከቱት የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓቶች መሠረት ጋብቻ ለሚፈጽሙ ተጋቢዎች የተደነገጉት ውጤቶች በእንዲህ ዓይነት ግንኙነት በትዳር ለሚኖሩ በቀጥታ ተፈፃሚነት እንዲኖራቸው ማድረግ በጋራ ጥረትና ድካም የተገኘውን ውጤት/ንብረት/ ሕጉ የጠየቀው ፎርማሊቲ ባለማሟላቱ ብቻ ሁለቱም በእኩል ደረጃ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ መከልከል ከፍትሕ አኳያ አግባብነት ሊኖረው እንደማይገባ ታምኖበታል፡፡

በዚህ ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በግንኙነቱ የተወሰነ ዓመታት ከኖሩ እንደተጋቡ ሰዎች እንዲቆጠሩ የሚያደርግ ሕግ ያላቸው ሃገሮች መኖራቸውን፣ በሌሎች ሀገሮች በእንዲህ ዓይነት ግንኙነት የተወሰነ ጊዜ ከኖሩ በዚህ ግንኙነት መኖር ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ የሚፈራው ንብረት የጋራ ንብረት እንደሚሆን የሚደነግግ ሕግ ያላቸው ሲሆን አንዳንድ አገሮች በግንኙነቱ ልጅ ከተወለደ ግንኙነቱ በቀጥታ ከጋብቻ እኩል እንዲታይ የሚያደርግ ሕግ ደንግገዋል፡፡ በጋብቻ ግንኙነቱ የተሳሰሩ ተጋቢዎች በትዳር ዘመን ያፈሩት ንብረት የጋራ እንዲሆን የሚደነገግበት ምክንያት ንብረቱን ለማፍራት ባልም ሆነ ሚስት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በገንዘብና በጉልበት በመሳሰሉት መንገዶች አስተወጽኦ ያደርጋሉ በሚል እምነት ስለሆነ ጋብቻ ሳይፈጽሙ የተወሰነ ጊዜ በትዳር መልክ አብረው የሚኖሩ ከሆነ በተመሣሣይ አኳኃን በግንኙነቱ ዘመን ላፈሩት ንብረት የጋራ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይገባል የሚለው አስተሳሰብ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

የጊዜውን ገደብ በተመለከተ የሌሎች አገሮችን ልምድ መነሻ በማድረግ 3፣5፣10 ዓመት የሚሉ አማራጮች ቀርበው በግንኙነቱ ለመቀጠልም ሆነ ላለመቀጠል፣ ንብረትም ሆነ ልጅ ለማፍራት ሦስት ዓመት ቢሆን የተሻለ እንደሚሆን ታምኖበት በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 102 አዲስ ድንጋጌ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

ግንኙነቱ በቤተሰብ ሕጉ የተቀመጠው የሦስት ዓመት ጊዜ ከመድረሱ በፊት የሚቋረጥም ቢሆን ንብረቱን እንዲወስድ ማድረግ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40 ስለንብረት መብት የሰፈረውን ድንጋጌ የሚተገብርና ከፍትሕ አንፃርም ሲታይ አግባብነት የሚኖረው በመሆኑ ይኸው ሁኔታ ሰፍሯል፡፡

www.abyssinialaw.com

በግንኙነቱ የጋራ ሀብት በሚፈጠርበት ጊዜ የሀብት አስተዳደሩን፣ ዕዳ አከፋፈልን፣ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር የሚኖርን ግንኙነት፣ ንብረት ማጣራትና የመሳሰሉት ጉዳዮች በጋብቻ ተሳስረው ለሚኖሩ ተጋቢዎች ተፈፃሚነት እንዲኖራቸው በቤተሰብ ሕጉ የሰፈሩት ድንጋጌዎች በዚህ መሰል ሁኔታ ለተፈጠረ ግንኙነትም ተፈፃሚ እንደሚሆኑ በአንቀጽ 103 እንዲሰፍር ተደርጓል፡፡

በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 714 እና 715 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ቀጣይነት ሊኖራቸው የሚገባ በመሆኑ አስፈላጊው ማሻሻያ ተደርጐባቸው በአንቀጽ 102 /4/ እና 104 ሥር እንዲካተት ሆኗል፡፡

ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት በማንኛውም ጊዜና ጠ ያቂ ሊቋረጥ የሚችል በመሆኑ፣ ጋብቻ ሲፈርስ ተጋቢዎች እንዲከተሏቸው በሕግ የሰፈሩት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት እንዲኖራቸው የሚያስገድድ ሁኔታና ምክንያት ባለመኖሩ ግንኙነቱ እንዲቋረጥ ያደረገውን ወገን ለፈፀመው ጥፋት በደል ለደረሰበት ወገን ካሣ ሊከፍል እንደሚገባ በግልጽ በማመልከት በፍ/ብ ሕጉ በቁጥር 716 እና 717 የግንኙነቱን መቋረጥ በተመለከቱ የሰፈሩት ሁኔታዎች በአንቀጽ 105 ሥር እንዲካተት ተደርጓል፡፡

በሌላ በኩል በሚሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ከተወሰነ ጊዜ በኃላ የጋራ ሀብት የሚፈጠ ርበት ሁኔታ ስለሚኖርና በግንኙነቱ ጊዜ የግል ሀብት ካላቸውም ግንኙነቱ ሲቋረጥ መውሰድ የሚችሉ በመሆናቸው የጋራ ሀብት ከተፈጠረ በኃላ ቢቋረጥ ድርሻ ስለሚኖራቸው፣ በዚህ መልኩ ከጋብቻ ጋር ተመሳሳይ ውጤት ስላለው ግንኙነቱ ከተቋረጠ በኃላ ጋብቻ ሲፈርስ እንደሚደረገው ቀለብ የመቁረጥ ድንጋጌ ማስቀመጡ ለጋብቻ የተሰጠውን ጥበቃና ትኩረት ዝቅ የሚያደርግ፣ በሁለቱ ግንኙነቶች መካከል ሊኖር የሚገባውን ልዩነት በእጅጉ የሚያጠብ በመሆኑ ግንኙነቱ ቀለብ የመቁረጥ መብትና ግዴታ ሊያስከትል እንደማይገባው ታምኖበታል፡፡

ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት በመኖር የተመሰረተ ግንኙነት ስለመኖሩ ለማስረዳት በፍ/ብ/ሕጉ አንቀጽ 718 እና 719 መሠረት የግንኙነቱን ሁኔታ መኖር በማስረዳት ማረጋገጥ የሚቻል ሲሆን የሁኔታውን መኖር ለማሳየት የሰፈረው ድንጋጌ ቀጣይነት ሊኖረው እንደሚገባ ታምኖበት በአንቀጽ 106 እንዲካተት የተደረገ ሲሆን የግንኙነቱን አለመኖር በተመለከተ በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 719/2/ የሰፈረውን ማሻሻያ በማደረግ ማናቸውም ዓይነት አሳማኝ ማስረጃ በማቅረብ በማስረዳት ማፍረስ እንደሚቻል በሚገልጽ ሁኔታ በአዲሱ ሕግ እንደካተት ተደርጓል፡፡

ጋብቻ ሳይፈፀም የሚደረጉ ሌሎች ግንኙነቶችን በተመለከተ በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 712 የሰፈረው ድንጋጌ መጠነኛ የአገላለጽ ለውጥ ታክሎበት በቀጥታ እንዲወሰድ ተደርጓል፡፡

## ምዕራፍ 8

## በጋበቻ እና ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ በመኖር የሚነሱ ክርክሮች ስለመወሰን

www.abyssinialaw.com

ይህ ምዕራፍ በፍ/ብ/ሕጉ በምዕራፍ 9 ሥር የሰፈሩትን ድንጋጌዎች የሚመለከት ሲሆን በጋብቻም ሆነ እንደባልና ሚስት አብሮ በመኖር የሚነሱ ክርክሮች ምን እንደሆኑ፣ በማንና በምን ሁኔታ እንደሚታዩ ተመልክቷል በፍ/ብ/ሕጉ ከቁጥር 722-737 የሚገኙ ድንጋጌዎች ከፊሎች ሥነ ሥርዓት ነክ ሁኔታዎችን ሌሎች በጋብቻ ውስጥ የሚፈጠሩ ክርክሮች መፍትሄ የሚያገኙበትን ሥርዓት የሚመለኩቱ ናቸው፡፡

በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ መጠቃለል የሚገባቸው ሥነ ሥርዓት ነክ ጉዳዩችን በቤተሰብ ሕጉ እንዲካተቱ ማድረግ በመርህ ደረጃ የአፈፃፀምና የአተረጓጐም ችግር እንደሚያስከትል ለመገመት የሚቻል ቢሆንም የቤተሰብ ሕጉን በተሟላ ደረጃ በተግባር ላይ ለማዋል ቀለል ያሉና ግልጽ የሆኑ የማስፈፀሚያ ሥርዓቶች ሊኖሩ ስለሚገባ አስፈላጊ የሆኑ ተጨማሪ ድንጋጌዎች ታክለው በፍ/ብ/ሕጉ ሥነ ሥርዓት ነክ ድንጋጌዎች እንዲቀጥሉ ተደርጓል፡፡

በመሆኑም በዚህ ምዕራፍ የተካቱት ድንጋጌዎች በሁለት እንዲከፈሉ ተደርጓል፡፡ ከአንቀጽ 108-114 የተዘረዘሩት ድንጋጌዎች ከጋብቻ ጋር በተያያዙ የሚነሱ ሥነ ሥርዓት ነክ ጉዳዩች እንዴትና በየትኛው ሕግ መታየት እንደሚኖርባቸው፣ ክርክር በመታየት ላይ እያለ ትኩረት የሚሹ ጉዳዩች ምን እንደሆኑ የሚያመለክቱ ሲሆን ያጋጠሙ ተጨባጭ ችግሮችን መነሻ ያደረጉ ናቸው፡፡

<u>አንቀጽ 108</u> <u>ተፈፃሚነት ስለሚኖረው ሕግ</u>

ይህ ሕግ ለቤተሰብ ጉዳይ ተስማሚ የሆኑ የሥነ ሥርዓት ሕጐች ከሞላ ጐደል አካቶ የያዘ መሆኑ ቢታወቅም ለሁሉም ሥነ ሥርዓታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል ተብሎ አይገመትም ስለሆነም በዚህ ሕግ የተካተቱ የሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉም ተፈፃሚ እንደሚሆን ተደንርጓል፡፡

<u>አንቀጽ 109</u> <u>የባልና የሚስትን ሀብት ስለማጣራት የተደነገጉት ተፈፃሚ ስለመሆናቸው</u>

በአሁኑ ወቅት ጋብቻ በሞት በሚፈርስበት ጊዜ በፍርድ ቤት ከሚታዩት ችግሮች አንዱ የባልና ሚስት ንብረት ጉዳይ በሕጉ መሠረት ለቤተዘመድ ሽምግልና ዳኞች ቀርቦ መወሰን ሲገባው የአንደኛው ተጋቢ ወራሽ ውርስ ይጣራልኝ ወይም አንድ የተወሰነ ንብረት ለእኔ ይገባል የሚል ጥያቄ በማቅረብ የባልና የሚስት ንብረት ማጣራትን የሚመለከት ጉዳይ የውርስ ጉዳይ በሚመለከት ችሎት እንዲታይ እየተደረገ ነው፡፡ ይህ ክስተት የውርሱ ንብረት ከባልና ከሚስት ንብረት ተለይቶ ከመታወቁ በፊት የውርስ ክርክር በፍርድ ቤቶች በኩል እንዲካሄድ በማድረግ እንዳንድ ኢፍትሐዊ ውሳኔዎች እንዲሰጡና ፍርድ ቤቶችም ከስልጣናቸው ውጭ የሆኑ ጉዳዩችን እንዲያስተግናዱ ሲያደርጋቸው ቆይቷል፡፡ ይህንን ከሕጉ ያፈነገጠ የአሠራር ልምድ ለማስቀረት ግልጽ የሆነ ድንጋጌ መቅረጽ በማስፈለጉ አንቀጽ 109 በዚህ ምዕራፍ ሥር እንዲካተት ተደርጓል፡፡

www.abyssinialaw.com

በዚህም መሠረት ይህ አንቀጽ የባልና የሚስት ንብረትና የውርስ ጉዳይ ተለያይተው፣ በቅደም ተከተልና ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች እንዲታዩ ለማድረግ ታስቦ የተቀመጠ ነው፡፡

## አንቀጽ 101፣ 111 የባልና ሚስት ክርክር ስለሚታይበት ሁኔታና ስለውሳኔ አሰጣጥ

የባልና ሚስት ክርክሮችና ችግሮች በተወሰነ ደረጃ ግላዊ ግንኙነትን መሠረት በሚያደርጉ ጉዳዮች ዙሪያ የሚከሰቱ በመሆናቸው በመደበኛ የክርክር ሥርዓት በአደባባይ መታየታቸው የበለጠ መቃቃርን ጥላቻን የሚፈጥሩ በመሆናቸው፣ የተወሰኑ ጉዳዮችም በባህሪያቸው ጥንቃቄ የሚጠይቁና በተለየ ሁኔታ ሊታዩ የሚገባቸው በመሆኑ ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ጉዳዩን በዝግ ችሎት ለማየት እንዲችል በአንቀጽ 110 ሥልጣን ተሰጥቷል፡፡ የባልና ሚስት ጉዳዮች ጋብቻው ከፈረሰም በኃላ በሚስጥርነት መያዝ ያለባቸው ጉዳዮች ሚስጥርነታቸው እንደተጠበቀ እንዲቆይ ለማድረግ እንዲቻል ፍርድ ቤቱ እነዚህን መሰል ጉዳዮች በውሳኔው ውስጥ እንዲያካትት ለማድረግ በዚህ ሕግ አንቀጽ 111 ተደንግጓል፡፡

## አንቀጽ 112 ስለይግባኝ

የዚህ ሕግ አንቀጽ 112 ዓላማ ፍቺን አስመልክቶ የተሰጡትን ውሳኔዎችና ትእዛዞች ሕጋዊነት በሚመለከት የሚቀርቡ ይግባኞችን ለመከልከል ሳይሆን ፍቺ ሊወሰን አይገባም የሚለውን ነጥብ መሠረት በማድረግ ብቻ የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ እንደማይቻል ለማመልከት ነው፡፡ ከባልና ከሚስት አንዳቸው የፍቺ ጥያቄ እስካቀረቡ ድረስ ፍቺው ሊከለከል ስለማይችል ፍቺ ሊሰጥ አይገባውም በማለት የሚቀርብ ማናቸውም ይግባኝ የህጉን መንፈስና የተጋቢዎቹን የመፋታት መብት የሚፃረር ከመሆኑም በላይ ፍቺው የማይከለከል ሆኖ እያለ የይግባኝ ክርክር እንዲቀጥል ማድረጉ ፋይዳ የሌለውና መጉላላትን ብቻ የሚያስከትል ከመሆን አያልፍም ከሚል እምነት በመነሣት ነው ይህ አንቀጽ እንዲካተት የተደረገው፡፡

## አንቀጽ 113 ስለልጆች አጠባበቅና አያያዝ

ጋብቻ በሚፈርስበት ጊዜ የሕፃናት አጠባበቅና አያያዝን በተመለከተ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 681 እና 682 የቤተዘመድ ሽምግልና ጉባኤ ሊያደርግ ስለሚገባው ትኩረትና ጥንቃቄ የሰፈረው ድንጋጌ ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን ማድረግ የሚያስፈልግ ሲሆን ይኸው ሥልጣን ለፍ/ቤቶች የተላለፈ በመሆኑ በዚህ ምዕራፍ ሥር በአንቀጽ 113 ሥር ማሻሻያ ተደርጉበት እንዲካተት ተደርጓል፡፡

በልጆች አጠባበቅና አያያዝ ላይ ፍ/ቤቱ ይበልጥ ትኩረት ሊያደርግባቸው የሚገባ ጉዳዮች ትምህርት፣ የጤና አጠባበቅ ቀለብ እንዲሁም ወላጆችም ሆነ ልጆች ለመጠ ያያቅ ስለሚችሉበት ሁኔታ እንደሆነ በውሳኔ አሰጣጥ ረገድም የወላጆች የገቢ፣ የጤና፣ የዕድሜና የአኗኗር ሁኔታ የልጆች ዕድሜ ጥቅማቸውና ፍላጐታቸውን በማገባ ሊገናዘብ እንደሚገባ በቤተሰብ ሕጉ ተመልክቷል፡፡ ከላይ በዝርዝር የሰፈሩትን አስፈላጊ ሁኔታዎች ፍ/ቤቱ ከግምት ውስጥ እንዲያስገባ በመደረጉ ከአምስት ዓመት በታች ያላቸው ሕፃናት ከእናታቸው ጋር ብቻ እንዲቆዩ የሚያስገድደው የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 680/2/ ባለበት እንዲቀጥል ማድረግ አላስፈለገም፡፡

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ 114 ጋብቻ ሳይፀም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር

የጋብቻ ክርክርን ለመወሰን ተፈፃሚ ስለሚሆኑ አሰራሮች በተመለከተ በምዕራፍ 8 የሰፈሩትን ድንጋጌዎች እንደየአግባብነታቸው ጋብቻ ሳይፈፀም አንደባልና ሚስት አብረው በሚኖሩ ሰዎችም ላይ ተፈፃሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ በአንቀጽ 114 ሰፍሯል፡፡

በምዕራፍ 8 ሥር በክፍል 2 ከአንቀጽ /115-118/ የተመለከቱት ድንጋጌዎች በጋብቻና በሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ የሚነሱ ክርክሮችን ለማየት ሥልጣን ወይም አግባብነት የሚገኖረውን አካል ለመወሰን የተቀመጡ ናቸው፡፡

አንቀጽ 115፣ 116 የሚፀና ጋብቻ ስለመኖሩና እንደባልና ሚስት አብሮ በመኖር የሚነሳ ክርክር

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 724 የሚፀና ጋብቻ ስለመኖሩ፣ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 730 ከጋብቻ ውጭ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ስለመኖሩ ለማየትም ሆነ ለመወሰን ሥልጣን የተሰጠው ለፍ/ቤቶች እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ የሚነሱ ክርክሮች በፍ/ቤቶች ብቻ ሊታዩ የሚገባቸው በመሆናናቸው መጠነኛ የአገላለጽ ለውጦች በማድረግ በአንቀጽ 115 እና 116 እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

አንቀጽ 117 ስለፍቺና ውጤቶቹ

የፍቺን ክርክር ለመወሰን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 728 ለቤተዘመድ ሽምግልና ዳኞች የተሰጠው ሥልጣን በቤተሰብ ሕጉ ለፍ/ቤቶች እንዲተላለፍ በመደረጉ የፍቺም ሆነ ውጤቶቹን በተመለከተ የሚቀርቡ ጉዳዮች ታይተው ውሳኔ የሚያገኙት በፍ/ቤቶች ብቻ እንደሆነ በአንቀጽ 117 በግልጽ ተመልክቷል፡፡

አንቀጽ 118 በጋብቻ ውስጥ ስለሚፈጠሩ ለአመግባባቶች

የፍትሐብሔር ሕጉ በጋብቻ ውስጥ የሚፈጠሩ ክርክሮች በቤተዘመድ ሽምግልና ዳኞች ታይተው መፍትሔ እንዲያገኙ ይደነግጋል፡፡ ከፍቺ መለስ የሚነሱ ጉዳዮች እንደአስፈላጊነቱ ባልና ሚስቱ በሚመርጧቸው ሽማግሌዎች አማካኝነት እንዲታዩ ቢደረግ ጠቀሜታ የሚኖረው በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 725 የነበረው ድንጋጌ በቤተሰብ ሕጉ በአንቀጽ 118 እንዲንፀባረቅ ተደርጓል፡፡

ክርክሩን በሽምግልና መፍታት ካልተቻለ ወይም የሽምግልናው ውሳኔ ቅሬታ የሚያሳድር ሆኖ ከተገኘ ፍትሕ እንዳይጓደል ጉዳዩ ለፍ/ቤት የሚቀርብበት መንገድ ሊኖር እንደሚገባ ታምኖበታል በሽምግልና በተሰጠ ውሳኔ ላይ ለፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረብ እንደሚቻል ተደንግጓል፡፡

ከፍቺ በመለስ ያሉ የባልና ሚስት አለመግባባቶችን ወደ ፍርድ ቤት ከመወሰድ ይልቅ ጉዳያቸው በሽማግሌዎች እንዲታይላቸው ቢያደርጉ ለጋብቻው ፀንቶ መቀጠል ከሚሰጠው ጥቅም በተጨማሪ በፍርድ ቤቶች ሊፈጠር የሚችለው የሥራ ጫና በማቃለል ረገድም ጉልህ ሚና ስለሚኖረው ሽምግልና በዚህ ደረጃ እንዲቀጥል ማድረጉ ተመርጧል፡፡ ይህ አሠራር ከባህልም አኳያ ሲሰራበት የቆየና ተቀባይነት ያለው ነው፡፡

www.abyssinialaw.com

## ክፍል 3

## ስለ እርቅ

የሽምግልና አሰራር በሀገራችንም ሆነ በሌሎች ሀገሮች በባህልም ሆነ በዘመናዊ መንገድ በሰፊው ሲሰራበት ቆይቷል፣ አሁንም እየተሠራባት ይገኛል። በማህበራዊ ሆነ ግላዊ ግንኙነቶች የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ወይም ልዩነቶችን ለማጥበብም ሆነ እርቅ ለማምጣት ሽምግልና ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ይታመናል።

የጋብቻ ግንኙነት የሚያስከትላቸው ውጤቶች በአካባቢ በባህል ደረጃ በሕብረተሰቡ ወይም በማህበረሰቡ በሰፊው የሚታወቁ እንደመሆናቸው መጠን በዚህ ዙሪያ የሚፈጠሩ አለመግባባቶች በመደበኛ የፍትሕ መድረክ ከሚቀርቡ ይልቅ አካባቢያዊ በሆነ አሰራርና ዘዴ እንዲታዩ ማድረግ ይበልጥ ተቀባይነት ይኖረዋል።

በሌላ በኩል ሽምግልና መደበኛ የፍትሕ አካላትን አጋዥ ተቋም ከመሆን አልፎ ፍ/ቤቶችን ተክቶ እንዲሰራ ማድረጉ የዜጐችን መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች በተሟላ ሁኔታ መከበራቸውን ለማረጋገጥ አያስችልም። በጋብቻ የሚፈጠሩ ማንኛውም አለመግባባቶች በቤተዘመድ ሽምግልና ጉባኤ ሊታዩ እንደሚገባ የፍትሐብሔር ሕጉ በመደንገጉ ምክንያት በተወሰነ ጊዜ መፍትሔ ሊያገኙ የሚገባቸው ጉዳዩች እየተንዛዙ ፍትሕ የሚጓደልበት ሁኔታ እንደነበር ተስተውሏል።

በመሆኑም በአዲሱ የቤተሰብ ሕግ የፍቺ ክርክር በአስገዳጅ መልኩ ሳይሆን ፍትሕ ሊያስገኝ በሚችልበት ሁኔታና ደረጃ በሽምግልና እንዲታይ በማድረግ የሽማግሌዎች ሚናም እርቅ ከማስገኘት ውጭ እንዳይሆን ተገድቧል። የጋብቻ ክርክሮች እንደአስፈላጊነቱ በሽምግልና እንዲታዩ ሲደረግ ቀደም ሲል ተቋሙ በውሳኔ ሰጭነቱ በፍ/ብ/ሕጉ የሰፈሩት የአፈፃፀም ሥርዓቶች በቀጥታ ተፈፃሚነት የማይኖራቸው በመሆኑ ክርክሮች በሽምግልና እንዴት፣ በምን ሁኔታና በምን ያህል ጊዜ ሊታዩ እንደሚገባ፣ ውጤቱ እስከምን ድረስ እንደሆነ የሚያመለክቱ ቀለል ያሉ የሥነ ሥርዓት ደንቦች ማስቀመጠጥ እንደሚገባ ታምኖበት በዚህ ምዕራፍ ሥር በክፍል 3 ከአንቀጽ /119-122/ ያሉት አዲስ ድንጋጌዎች እንዲጨምሩ ተደርጓል።

### አንቀጽ 119 ስለስታራቂ ሽማግሌዎች

በፍ/ብ/ሕጉ የሽምግልና ዳኞች ፍ/ቤቶችን ተክተው ይሰሩ ስለነበር የሽምግሌዎች አሠራርና ብዛት መደበኛ የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓትን ለመከተል የሚያስገድድ ሲሆን ቁጥራቸው በሕግ የተገደበ ነበር። በቤተሰብ ሕጉ የሽምግልና ሚና ውስን ከመሆኑም በተጨማሪ በፍ/ቤት ቁጥጥርና ክትትል የሚካሄድ በመሆኑ ምክንያት የሽምግሌዎች ብዛት በተከራካሪ ወገኖች እንዲወሰን ተደርጓል።

በፍ/ቤት እንዲታይ የቀረበው የፍቺ ክርክር በሽምግልና እንዲታይ ሲደረግ ተከራካሪዎች ሁኔታው ከተገለፀላቸው በኃላ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የመረጧቸውን ሽማግሌዎች ማሳወቅ እንደሚኖርባቸው፣ ሽማግሌዎቹ ሊያደርጉት ስለሚገባ ጥረትና ሊከተሉት ስለሚገባ አሰራር ፍ/ቤቱ አስፈላጊውን ምክርና መመሪያ በመስጠት በአሰራራቸው ላይ ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ የተፈለገው ውጤት ስለመገኘቱ ማረጋገጥ ስለሚኖርበት ይህንኑ የሚመለከት ድንጋጌ እንዲኖር ተደርጓል።

www.abyssinialaw.com

<u>አንቀጽ 120</u> <u>ስለተጨማሪ የእርቅ ጊዜ</u>

የእርቅ ሙከራው በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ መታየትና ማብቃት ስለሚኖርበት እርቅ ሊፈጥር የሚችል ሁኔታ መኖሩን ማረጋገጥ እስካልተቻለ ድረስ በሶስት ወር ውስጥ ታይቶ ለፍ/ቤቱ ሪፖርት መደረግ እንደሚኖርበት በአንቀጽ 119 እንዲሰፍር የተደረገ ሲሆን ተጨማሪ ጊዜውም ቢሆን ከአንድ ወር የበለጠ ሊሆን እንደማይገባ በአንቀጽ 120 ተመልክቷል።

<u>አንቀጽ 121</u> <u>የአስታራቂ ሽማግሌዎች ኃላፊነት</u>

የአስታራቂ ሽማግሌዎች ሚና እርቅ ከመፍጠር ውጭ እንዳልሆነ ከፍቺ ጋር የተያየዘ ውሳኔም ሆነ ትዕዛዝ የመስጠት ሥልጣን እንደሌላቸው የሽምግልናው ውጤት ለፍ/ቤት ሪፖርት እንደሚደረግ በአንቀጽ 121 ሥር በግልጽ እንዲሰፍር ተደርጓል።

የፍቺ ክርክሩ ለሽምግልና ሊመራ የሚችለው በቤተሰብ ሕጉ ስለጋብቻ መፍረስ በምዕራፍ 4 ሥር በአንቀጽ 82/2/ በተዘረዘሩው መሠረት አስፈላጊነቱን ፍ/ቤቱ ሲያምንበት እንደሆነና በአንፃሩ ጉዳዩ በፍ/ቤት በኩል ሊታይ የሚችልበት ሁኔታም መኖሩ ተመልክቷል።

<u>አንቀጽ 122</u> <u>የሽምግልና ሪፖርት አለመቅረብ</u>

ሽምግልናው በተፈለገው ጊዜና ሁኔታ ካልተደረገ፣ ውጤቱም ለፍ/ቤቱ በሪፖርት መልክ እንዲቀርብ እስካልተደረገ ድረስ ፍ/ቤቱ የፍቺ ጥያቄውን በቀረበለት አኳኃን በቀጥታ የሚያስተናግድበት ምክንያት ስለማይኖር ፋይሉም ቢሆን ሊንቀሳቀስ ስለማይገባ ወደፊት ሊታይ የሚችልበትን ሥርዓት በማስቀመጥ ፋይሉ ሊዘጋ ይገባል። ያለበቂ ምክንያት የሽምግልና ሪፖርት ሳይቀርብ ከቀረ ውጤቱ የፋይል መዘጋትን ሊያስከትል እንደሚችል በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 122 ተመልክቷል። ይህ ሲባል ግን ከባልና ሚስቱ አንዳቸው ወይም ሁለቱም ቀርበው ሽምግሌዎቹ ግዴታቸውን በአግባቡ እንዳልተወጡ ለፍርድ ቤቱ ከገለጹ ሽማግሌዎቹ ሪፖርት ባለማቅረባቸው ብቻ ፋይሉ ይዘጋል ማለት አይደለም።

## ምዕራፍ 9

## ስለመወለድ
## ክፍል 1

### <u>አባትነትንና እናትነትን ስለማወቅ</u>

### <u>ንዑስ ክፍል 1 አጠቃላይ ድንጋጌዎች</u>

አባትነትና እናትነት የሚታወቀው በመወለድ ሲሆን መወለድም በጋብቻም ሆነ ከጋብቻ ውጭ በሚፈጠሩ ሌሎች ግንኙነቶች ሊከሰት ይችላል። እናትነት ተፈጥሮአዊ በሆነ የእርግዝና ሁኔታ የሚታወቅ በመሆኑ አብዛኛው ከመወለድ ጋር በተያያዘ ክርክር ሊያስነሳ የሚችለው የአባትነት ጉዳይ ነው። ልጆች ያለአባት እንዳይቀሩ፣ አባት ሊሆኑ

www.abyssinialaw.com

የሚችሉ ሰዎችም ላልወለዷቸው ልጆች አባት እንዳይሆኑ ለማድረግ አባትነትና እናትነት ሊታወቅ የሚችልባቸውን ሁኔታዎች በሕግ መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕጉ በምዕራፍ 10 ከቁጥር /738-795/ የሰፈሩት ድንጋጌዎች አስፈላጊ ማሻሻያ ተደርጐባቸው በዚህ ምዕራፍ ሥር እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

በክፍል 1 ሥር የተመለከቱት ድንጋጌዎች እናትነትና አባትነት በሕግ ግምት የሚታወቅባቸውን ሁኔታዎች ያካተቱ በመሆኑ በዚህ ረገድ የአገላለጽ ለውጥ ማድረግ አስፈልጓል፡፡

<u>አንቀጽ 123 የሕግ ድንጋጌዎች አስገዳጅነት</u>

አንቀጽ 123 የሕግ ድንጋጌዎች አስገዳጅ መሆናቸውን በተመለከተ የሰፈረው ድንጋጌ ከፍ/ብ/ሕጉ ከቁጥር 738 የተወሰደ ሲሆን በርዕሱና በድንጋጌው ላይ የአገላለጽ ለውጥ ተደርጓል፡፡

<u>አንቀጽ 124 ስለእናትነት</u>

በአንቀጽ 124 እናትነት ሊታወቅ ስለሚችልበት ሁኔታ የተመለከተው ድንጋጌ እናትነትን ስለማስረዳት በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 739 የሰፈረው ሲሆን ርዕሱም ሆነ ይዘቱ እናትነትን ከማስረዳት /Proof of maternity/ ጋር የተገናኘ በመሆኑ እናትነት በመውለድ የሚታወቅ መሆኑን በግልጽ በማመልከት ተሻሽሎ ተቀርጿል፡፡

<u>አንቀጽ 125 ስለአባትነት</u>

በአንቀጽ 125 አባትነት ስለሚታወቅበት ሁኔታ የተመለከተው በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 740 የሰፈረው ድንጋጌ ሲሆን በንዑስ /3/ ላይ ከተደረገው ማሻሻያ በስተቀር ሌላው ባለበት ተወስዷል፡፡

አባትነት በፍርድ ሊታወቅ ስለሚችልበት ሁኔታ በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 740 ንዑስ ቁጥር 3 የተመለከተው ድንጋጌ ከመደፈርና ከመጠለፍ ጋር በተያያዘ የተቀረፀ ነው፡፡

በፍ/ብ/ሕጉ በፍርድ አባትነት ከሚታወቅባቸው መንገዶች በተጨማሪ ሌሎች ሁኔታዎች በቤተሰብ ሕጉ እንዲካተቱ በመደረጋቸው በዝርዝር ማስፈር አላስፈለገም በመሆኑም አባትነት በፍርድ ቤት ውሳኔ ሊታወቅ እንደሚችል በጥቅሉ ሰፍሯል፡፡

በምዕራፍ 9 በክፍል 2 ሥር አባትነት በሕግ ግምት ሊታወቅ የሚችልበትን ዝርዝር ሁኔታ የሚያሳዩ ከአንቀጽ /126 እስከ 130/ ያሉትን ድንጋጌዎች ይዟል፡፡

<u>አንቀጽ /126 - 130/ አባትነት በሕግ ግምት ስለሚታወቅበት ሁኔታ</u>

በዚህ ክፍል የተመለከቱት ድንጋጌዎች በፍ/ብ/ሕጉ ከቁጥር /741 - 745/ የሰፈሩትን የሚያጠቃልል ሲሆን፣ በአንቀጽ 126 ባል አባት ነው ተብሎ ስለሚገመትበት ሁኔታ፣ በአንቀጽ 127 በሕግ የተቀመጠው ግምት በሌላ ሁኔታ

www.abyssinialaw.com

ሊስተባበል የማይችል ስለመሆኑ፣ በአንቀጽ 128 በጋብቻ ዘመን የተፀነሰ ልጅ አባትነት ስለሚታወቅበት ሁኔታ የተካተቱት ድንጋጌዎች፣ ከፍ/ብ/ሕጉ ከቁጥር 741፣ 742፣ 743 የተወሰዱ ናቸው።

ድንጋጌዎቹ የጽንሰ ሃሳብ ለውጥ የሚያስፈልጋቸው ባለመሆኑ መጠነኛ የቃላት ለውጦች ብቻ በማድረግ ተወስደዋል።

ባልየው በሃገር ያለመኖሩን በፍርድ በሚነገርበት ጊዜ ባል የተወለደው ልጅ አባት ሊሆን እንደማይችል በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 740 የሰፈረው ድንጋጌ ስለመጥፋት በፍ/ብ/ሕጉ አንደኛ መጽሐፍ በምዕራፍ 4 ሥር የሰፈሩትን ድንጋጌዎች የሚመለከት ነው።

የአንድ ሰው መጥፋት በፍርድ እንዲነገር ጥያቄ የሚቀርበው ለሁለት ዓመት ጊዜ ወሬውን ሳይሰጥ በመቅረቱ ምክንያት እንደሆነ በቁጥር 154 እና በተከታይ ቁጥሮች ተመልክቷል።

የእርግዝና ጊዜ ከሶስት መቶ ቀናት ሊያልፍ እንደማይችል በመደንገጉ ባል የልጁ አባት እንዳልሆነ የሕግ ግምት ሊወሰድ የሚገባው ፍርድ ከተሰጠ በኋላ ሳይሆን ወሬውን መስጠት ካቆመበት የመጨረሻ ቀን ጀምሮ እርግዝና እስከሚቆይበት ጊዜ ድረስ ሊሆን ይገባል። በመሆኑም በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 740 የሰፈረው ድንጋጌ በዚሁ አኳኋን ማሻሻያ ተደርጐበት በአንቀጽ 129 ሥር ተካትቷል።

በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 130 የተመለከተው ድንጋጌ ከፍ/ብ/ሕጉ ቁጥር 745 የተወሰደ ሲሆን በጋብቻ ጊዜ አባትነትን በሕግ ስለማወቅ በአንቀጽ 127 እና 128 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ መሆናቸውን በመግለጽና የቃላት ለውጥ በማድረግ በንዑስ ቁጥር 2 መጠነኛ ማሻሻያ ታክሎበት በቀጥታ እንዲወሰድ የተደረገ ነው

<u>አንቀጽ / 131 - 142/ ልጅነትን ስለመቀበል</u>

በፍትሐብሔር ሕጉ በንዑስ ክፍል 3 አባትነትን ስለማወቅ ከቁጥር /746 - 757/ የተመለከቱት ድንጋጌዎች በሕግ ግምት መነሻነት ብቻ አባትነት የሚታወቅበት ዘዴ ሳይሆን አባት ልጁ መሆኑን የሚቀበልበትን ሥርዓት የሚዘረዝሩ ናቸው። በዚህ አኳኋን አባትነት ሊታወቅ የሚችል ቢሆንም አባት ነው የተባለው ሰው ልጁን የሚያውቅበትና የሚቀበልበት ዘዴ ነው። ስለሆነም የንዑስ ክፍል 3 አርዕስት ልጅነትን ስለመቀበል በሚል ተስተካክሎ እንዲሰፍር ተደርጓል።

በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 131 የተመለከተው ከፍ/ብ/ሕጉ ቁጥር 746 የተወሰደ ነው። በፍትሐብሔር ሕጉ በቁጥር 747 ልጅነትን ለመቀበል ስለሚቻልበት ሁኔታ የሰፈረው ድንጋጌ «የማወቁ ፅሁፍ የሚፃፍበት» በሚል አርዕስት መግለጹ አግባብነት እንደሌለው ታይቶ «ትርጓሜ» በሚል እንዲተካ የተደረገ ሲሆን የተፀነሰንም ልጅ መቀበል የሚቻልበት ሁኔታ በመኖሩ ማስተካከያና የአገላለጽ ለውጥ በማድረግ በንዑስ ቁጥር 2 የሰፈረውን በማስወጣት በአንቀጽ 132 ሥር እንዲካተት ተደርጓል።

በአንቀጽ 133 ልጅነትን ለመቀበል ስለሚቻልበት ሥርዓት /ፎርም/ የሰፈረው ድንጋጌ ከፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 748 የተወሰደ ሲሆን በጽንሰ ሃሳብ ደረጃ ተመሣሣይነት

www.abyssinialaw.com

ቢኖረውም ልጅነትን ለመቀበል በማስረጃነት ሊወሰዱ የሚችሉ ሰነዶች /ጽሁፎች/ ምን እንደሆኑ ተዘርዝረው እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡

በክብር መዝገብ ሹም ጽ/ቤት ፊት የሚደረግ ምዝገባ በተለይ ከጋብቻ እና መወለድ ጋር በተያያዘ ለሚነሱ ክርክሮች በማስረጃነት እንዲወሰድ መደረጉ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

ምዝገባው ታስቦበት የሚደረግ ከመሆኑም በተጨማሪ በጽ/ቤቱ የሚሰጠው ቃል በጥንቃቄ የሚከናወን በመሆኑ ልጅነትን ለመቀበል ከሚቻልባቸው ሥርዓቶች በዋነኛነት ሊታይ ይችላል፡፡

አንድ ሰው ልጁ ከመወለዱ በፊትና በኋላ በተግባር የሚያሳየው ሁኔታና የነበረው ግንኙነት አባት ሊያሰኘው የሚችልበት መንገድ ሊሆን እንደሚችል የሚገመት ቢሆንም ልጅነቱን ራሱ በግልጽ ካልተቀበለ በስተቀር በግንኙነቱ ብቻ በማስረዳት ልጅነትን ለመቀበል የሚያስችል ፎርም ሆኖ ሊወሰድ አይገባም፡፡

በሌላ በኩል አንድ ሰው ልጄ ነው ሲል በቅጥር፣ በጡረታ ፎርም እና በመሣሰሉት ፎርሞች አረጋግጦ ከሆነ ልጅነትን ለመቀበል የሚያስችል ማስረጃ ሆኖ ሊወሰድ እንደሚገባ ታምኖበታል፡፡

ወራሽነትን ለማረጋገጥ በኑዛዜ የሚሰጥ ቃል አንድ ሰው ልጅነቱን አምኖ መቀበሉን የሚያሳይ በመሆኑ በሕጉ ከሚጠየቁ ሥርዓቶች አንደኛው እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ሆኖም በሌሎች ግላዊ የደብዳቤ ልውውጦችና ጽሁፎች ላይ አባት መሆኑን የሚያመለክቱ ሁኔታዎች መኖራቸውን ለማስረዳት የሚቻል ቢሆንም በፍ/ቤት ተመዝነው እስካልተረጋገጡ ድረስ ልጅነትን ለመቀበል የሚቻልባቸው ብቂ ሁኔታዎች ባለመሆናቸው በዚህ ድንጋጌ ሥር እንዲካተቱ አልተደረገም፡፡

በመሆኑም በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 113 መሠረት ልጅነትን ለመቀበል የሚያስችል ፎርም/ሥርዓት/ በጽሁፍ ካልሆነ በስተቀር ተቀባይነት እንደማይኖረው ተመልክቷል፡፡ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 134 ልጅነትን በፍ/ቤት በፀደቀ የውክልና ሥልጣን ካልሆነ በስተቀር በማንኛውም ሰው ሊደረግ እንደማይችል የሰፈረው ድንጋጌ በፍ/ብ/ሕጉ ከቁጥር 749 የተወሰደ ሲሆን የቃላት ለውጥ ከማድረግ በስተቀር በጽንሰ ሃሣብ ደረጃ ማሻሻያ ማድረግ አላስፈለገም፡፡

በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 750 የልጁ አባት ከሞተ ወይም ፈቃዱን ለመስጠት በማይችልበት ጊዜ ልጅነትን በአባት በኩል ያለ ወንድ ወይም ሴት አያት፣ ከሌሉም ወላጆች ሊቀበሉ እንደሚችሉ የተደነገገ ሲሆን የቃላት ለውጥ ተደርጎ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 135 እንዲካተት ተደርጓል፡፡

ልጅነትን መቀበል ውጤት የሚኖረው የልጁ እናት አባትነቱን አምና የምትቀበል ሲሆን እንደሆነ በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 751 የሰፈረው ድንጋጌ የቃላት ለውጥ ተደርጎበታል፡፡ የልጁ እናት ከሞተች ወይም ፈቃዷን መስጠት በማትችልበት ጊዜ ከልጁ እናት ወላጆች አንዱ የእምነት ቃሉን መስጠት እንደሚችል ተገልጾ የወላጆችን ማንነት በዝርዝር በማስቀመጥ ሳያስፈልግ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 136 በግልጽ ሰፍሯል፡፡

በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 137 አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ አካለመጠን ሲደርስ አባትነቱን ካልተቀበለ በስተቀር የልጅነት መቀበል ውጤት እንደማይኖረው የሰፈረው

www.abyssinialaw.com

ድንጋጌ ከፍ/ብ/ሕጉ ከቁጥር 752 የተወሰደ ነው:: ልጅነትን ለመቀበል የሚቀርብ ጥያቄ በልጁ እናት በኩልም ሆነ አካለመጠን በደረሰው ልጅ አስተያየት የሚጠየቅበት ጊዜ አንድ ወር እንደሆነ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 138 ተሻሽሎ ተቀርጿል:: ድንጋጌው በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 753 የመቀበሉ ፎርም በሚል ርዕስ ከሰፈረው የተወሰደ ሲሆን ክርክር ለማቅረብ የሚችሉትን ወገኖች ለይቶ የሚያመለክት በመሆኑና ለትርጉም በር የሚከፍት ስለሆነ ማሻሻያ ተደርጐበታል::

በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 139 ልጁ ከሞተ ልጅነት የመቀበል ሁኔታ በተወላጆች ካልሆነ ተፈጻሚነት የሌለው መሆኑን፣ የልጅነትን መቀበል መሻር አካለመጠን ባላደረሰ ልጅ ካልሆነ በስተቀር የማይቻል ስለመሆኑ በአንቀጽ 140 የሰፈሩት ድንጋጌዎች የቃላት ለውጦች ከማድረግ በስተቀር ከፍ/ብ/ሐጉ ከቁጥር 754 እና 755 በቀጥታ እንዲወሰዱ የተደረጉ ናቸው::

በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 756 በኃይል የተሰጠ ልጅነትን የመቀበል ሁኔታ ፈራሽ ሊሆን እንደሚችልና ከአንድ ሰው በላይ ልጅነትን ለመቀበል የማይቻል ስለመሆኑ በቁጥር 757 የሰፈሩት ድንጋጌዎች መጠነኛ የአገላለጽ ለውጥ ተደርጐባቸው በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 141 እና 142 ሥር ተካትተዋል::

## <u>ንዑስ ክፍል 4</u>

## <u>በፍርድ ውሳኔ አባትነት እንዲታወቅ ስለማድረግ</u>

### <u>አንቀጽ 143 - 145 አባትነትን በፍርድ ስለማወቅ</u>

ይህ ክፍል በፍ/ብ/ሕጉ በንዑስ ክፍል 4 ከቁጥር 758 - 761 ያሉትን ድንጋጌዎች የሚመለከት ነው:: በምዕራፍ ዘጠኝ ሥር የልጁ አባት በሕግ ግምት ወይም ልጅነትን ለመቀበል በሚቻልባቸው መንገዶች ለማወቅ የማይቻልበት ሁኔታ ሲያጋጥም አባትነት በፍርድ ቤት በኩል እንዲታወቅ ሊደረግ ይችላል::

በፍርድ ውሳኔ አባትነት እንዲታወቅ የሚያስችሉ ሁኔታዎች በግልጽ ተለይተው እንዲቀመጡ ማድረጉ ልጆች ያለአባት እንዳይቀሩ፣ ሰዎች ላልወለዷቸው ልጆች አባት እንዳይሆኑ ጥንቃቄ ለማድረግ ሲሆን አግባብነት የሌላቸው የክስ ማመልከቻዎች እንዳይቀርቡ ለመከላከል የጐላ ጠቀሜታ ይኖረዋል::

በፍ/ብ/ሕጉ አባትነት በፍርድ እንዲታወቅ የሚቀርብባቸው ምክንያቶች ውስን ናቸው:: በመጠለፍ ወይም በመደፈር በተፈጠረ ግንኙነት ልጅ ተፀንሶ ከሆነ በፍርድ አባትነት እንዲታወቅ ሊደረግ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 758 ተመልክቷል:: ከተጠቀሱት ምክንያቶች ውጭ አባትነት በፍርድ እንዲታወቅ የሚቀርብ ጥያቄ በቀጥታ የሚስተናገድበት ሁኔታ አልነበረም::

ይሁን እንጂ አባትነት እንዲታወቅ በሚቀርቡ ክርክሮች መነሻነት ተቀባይነት ያገኙ አመለካከቶችን እንዲሁም በተጨባጭ ሲያጋጥሙ የሚስተዋሉ ችግሮችን

www.abyssinialaw.com

በማገናዘብ አባትነት በፍርድ ሊታወቅ የሚችልባቸው ሌሎች ተጨማሪ ሁኔታዎች እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

በተንኮል ድርጊት በመነሳሳት ወይም በወንድና በሴቷ መካከል ያለውን ግንኙነት መነሻ በማድረግ በሥልጣን ያለአግባብ በመጠቀም ወይም ለጋብቻ የተስፋ ቃል በመስ ጠት በሚደረግ የግብረሥጋ ግንኙነት ልጅ ሊፀነስ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ በእንዲህ ዓይነት ግንኙነት የሚወለዱ ልጆች አባትነት የሚካድበት አጋጣሚ ተስተውሏል፡፡

በሌላ በኩል በጋብቻ ወይም ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ በመኖር ሳይሆን ቀጣይነት ባለው ሁኔታ አብረው በመኖር የግብረሥጋ ግንኙነት ከሚፈጽሙ ሰዎች የሚወለዱ ልጆች ጉዳይ ክርክር ሲያስነሳ ቆይቷል፡፡ በተጠቀሱት ግንኙነቶችም ሆነ በሌሎች ለተወለዱ ልጆች በእርግዝና ወራትና ከተወለደ በኋላ አባትነቱን ለማረጋገጥ የሚቻልባቸው ዘዴዎች አባት ነው በተባለው ሰው ስለልጁ ጉዳይ የተፃፉ ደብዳቤዎችና ጽሁፎች እንዲሁም ልጁን በመንከባከብ፣ በማስተማር፣ ወይም በማሳደግና በመሣሰሉት ተግባራት እንደአባት መሳተፍ አባትነትን በፍርድ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መንገዶች ናቸው፡፡

የቤተሰብ ሕጉ እነዚህን ተጨማሪ ሁኔታዎች በማካተት የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 758 ተሻሽሎ በአንቀጽ 143 ሥር እንዲሰፍር ተደርጓል፡፡

አባትነትን በፍርድ ለማረጋገጥ የወንጀል ክስ ውሳኔ ሊጠበቅ የሚገባ ባለመሆኑና ከወንጀል ድርጊት በተያያዘ ምክንያት ብቻ ሳይሆን በሌሎች ምክንያቶች ማረጋገጥ የሚቻል በመሆኑ በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 759/2/ የሰፈረው ድንጋጌ ተሰርዟል፡፡

አባትነት በፍርድ ሊረጋገጥባቸው የሚችሉ ሁኔታዎች ክርክር ሊነሳባቸው እንደሚችል የሚታወቅ ሲሆን በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 760 በጥቅሉ የሰፈረውን ተቀባይነት የሚኖራቸውን የማስተካከያ ምክንያቶች በማሻሻል በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 144 ተዘርዝረው እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡ አባት ነህ የተባለው ሰው እናቲቱ የተወለደው ልጅ በተፀነሰበት ጊዜ እና ከአንድ ሰው በላይ የግብረሥጋ ግንኙነት ያደረገች መሆኗን በማረጋገጥ ዘመናዊ በሆነ የሕክምና ወይም የምርመራ ዘዴ አባት ያለመሆኑን ማስረዳትና ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

አባትነቱ እንዲረጋገጥ ክርክር የቀረበበት ሰው ልጁ በተረገዘበት ጊዜ ከእናትዬው ጋር ግንኙነት ያልነበረው ስለመሆኑ መጥፋቱን ወይም የደረሰበትን አደጋ በምክንያትነት በማቅረብና በማስረዳት ማስተባበል የሚቻልበት ሁኔታ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 145 በሌላ ሁኔታ አባትነት በፍርድ ሊታወቅ እንደማይችል የሰፈረው ድንጋጌ አላስፈላጊ ክርክሮችን ለማስቀረት የሚረዳ በመሆኑ ከፍ/ብ/ሕጉ አንቀጽ 761 በቀጥታ የተወሰደ ነው፡፡

## ክፍል 2

## አባትነትን በመወሰን ላይ ስለሚኖረው የሕግ ግምት

www.abyssinialaw.com

በፍ/ብ/ሕጉ በምዕራፍ አስር በክፍል ሁለት «በአባትነት ምክንያት ስለሚነሳው ክርክር» በሚል ርዕስ ሥር ከቁጥር /762 - 768/ የተመለከቱት ድንጋጌዎች የተወለደው ልጅ ከአንድ በላይ አባት እንዲኖረው ለማድረግ የሚያስችሉ ግምቶች /ሁኔታዎች/ በሚያጋጥሙበት ጊዜ ተፈፃሚ የሚሆኑ የሕግ ግምቶች /መፍትሔዎች/ ናቸው፡፡

በፍ/ብ/ሕጉ ለርዕሱ የተሰጠው ስያሜ በድንጋጌዎቹ የሰፈረውን ዝርዝር ሁኔታ በቀጥታ የሚያንፀባርቅ በመሆኑ የሕግ ግምት ተብሎ ተስተካክሏል፡፡

<u>አንቀጽ 146 አባትነትን ስለመወሰን</u>

በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 762 በሁለት አባቶች መካከል ሊደረግ ስለሚችል ውል የሰፈረው ድንጋጌ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 146 እንዲካተት የተደረገ ሲሆን «ውል» የሚለው ቃል ንብረት ነክ የሆኑ ግንኙነቶችን የሚያመለክት በመሆኑ በርዕሱና በሌሎች ድንጋጌዎች «ስምምነት» በሚል ማስተካከያ ተወስዷል፡፡

<u>አንቀጽ 147 አባትነትን ለመወሰን ስለሚጠየቅ ፎርም</u>

በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 763 አባትነትን በውል ለመወሰን መሟላት ስለሚገባው ስርዓት የተመለከተው ድንጋጌ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 147 እንዲሰፍር የተደረገ ሲሆን በሃገራችን በተግባር ያለውን የሽምግልና አሰራርና ቁጥር ከግምት ውስጥ በማስገባት ስምምነቱን ሊያረጋግጡ የሚገባቸው ሽማግሌዎች ቁጥር ከአራት ወደ ሶስት ዝቅ እንዲል ተደርጓል፡፡

<u>አንቀጽ 146 በሕግ ስለሚወሰድ ግምት</u>

በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 148 የተመለከተው ድንጋጌ ከአንድ በላይ አባት ሊሆኑ በሚችሉ ሰዎች መካከል ክርክር በሚኖር ጊዜ አባትነትን ለማረጋገጥ በመፍትሔነት ሕጉ የሚያስቀምጣቸው ግምቶችን የሚወስን ነው፡፡ ይኸው ድንጋጌ ከፍ/ብ/ሕጉ ከቁጥር 764 የተወሰደ ሲሆን በንዑስ ቁጥር 1 ላይ የቃላት ለውጥ የተደረገ ቢሆንም የጽንሰ ሃሳብ ማሻሻያ አልተደረገም፡፡ የልጁ እናት ከአንድ በላይ ከሆኑ ሰዎች ጋር ባላት ግንኙነት ምክንያት የአባትነቱ ክርክር በአንድ በኩል በሕጋዊ ባል በሌላ በኩል ጋብቻ ሳይፈጽም እንደባል በሚኖር ሰው መካከል በሚሆንበት ጊዜ የተፈጠረውን ግጭት ለማስወገድ በሕጉ በኩል የተመረጠው ግምት ሕጋዊ የጋብቻ ግንኙነት ያለው ሰው እንደሆነ ያመለክታል፡፡

በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 764 ንዑስ ቁጥር /2/ በሁለት የተለያየ ጊዜ እናቲቱ በፈፀመችው ጋብቻ መነሻነት የአባትነት ክርክር ሲያጋጥም ልጁን በወለደችበት ጊዜ ከነበራት ባል ይልቅ በተፀነሰበት ጊዜ የነበራት ባል የልጁ አባት እንደሆነ የሕግ መፍትሔ ተቀምጧል፡፡

የዚህ ግምት ትኩረት የተፈጥሮ አባቱ ልጁ በተፀነሰበት ጊዜ ከእናት ጋር በጋብቻ የኖረው ሰው እንደሆነ በቤተሰብ ሕጉ ምዕራፍ 9 ክፍል 2 አባትነት በሕግ

www.abyssinialaw.com

ግምት ሊታወቅ ስለሚችልበት ሁኔታ የሰፈሩትን ድንጋጌዎች መሠረት የሚያደርግ ነው፡፡ የፍ/ብ/ሕጉ እንግሊዝኛ ቅጂ ከአማርኛው ጋር ልዩነት በሚፈጥር አገላለጽ የሰፈረ ሲሆን ልጁ በተፀነሰበት ጊዜ ከነበረው ባል ይልቅ በተወለደበት ጊዜ የነበረው ባል የልጁ አባት እንደሆነ ያመለክታል፡፡

በእንግሊዝኛ ቅጂ የተወሰደው የሕግ ግምት የልጁን ዘላቂ ጥቅምና አስተዳደግ መሠረት ያደርጋል፡፡ ልጁ በተወለደበት ጊዜ ከእናት ጋር የነበረው ባል አባትነቱን ለመቀበል በመፈለጉ ምክንያት ክርክር ሲያጋጥም የተፈጥሮ ግንኙነቱን ከመከተል ይልቅ ለልጁ ዘለቄታ ጥቅም የሚያስገኘውን አማራጭ መቀበል ተመራጭነት ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም በእንግሊዝኛው ቅጂ የሰፈረው አገላለጽ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 148/ለ/ እንዲሰፍር ተደርጓል፡፡

<u>አንቀጽ 149 አባትነትን በስምምነት ስለማስተላለፍ</u>

በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 149 አባትነትን በስምምነት ለሌላ ሰው ማስተላለፍ ስለሚቻልበት ሁኔታ የሰፈረው ድንጋጌ ከፍ/ብ/ሕጉ አንቀጽ 765 የተወሰደ ነው፡፡ ጋብቻ በተፈጸመ በ180 ቀናት ውስጥ የተወለደ ልጅ አባት ባልዬው እንደሆነ አባትነት ሊታወቅ ስለሚቻልበት ሁኔታ ባስቀመጠው ግምት ተመልክቷል፡፡

የተፀነሰ ልጅ ሊወለድ የሚችልበት የመጨረሻ ጊዜ ሶስት መቶ ቀናት ከመድረሱ በፊት ባሉት ሶስት ወራት ውስጥ በመሆኑና ከጋብቻ የሚወለዱ ልጆች የአባትነት ክርክር ሊያስነሳ የሚችል ሁኔታ የሚያጋጥም ባለመሆኑ በጋብቻ ዘመን የተወለደ ልጅ አባቱ የእናቱ ባል እንደሆነ አጠቃላይ ግምት ይወስዳል፡፡

በአንፃሩ በጋብቻ ወይም ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ በመኖር ግንኙነት የተፀነሰው ልጅ ከሁለት መቶ አስር ቀናት በፊት የሚወለድ ከሆነ ግንኙነቱ ከመፈጠሩ በፊት ባሉት ዘጠና ቀናት ውስጥ አስቀድሞ በነበረ የግብረሥጋ ግንኙነት የተፀነሰ ልጅ ሊሆን ይችላል የሚል ግምት የሚያሳድር በመሆኑ ለተወለደው ልጅ የአባትነት ክርክር ሲያጋጥም ወይም ለተወለደው ልጅ አባት ነኝ የሚል ሰው ሲቀርብ አባትነትን በስምምነት ማስተላለፍ የሚቻልበት ሁኔታ ሊፈቀድ ይገባል፡፡ በመሆኑም ይኸው ሁኔታ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 149/1/ ሥር እንዲገባ ተደርጓል፡፡

በሌላ በኩል ጋብቻ ከፈረሰ ወይም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት ከተቋረጠ ቀን ጀምሮ ባሉት ሶስት መቶ ቀናት ውስጥ የሚወለዱ ልጆች አባት በግንኙነቱ እንደተወለዱ በመገመት አባትነታቸው በሕግ ግምት ይታወቃል፡፡ ሆኖም የተፀነሰ ልጅ ሊወለድ ከሚቻልበት መነሻ ጊዜ በኋላ ማለትም ሁለት መቶ አስር ቀናት አሳልፎ ከተወለደ የጋብቻው ወይም ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖሩ ግንኙነት ከተቋረጠ በኋላ ባሉት ዘጠና ቀናት ውስጥ በተፈጸመ ሌላ ግንኙነት የተፀነሰ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡

ይህንኑ የሕግ ግጭት ለማስወገድ በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 765/1/ የሰፈረው ድንጋጌ አስፈላጊ በመሆኑ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 149/2 ሥር ተካትቷል፡፡

<u>አንቀጽ 150 አባትነትን በስምምነት ለማስተላለፈ ስለሚጠየቅ ፎርም</u>

www.abyssinialaw.com

አባትነትን በስምምነት ለማስተላለፍ ስለሚቻልበት ሥርዓት በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 766 የተመለከተው ድንጋጌ የምስክሮች ቁጥር ከአራት ወደ ሶስት ዝቅ እንዲል ከመደረጉ በስተቀር ሌላው በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 150 ሥር እንዲካተት ተደርጓል፡፡

<u>አንቀጽ 151 ስለውክልና</u>

አባትነትን በስምምነት የማስተላለፍም ሆነ የመቀበል ሁኔታ አካለመጠን ያልደረሱና በፍርድ የተከለከሉ ሰዎችም ቢሆኑ በተቻለ መጠን በባለጉዳዩ ሊከናወን እንደሚገባ፣ ስምምነቱን ሌላ ሰው እንዲያከናውን ለማድረግ የፍ/ቤት ፈቃድ እንደሚያስፈልግ በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 767 የሰፈረው ድንጋጌ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 134 ተሻሽሎ በተቀረው አኳኋን ማሻሻያ ተደርጐበት በአንቀጽ 151 ሰፍሯል፡፡

<u>አንቀጽ 152 ቃልን ስለመሻር</u>

አባትነትን ለመቀበል የሚደረጉ ስምምነቶችን ስለማፍረስና ስለመለወጥ በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 768 የሰፈረው ድንጋጌ አባትነትን ስለማወቅ በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 755 እና 766 በሰፈሩት ድንጋጌዎች ተለይቶ የተቀመጠ በመሆኑና የቤተሰብ ሕጉም በዚህ መልክ በመቀረጹ በስምምነት ልጅነትን የተቀበለ አባት ቃሉን መሻር እንደማይችል የተደነገገው በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 152 እንዲሰፍር ተደርጓል፡፡

## <u>ክፍል 3</u>
## <u>ስለልጅነት ማስረጃ</u>

ይህ ክፍል በፍ/ብ/ሕጉ በምዕራፍ 10 በክፍል ሶስት ከቁጥር /769-777/ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ይሸፍናል፡፡ ልጅነትን በልደት የምስክር ወረቀት ይህ ከሌለም የልጅነት ሁኔታ መኖሩን በማስረዳት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

<u>አንቀጽ 154 ልጅነትን በልደት ምስክር ወረቀት ስለማስረዳት</u>

በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 769 ልጅነትን በመወለድ የምስክር ወረቀት ማረጋገጥ የሚቻል ስለመሆኑ የተመለከተው ድንጋጌ የልደት የምስክር ወረቀት በሚል አገላለጽ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 154 እንዲካተት ተደርጓል፡፡

<u>አንቀጽ /155-157/ ልጅነትን በሁኔታ ስለማስረዳት</u>

በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 770/1/ የልጅነት ሁኔታን በተመለከተ የሰፈረው ድንጋጌ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 155 እና 156 እንዲካተት የተደረገ ሲሆን የልጅነት ሁኔታ ስለመኖሩ «ሌሎች ሰዎች» ልጁ ነው እያሉ የሚገምቱበት ሁኔታ የሚለው «ማህበረሰብ» በሚል ቃል ተተክቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 771 የልጅነት ሁኔታን ማስረዳትና ማስተባበል ስለሚቻልበት መንገድ የሰፈረው ድንጋጌ በርዕሱና የይዘት ለውጥ በማድረግ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 157 ተደንግጓል፡፡ የልጅነት ሁኔታ መኖሩ ከተረጋገጠ ፍ/ቤቱ አባት መሆኑን ግምት መውሰድ እንደሚኖርበትም ተመልክቷል፡፡

<u>አንቀጽ /158፣ 162/ ተወላጅነትን ስለማስረዳትና ክስ ማቅረብ ስለሚቻልበት ሁኔታ</u>

ልጅነትን በልደት የምስክር ወረቀት ማስረዳት የሚቻል ሲሆን ማስረጃው በሌለ ጊዜ በልጅነት ሁኔታ /Possession of status/ መኖሩን በማረጋገጥ ነው፡፡ የልጅነት ሁኔታ መኖሩን ለማረጋገጥ ካልተቻለ ለፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ማስወሰን እንደሚቻል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 772 እና 773 ተመልክቷል፡፡

የልጅነት ሁኔታ ስለመኖሩ በሕግ ግምት የሚረጋገጥ በመሆኑ ለፍ/ቤት የሚቀርበው ክስ ልጅነቱ /Filiation/ መኖሩን ለማረጋገጥና ለማስወሰን ነው፡፡ በመሆኑም የልጅነትን ሁኔታ ለማስወሰን የሚለው አገላለጽ «ተወላጅነት» በሚል እንዲሰፍር የተደረገ ሲሆን አግባብነት የሌላቸው ጥያቄዎችን ለመከላከል እንዲቻል የፍ/ቤት ፈቃድ በመያዝ በማንኛውም ዓይነት ማስረጃ ማረጋገጥ የሚቻልበት ሁኔታ ሊከለከል ወይም ሊገደብ አይገባም፡፡ ተወላጅነትን በምስክሮች ወይም በማናቸውም ዓይነት ማስረጃ ማስረዳት እንደሚቻል በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 158 ተደንግጓል፡፡ ልጅነት በባለሥልጣን በተሰጠና ዳኞች ባፀደቁት ጽሁፍ የሚረጋገጥበት አሠራር ባለመኖሩ ምክንያት በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 772 ይህንን በተመለከተ የሰፈረው ሁኔታ እንዲካተት አልተደረገም፡፡

በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 159 ተወላጅነትን ለማረጋገጥ ክስ ማቅረብ ስለማይቻልበት ሁኔታ የሰፈረው ድንጋጌ መጠነኛ የቃላት ለውጦች ከመደረጉ በቀር ከፍ/ብ/ሕጉ ከቁጥር 774 በቀጥታ የተወሰደ ነው፡፡

በፍ/ብ/ሕጉ ተወላጅነትን ለማረጋገጥ የሚቀርብ ክስ በማንና በእነማን ላይ እንደሆነ የማቅረቢያ ጊዜውም መቼ እንደሆነ በቁጥር 775-776 እንዲሁም 777 የተመለከቱት ድንጋጌዎች በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 160፣ 161፣ እና 162 ሥር እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 775/3/ የሰፈረው ድንጋጌ በዚህ ክፍል ሥር ሊካተት የማይገባ በመሆኑ፣ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 777/3/ የተመለከተው ሁኔታ በዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር /1/ እና /2/ ላይ ከሰፈረው ጋር የሚስማማ ባለመሆኑ፣ እንዲወጡ ተደርጓል፡፡

## ክፍል 4

## <u>በተወላጅነት ላይ ስለሚነሳ ክርክርና ስለመካድ</u>

### <u>ንዑስ ክፍል 1 በተወላጅነት ላይ ስለሚነሳ ክርክር</u>

www.abyssinialaw.com

በክፍል 3 ስለልጅነት ማስረጃ የተመለከቱት ድነጋጌዎች ተወላጅነትን ለማረጋገጥ የሚቀርቡ ክሶች የሚመሩበትን ሥርዓት የሚያመላክቱ ሲሆን በክፍል 4 «በሁኔታ ላይ ስለሚነሳ ክርክር» በሚል ርዕስ ሥር ከቁጥር /778-781/ የሰፈሩት ድንጋጌዎች በእናት በኩል ባለ ተወላጅነት ላይ የሚነሱ ክርክሮች የሚታይበት ሥርዓት ምን እንደሆነ የሚዘረዝሩ ናቸው፡፡

በመሆኑም በክፍል 3 በተደረገው ማሻሻያ አኳኋን ርዕሱ « በተወላጅነት ላይ ስለሚነሳ ክርክር» በሚል አገላለጽ ተተክቷል፡፡

<u>አንቀጽ /163-166/ በተወላጅነት ላይ የሚነሳ ክርክር ስለሚታይበት ሁኔታና ሥርዓት</u>

በእናት በኩል በተወላጅነት ላይ ስለሚቀርብ ክርክር በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 778 የሰፈረው ድንጋጌ፣ ክሱ በፍ/ቤት ፊቃድ የሚቀርብ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 779 የተመለከተው ሁኔታ፣ ክሱ ተቀባይነት ስለሚያጣበት ሁኔታ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 780 የሰፈረው ድንጋጌ፣ እንዲሁም ክሱ በማን ላይ ሊቀርብ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 781 የተመለከተው ዝርዝር ሁኔታ መጠነኛ የቃላት ለውጦች ተደርጐባቸው የጽንሰ ሃሳብ ለውጥ ሳያስፈልጋቸው በቤተሰብ ሕጉ ከአንቀጽ /163-166/ ባሉት ድንጋጌዎች በቅደም ተከተል እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

## ንዑስ ክፍል 2

## <u>ስለመካድ</u>

<u>አንቀጽ /167-179/ በአባት በኩል ያለን መወለድ መካድ ስለሚቻልበት ሁኔታ</u>

በዚህ ንዑስ ክፍል «ስለመካድ» በቤተሰብ ሕጉ ከአንቀጽ /167-179/ የተመለከቱት ድንጋጌዎች በፍ/ብ/ሕጉ ከቁጥር /782-795/ የተደነገጉትን የሚመለከት ሲሆን በአባት በኩል ያለን መወለድ በመቃወም የመካድ ክስ ማቅረብ ስለሚቻልበትና ክርክር ስለሚደረግበት ሁኔታ ተፈፃሚ የሚሆኑ ዝርዝር ጉዳዮች ተካተዋል፡፡

በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 790 የማይመስል አባትነት በሚል ርዕስ የሰፈረው ድንጋጌ በሌሎች ድንጋጌዎች ሥር የተጠቃለለ በመሆኑ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 792 የመካድ ክስ የሚቀርብበት ጊዜ ልጁ ከተወለደ በኋላ 180 ቀናት ውስጥ እንደሆነ የተመለከተ ሲሆን በተባለው ጊዜ ውስጥ የመካድ ክስ ሊያቀርብ የሚገባው ሰው በሃገር ባለመኖሩ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች የልጁን መወለድ ላያውቅ እንደሚችል በመገመት የክስ መቅረቢያ ጊዜው የልጁን መወለድ ካወቀበት ወይም ማወቅ ከሚገባው ቀን ጀምሮ መሆኑን በመግለጽ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 176 ተሻሽሎ ሰፍሯል፡፡

በቤተሰብ ሕጉ ምዕራፍ 3 በክፍል 2 ባልና ሚስቱ በስምምነት ተለያይተው መኖር እንደሚችሉ የተደነገገ ሲሆን ስምምነቱ የሚመራበት የተለየ ፎርም ባለመኖሩ በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 784 ንዑስ ቁጥር /1/ ላይ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡

www.abyssinialaw.com

ከላይ ከተደረጉት ማሻሻያዎች በስተቀር የልጁ አባት እኔ አይደለሁም የሚል የመካድ ክስ ማቅረብና መከራከር ስለሚቻልበት ሁኔታ በፍ/ብ/ሕጉ የሰፈሩት ሌሎች ድንጋጌዎች መጠነኛ የቃላት ለውጦች ከማድረግ በስተቀር የጽንሰ ሃሳብ ለውጥ ሳያስፈልጋቸው ተወስደዋል።

## ምዕራፍ 10

## ስለ ጉዲፈቻ

ይህ ምዕራፍ በፍ/ብሔር ሕጉ በምዕራፍ 11 'ስለ ጉዲፈቻ' /'የማር ልጅ' በሚል ርዕስ ሥር የተደነገገውን ይመለከታል።

ሥርዓቱ ባህላዊ በሆነ መንገድ የሚከናወንበት ሁኔታ በመኖሩ የተለያየ ትርጉም ውጤትና ስያሜ ሲሰጠው ቆይቷል። ጉዲፈቻ ከሌላ አብራክ የተገኘን /ያልወለዱትን/ ልጅ የልጅነት ግንኙንት ለመፍጠር የሚደረግ ሥርዓት ነው።

በመሆኑም ለቃሉ ከአንድ በላይ ስያሜ እንዲኖረው ማድረግ በትርጉምና በአፈፃፀም ላይ ችግር የሚያስከትል መሆኑን በመገንዘብ የማር ልጅ የሚለው ቃል እንዲወጣ ተደርጓል።

የጉዲፈቻ ግንኙነት በውል የሚመሰረት መሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 796 ተመልክቷል። ግንኙነቱ በአባትና በጉዲፈቻ ልጁ መካከል ይመሰረታል። ጉዲፈቻ በሌሎች ሀገሮች በስፋት የሚታወቅ አሰራር ሲሆን ጉዲፈቻ ተደራጊው ከተፈጥሮ ወላጆቹ ጋር ያለው ዝምድና የሚቋረጥበት ሁኔታ ይኖራል። በሌላ በኩል የጉዲፈቻ ግንኙነት ከተፈጥሮ ወላጅ ጋር ያለው ዝምድና ሙሉ በሙሉ ሳይቋረጥ የተወሰኑ መብትና ግዴታዎች የሚቀጥልበትን ሁኔታ የሚቀበሉ ሀገሮች አሉ። ሀገራችንም ይህንኑ አካሄድ በመከተል ጉዲፈቻ ከተፈጥሮ ወላጅ ጋር ያለን ግንኙነት እንደማያቋርጥ በፍ/ብ/ሕጉ ተመልክቷል።

የጉዲፈቻ ግንኙነት በሀገር ውስጥ ብቻ የሚወሰን ባለመሆኑ የሌሎች ሀገሮችን አሰራርና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ባገናዘበ መልኩ ሊከናወን ይገባል። በመሆኑም የጉዲፈቻ ውል /ግንኙነት/ የልጁን ጥቅምና ደህንነት የሚያስጠብቅ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል አሰራርና የሕግ ድንጋጌ መኖርን የሚጠይቅ ይሆናል።

ልጆችን ከተፈጥሮ ወላጅ ውጭ የማሳደግ ሁኔታ በተለያየ ምክንያት ሊደረግ ይችላል። በተለይ ባህልን መሠረት በማድረግ ከርህራሄ በመነጨ ፍላጐት ወላጅ አልባ የሆኑና በችግር ምክንያት የሚገኙ ልጆችን በመውሰድ ህይማኖታዊ ግዳጅ ለመፈፀም/ጽድቅን በመፈለግ/ ወይም ስብአዊ አገልግሎት በመስጠት መንፈሳዊ ርካታን ለማግኘት የሚያሳድጉ በርካታ ቤተሰቦች አንዳሉ ይታወቃል። ይህ በጐ ምግባርና ሥራ ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚገባው ተግባር ነው። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች ልጆችን የሚያሳድጉ ወላጆች/ቤተሰቦች/ የራሳቸው ፍቃድና ፍላጐት ሳይገናዘብ አስገዳጅነት የሚኖራቸው የጉዲፈቻ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንዲሆኑ ማድረግ የበጐ ምግባር ሰብአዊ አገልግሎት ተግባራትን የሚያዳክም ከመሆኑም በተጨማሪ የሕጉ ዓላማ በዚህ መልክ ሊተረጎም አይገባም።

www.abyssinialaw.com

በባህላዊ መንገድ የሚፈጸመውን የጉዲፈቻ አሰራር በአካባቢው ወግና ልማድ መሠረት ቀጣይነት እንዲኖረው በማድረግ የጉዲፈቻ ሕግ ከዚህ በተለየ ሁኔታ በስምምነት በልጅና የተፈጥሮ ወላጅ ባልሆኑ ቤተሰቦች መካከል በሚከናወኑ ግንኙነቶች ላይ እንዲያተኩር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የጉዲፈቻ ስምምነት በተፈጥሮ ወላጅና ልጅ መካከል የሥጋና የጋብቻ ዝምድና እንደሚፈጥር በፍ/ብ/ሕጉ ሁለተኛ መጽሐፍ ስለዝምድናና ስለጋብቻ በምዕራፍ 1 ከቁጥር /556-559/ ባሉት ድንጋጌዎች ተመልክቷል፡፡

<u>አንቀጽ 180 ስለጉዲፈቻ ዝምድና</u>

የጉዲፈቻ ዝምድና በጉዲፈቻ ተደራጊው ልጅና በአድራጊው ሰው መካከል በስምምነት ሊፈጠር እንደሚችል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 556 የሰፈረው ድንጋጌ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 180 እንዲሰፍር ተደርጓል፡፡

<u>አንቀጽ 181-183 ጉዲፈቻ ስለሚያስከትለው ውጤትና ዝምድና</u>

በፍ/ብ/ሕጉ ከቁጥር /557-559/ ባሉት ድንጋጌዎች ስምምነት ስለሚያስከትለው ውጤት፣ የጉዲፈቻ አድራጊው ዘመዶች ስለሚያቀርቡት ተቃውሞ እንዲሁም የጉዲፈቻ ልጅ ከቀደምት ዘመዶቹ ከጉዲፈቻና ከጋብቻ ዘመዶች ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት በዝርዝር የተመለከተ ሲሆን ድንጋጌዎቹ ማሻሻያ ሳያስፈልጋቸው በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ /181-183/ ተወስደዋል፡፡

<u>አንቀጽ 184 የጉዲፈቻ አድራጊው ዕድሜ</u>

ጉዲፈቻ አድራጊው የልጁን ጥቅምና ደህንነት ለመጠበቅ ሕፃኑን በተሟላ ሁኔታ ለማሳደግ በሚያስችል የዕድሜ ደረጃ ላይ የደረሰ መሆን ስለሚገባው በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 797 የተመለከተውን የዕድሜ መነሻ ከፍ በማድረግ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 194 ሃያ አምስት ዓመት እንዲሆን ተደርጓል፡፡

<u>አንቀጽ 185 የጉዲፈቻ ልጅ ዕድሜ</u>

የፍ/ብ/ሕጉ የጉዲፈቻ ተደራጊውን የዕድሜ ጣራ ባለመወሰኑ የጉዲፈቻ አድራጊው ዕድሜ ከጉዲፈቻ ልጁ ያነሰ ቢሆንም ስምምነት ከማድረግ የሚከለክል አይደለም፡፡

የጉዲፈቻ ተደራጊው ልጅ ዕድሜ ወሰን እንዲኖረው ካልተደረገ በመነሻነት የሚያገለግለው ዓላማና ግብ ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል፡፡ ስለሆነም ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነውና ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ያልወጣ ማንኛውም ሰው የጉዲፈቻ ልጅ ለመሆን ይችላል፡፡

<u>አንቀጽ 186 ያገባ ሰው ጉዲፈቻ ስለሚያደርግበት ሁኔታ</u>

www.abyssinialaw.com

ያገባ ሰው ጉዲፈቻ ስለሚያደርግበት ሁኔታ በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 798 የተመለከተው ድንጋጌ የቃላት ለውጥ ተደርጐበት በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 186 ሰፍሯል፡፡

<u>አንቀጽ 187 በጽንስ ያለን ልጅ ጉዲፈቻ ስለማድረግ</u>

በፅንስ ላይ ያለን ልጅ የጉዲፈቻ ልጅ ለማድረግ የሚቻል ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 798 ተደንግጓል፡፡ ስምምነቱን የልጁ እናት ልጅ በተወለደ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ መቃወምና ስምምነቱን ለመሠረዝ ትችላለች፡፡

<u>አንቀጽ 188 ልጆች ያሉት ሰው ጉዲፈቻ ስለሚያደርግበት ሁኔታ</u>

አንድ ሰው ልጅ ያለው ቢሆንም በጉዲፈቻ ልጅ ወስዶ ለማሳደግ የሚከለከል እንዳልሆነ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 800 ተመልክቷል፡፡ ይኸው ድንጋጌ በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ ቀጣይነት ሊኖረው እንደሚገባ ታምኖበት በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 188/1/ እንዲካተት የተደረገ ሲሆን በተፈጥሮ ልጅ እና በጉዲፈቻ ልጅ መካከል የአያያዝም ሆነ የአሰተዳደግ ልዩነት እንደማይፈጠር አስቀድሞ መረጋገጥ የሚገባው በመሆኑ ፍ/ቤቱ የጉዲፈቻ ስምምነቱን ከማፅደቁ በፊት የጉዲፈቻውን ልጅ ጥቅም የሚያስጠብቅ ስለመሆኑ የሚያጣራበት ሁኔታ በንዑስ ቁጥር 2 ሥር ተደንግጓል፡፡

<u>አንቀጽ 189 ከአንድ ጊዜ በላይ የጉዲፈቻ ግንኙነት ማድረግ የማይቻል ስለመሆኑ</u>

የጉዲፈቻ ስምምነት ፀንቶ ባለበት ጊዜ ሌላ የጉዲፈቻ ግንኙነት መመስረት እንደማይቻል በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 801 የሰፈረው ድንጋጌ ማሻሻያ ሳያስፈልገው በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 189 ተወስዷል፡፡

አንቀጽ 190-191 የጉዲፈቻ ስምምነት ከማን ጋር እንደሚደረግና ስለወላጆች ፈቃድ

የጉዲፈቻ ስምምነት የሚደረገው በጉዲፈቻ አድራጊውና በልጁ መካከል ሆኖ የልጁ ወላጆች በሕይወት ያሉ ከሆነና የታወቁ ከሆነ ፈቃዳቸውን እንዲሰጡ መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡

በፍ/ብ/ሕጉ የእንግሊዘኛው ቅጅ ከወላጆች አንዱ በመሞቱ ወይም በመጥፋቱ ወይም በሌላ ምክንያት ፈቃዱን ለመስጠት በማይችልበት ጊዜ ወደላይ የሚቆጠሩ ዘመዶች ፈቃድ አስፈላጊ መሆኑን ሲደነግግ የአማርኛው ቅጅ ደግሞ ወደ ላይ የሚቆጠሩ ዘመዶች ፈቃድ አስፈላጊ የሚሆነው የልጁ አባትና እናት በሞት ወይም በሌላ ምክንያት ፈቃዳቸውን ለመስጠት በማይችሉበት ጊዜ ብቻ መሆኑን ይደነግጋል፡፡

የልጁ አንደኛው ወላጅ በሕይወት ካለና ጉዲፈቻው ለልጁ ጥቅምና መልካም አስተዳደግ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ማረጋገጥ ከተቻለ ፈቃዱን ለመስጠት ያልቻለውን ወላጅ በመተካት ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች እንዲሰጡ ማድረግ በወላጆች መካከል በሚፈጠሩ አለመግባባቶች /ልዩነቶች/ ምክንያት ጉዲፈቻ ማድረግ ወደማያስችል ደረጃ የሚያደርስ በመሆኑ የልጁ ዘመዶች ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው ሁለቱም ወላጆች በማይኖሩበት ጊዜ ብቻ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በመሆኑም የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 803 ንዑስ ቁጥር 2 በቀጥታ እንዲወሰድ ተደርጓል፡፡

www.abyssinialaw.com

በአንፃሩ የልጁ አንደኛው ወላጅ በሞት ወይመ በሌላ ምክንያት ፈቃዱን ለመስጠት ካልቻለ በሕይወት ያለው /ሌላኛው/ ወላጅ በሚሰጠው ፈቃድ መነሻነት የጉዲፈቻ ስምምነት ማድረግ እንደሚቻል የሚደነግግ ሁኔታ ተካትቷል፡፡

<u>አንቀጽ 192 አሳዳጊ ተቋማት የጉዲፈቻ ስምምነት ስለሚያደርጉበት ሁኔታ</u>

ወላጅ አልባ በመሆናቸው ወይም በችግር ወይም በሌሎች ምክንያቶች ሕፃናትን ለማሳደግና ለመንከባከብ በተቋቋሙ ድርጅቶች /እጓለማውታን/ ቁጥጥር ሥር ሆነው የሚያደርጉበት ሁኔታ ይኖራል፡፡

በእነዚህና በመሰል ተቋማት አሳዳሪነት የሚገኙ ሕፃናት/ልጆች/ በጉዲፈቻ ለማሳደግ የሚቀርብ ጥያቄ የማይታይበት ሥርዓት በፍ/ብ/ሕጉ በግልጽ ባለመስፈሩ በአፈፃፀም ረገድ የትርጉም ጥያቄ ከማስከተሉም በተጨማሪ ጉዲፈቻ ከወላጁ አስተዳደር ውጭ ያሉትን ልጆች ሊመለከት ይገባል፡፡

በመሆኑም ልጆችን ለማሳደግ የተቋቋሙ ድርጅቶች የሕፃናትን ደህንነት ለመከታተል ሥልጣን የተሰጠው የመንግሥት አካል በሚያቀርበው ዝርዝር መግለጫና አስተያየት መሠረት የጉዲፈቻ ስምምነት በማድረግ ለአሳዳጊዎች መስጠት የሚችሉ ስለመሆናቸው በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 192 ተደንግጓል፡፡

<u>አንቀጽ 193 ከሀገር ውጭ በጉዲፈቻ ስለሚወሰዱ ልጆች</u>

በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 193 የሰፈረው ድንጋጌ በፍ/ብ/ሕጉ ያልተካተተ ሲሆን በሀገሮች መካከል የሚደረግ ጉዲፈቻ ትኩረትና ጥንቃቄ ሊደረግበት እንደሚገባ ያመለክታል፡፡ ድንጋጌው እ.አ.አ. በ1989 በተባባሩት መንግሥታት ድርጅት ፀድቆ ሀገራችን ተቀብላ ያፀደቀችውን የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን መሠረት ያደረገ ነው፡፡

ጉዲፈቻ አድራጊው የውጭ ዜጋ በሚሆንበት ጊዜ የጉዲፈቻ ስምምነቱ በፍ/ቤት ከመጽደቁ በፊት አፈፃፀሙን ለመመርመር በመንግሥት ሥልጣን የተሰጠው አካል የጉዲፈቻ አድራጊውንም ሆነ የልጁን አጠቃላይ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አቋም በማጥናትና በመመርመር አስተያየት መስጠት እንዳለበት ይጠይቃል፡፡

ፍ/ቤቶችም ቢሆን ልጅን በጉዲፈቻ ከአገር ውጭ ለመውሰድ የሚደረጉ የጉዲፈቻ ስምምነቶችን በጥንቃቄ ማየትና ማጣራት እንደሚገባቸውና ጉዲፈቻው የልጁን ጥቅምና ደህንነት ለማስጠበቅ የሚችል መሆኑ መረጋገጥ እንደሚኖርበት ተመልክቷል፡፡

<u>አንቀጽ 194 ጉዲፈቻን ለማፅደቅ ፍ/ቤቶች ሊከተሏቸው ስለሚገባ አጠቃላይ መመሪያዎች</u>

የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 194 ፍ/ቤት በጉዲፈቻ ስምምነት ላይ ስለሚኖረው ሥልጣንና ስምምነቱን ለማፅደቅ ማጣራትና መሟላት ስለሚገባቸው መሠረታዊ ጉዳዩች የሚዘረዝር ድንጋጌ ነው፡፡ ድንጋጌገው በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 804፣ 805 የሰፈሩትን ሁኔታዎች ያገናዘበ ሲሆን የሕፃናት መብቶችን በተመለከተ ተፈፃሚነት ባላቸው ዓለም አቀፍ ሕጐች /ኮንቪንስኖች/ እና በኢ.ሕ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት የሰፈሩትን መመዘኛዎች ሊያሟላ በሚያስችል መልክ ተቀርጿል፡፡

www.abyssinialaw.com

ጉዲፈቻ አዲራጊው አቅምና ብቃት ያለው ስለመሆኑ፣ ልጁን መጠቀሚያ ሊያደርገው የማይችል ስለመሆኑ በፍ/ቤቱ በኩል ትኩረት ተደርጐ መጣራትና መረጋገጥ እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡

የውጭ ሀገር ዜጋ የሚያደርገውን የጉዲፈቻ ስምምነት ለማጽደቅ ልጁ በሀገር ውስጥ የሚያደርግበት ሁኔታ ያለመኖሩን፣ በጉዲፈቻ አድራጊው ሀገር ልጁን የጉዲፈቻ አድራጊው ቤተሰብ የሚያደርግ ሕግ መኖሩን ፍ/ቤቱ ማረጋገጥና በጥንቃቄ ማየት ይኖርበታል፡፡

<u>አንቀጽ 195 የጉዲፈቻ ስምምነት መሠረዝ የማይቻል ስለመሆኑ</u>

የጉዲፈቻ ስምምነት ከፀደቀ በኃላ በማናቸውም ምክንያት ሊፈርስ የማይችል ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 806 የሰፈረው ድንጋጌ በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ ተቀባይነት ያለው ቢሆንም ማሻሻያ ተደርጐበት በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 195 እንዲካተት ተደርጓል፡፡

ጉዲፈቻ አድራጊው ልጁን ዓለም አቀፍ የሕፃናትና ሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎን በሚፃረርና የልጁን ጥቅምና ደህንነት በሚጐዳ አኳኃን መያዙን ማረጋገጥ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የጉዲፈቻ ስምምነቱ እንዲቀጥል ማድረግ የሚያስገኘው ፋይዳ ባለመኖሩ ጉዳዩ በሚመለከተው ማንኛውም አመልካች ጠያቂነት መሰረዝ እንደሚቻል በቤተሰብ ሕጉ አንቅጽ 195 እና 196 ተደንግጓል፡፡

ሕጉ በጉዲፈቻ በሚወለዱ ልጆች ላይ በተጨባጭና በተግባር የሚያጋጥሙ ችግሮችን ማገናዘብ የሚጠበቅበት በመሆኑ የድንጋጌው መካተት የሕፃናትን ጥቅምና ደህንነት ከመጠበቅ አኳያ ጠቀሜታው የጐላ ነው፡፡ ድንጋጌው በአተረጓጐም ላይ ጥንቃቄ ካልተደረገ የጉዲፈቻ ስምምነት እንዲሰረዝ ጥያቄ ማቅረብ የሚቻለው በልጁ አኗኗርና አያያዝ እንዲሁም በወደፊት ሕይወቱ ላይ በተጨባጭ የደረሰ ጉዳት ወይም ወደፊት ሊደርስ የሚችል ጉዳት ስለመኖሩ ማረጋገጥ በሚቻልበት ጊዜ ይሆናል፡፡ ፍ/ቤቱም የስምምነቱ መሰረዝ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ በሚገባ ማጤንና መመዘን ይጠበቅበታል፡፡

<u>ምዕራፍ 11</u>

<u>ስለቀለብ መስጠት ግዴታ</u>

በፍ/ብ/ሕጉ በምዕራፍ 12 ከቁጥር /807-825/ በተመለከቱት ድንጋጌዎች በጋብቻና በሥጋ ዘመዳሞች መካከል ቀለብ የመስጠት ግዴታ እንዴት፣ መቼ እና በምን ሁኔታ እንደሚፈፀም ተዘርዝሯል፡፡

ቀለብ የመስጠት ግዴታው ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን በማቅረብ ላይ ያተኮረ ሲሆን ቀለብ ጠያቂው ሠርቶ ለመብላት ባለመቻሉ ምክንያት በችግር ላይ በሚውድቅበት ጊዜ ሊጠየቅ የሚችል መሆኑ በቁጥር 807 እና 812 ተደንግጓል፡፡

www.abyssinialaw.com

በዚህ ምዕራፍ ሥር በተመለከቱት ዝርዝር ጉዳዩች የማህበራዊ አገልግሎት ድጋፎች በሕብረተሰቡና በመንግስት ሳይሆን ዝምድናን መሠረት በማድረግ የሚከናወኑብትን ስልት ያካትታል፡፡

በዚህም መሠረት ቀለብ የመስጠት ግዴታ ምግብ፣ መኖሪያ፣ ልብስ በማቅረብ እና ጤናን በመንከባከብ ደረጃ ተገድቧል፡፡

ከሕብረተሰቡ ዕድገትና ፍላጐት አኳያ ትምህርት መሠረታዊና አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች በዋነኛነት ሊጠቀስ ይችላል፡፡ በመሆኑም የአካባቢውን ባህልና የቀለብ ሰጪውን አቅም በማገናዘብ ቀለብ የመስጠት ግዴታ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን ለመከታተል የሚያስችሉ አስፈላጊ ነገሮችን ማቅረብና ማመቻቸትን ሊያጠቃልል ይገባል፡፡ በተለይም የህፃናት መብት ኮንቬንሽን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት እንደ ግዴታ ለሁሉም እንዲዳረስ የደነገገ በመሆኑና አገራችንም ኮንቬንሽኑን ያፀደቀችው በመሆኑ መሠረታዊና አስፈላጊ እንዲሆን ተደንግጓል፡፡

<u>አንቀጽ 197 ቀለብ የመስጠት ግዴታ ስለማፈፀምበት ይዘት</u>

የፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 807 ቀለብ በምን መልክ ሊሰጥ እንደሚገባ የሚደነግግ በመሆኑ 'ስለግዴታው ዓላማ' የሚለው ርዕስ 'ስለግዴታው ይዘት' በሚል ማሻሻያ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 197 ሰፍሯል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቀለብ መስጠት ትምህርትንም እንደሚጨምር ተመልክቷል፡፡

<u>አንቀጽ 198 ቀለብ የመስጠት ግዴታ ስላለባቸው ሰዎች</u>

ቀለብ የመስጠት ግዴታ ስላለባቸው ሰዎች ማንነት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 808 የሰፈረው ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር /2/ ላይ ከተደረገው የአገላለጽ ለውጥ በስተቀር ሌላው በሴተሰብ ሕጉ አንቀጽ 198 እንዲካተት ተደርጓል፡፡

<u>አንቀጽ 199 ቀለብ የመስጠት ግዴታ ስለሚቋረጥበት ሁኔታ</u>

ጋብቻው በፍቺ ምክንያት ቀሪ በሚሆንበት ጊዜ በጋብቻ ዘመዳሞች መካከል ቀለብ የመስጠት ግዴታ ሊኖር እንደማይችል በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 809 ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ ጋብቻ በአንድ ተጋቢ ሞት ምክንያት ቀሪ ሲሆን የጋብቻ ዝምድናው የበለጠ የሚጠናከርበት ሁኔታ እንደሚኖር ስለሚታወቅ ድንጋጌው ይህንኑ ማንፀባረቅ እንዳለበት በማመን ጋብቻው የፈረሰው በሞት ምክንያት ከሆነ በጋብቻ ዘመዳሞች መካከል ያለው የቀለብ መስጠት ግዴታ የማይቋረጥ ስለመሆኑ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 199 ተደንግጓል፡፡

በዳኝነት ስለሚነገር አባትነት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 810 የሰፈረውን ድንጋጌ ሴትዮዋ በመጠለፏ ወይም በመደፈሯ ምክንያት ለተወለደ ልጅ አባትነት በፍርድ ውሳኔ በሚረጋገጥበት ጊዜ ልጁ አባትነው ለተባለው ሰው ቀለብ የመስጠት ግዴታ የሌለበት መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ልጁ የተፀነሰው በወንጀል ከመነጨ አድራጐት በመሆኑና የልጁ አባት ለመሆን ፍቃድና ፍላጐት ያለማሳያቱን ግንዛቤ በመወሰድ ነው፡፡ ምንም እንኳን የአባትና የልጁ ግንኙንነት የተመሰረተው በፍርድ ቤት ወሳኔ ቢሆንም ከፍርድ በኃላ ግንኙነታቸው የሚሻሻልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ በፍርድ አባት ነው የተባለው ሰው ለልጁ ቀለብና አስፈላጊ ነገሮችን እንዲያቀርብ የሚገደድ

www.abyssinialaw.com

በመሆኑ አባትነቱ በፍርድ መወሰኑን ምክንያት በማድረግ ብቻ ልጁ ቀለብ እንዳይሰጥ በፍ/ብ/ ሕግ ቁጥር 810 የሰፈረው ድንጋጌ አግባብነት እንደሌለው ታምኖበታል፡፡

አባትነት በፍርድ የሚረጋገጠው በወንጀል ድርጊት ለተፀነሱ ልጆች ብቻ ሳይሆን በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 143 ሥር በተዘረዘሩ ሌሎች ሁኔታዎች ጭምር እንደሆነ ተመልክቷል፡፡

ሆኖም አንድ ሰው ላላሳደረገው ልጅ ወይም የወላጅነት ግዴታውን ሳይወጣ ቀለብ እንዲሰጠው የሚጠይቅበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል የሚገመት ቢሆንም ድንጋጌውን ባለበት እንዲቀጥል ከማድረግ ይልቅ ቢወጣ የሚፈጥረው ችግር ያለመኖሩ ታምኖበት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 810 የሰፈረው ድንጋጌ በቤተሰብ ሕጉ እንዲካተት አልተደረገም፡፡

## አንቀጽ 200 ቀለብ የመስጠት ግዴታ ሊወገድ ስለችልበት ሁኔታ

የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 811 ቀለብ ጠያቂው በቀለብ ሰጭው ሕይወት ላይ አደጋ በመጣል ሙከራ ወንጀል ተከሶ ከተፈረደበት ቀለብ የመጠየቅ መብቱን እንደሚያጣ ይደነግጋል፡፡ ቀለብ ጠያቂው ሊፈጽም ያቀደው አደጋ በሕይወት ላይ ብቻ ሣይሆን በንብረትም ላይ ከሆነ ጉዳዩ በተመሣሣይ አኳኃን ሊፈረጅ ይገባል፡፡

ቀለብ ጠያቂው ሙከራውን ስለማድረጉ ማስረዳት አስከተቻለ ድረስ የወንጀል ፍርድ መጠበቅ አስፈላጊ አይሆንም፡፡ በፍ/ብ/ሕጉ የሰፈረው ደንጋጌ ይህን ሁኔታ ማካተት ስለሚገባ የቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 200 ንብረትንም እንዲጨምር በማድረግ ተሻሽሎ ተቀርጿል፡፡

## አንቀጽ 201 ቀለብ የመስጠት ግዴታ ለመጠየቅ ስለሚቻልበት ሁኔታ

የማህበራዊ አገልግሎት ድጋፍ /soical security / ከአንድ ሀገር የዕድገት ደረጃ ጋር ተያይዞ የሚከናወን መሠረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ በችግር ላይ የወደቀን ሰው መርዳትና ቀለብ የማቅረብ ሁኔታ በሀገራችን በስፋት የተለመደ ሲሆን ይኸው አስተሳሰብ ቀጣይነት ሊኖረው የሚገባ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 812 የሰፈረው ጽንሰ ሀሳብ በቤተሰብ ሕጉ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ አንድ ሰው በችግር ላይ ሊወድቅ የሚችለው ሰርቶ ለመብላት በማይችልበት ጊዜና ሁኔታ ብቻ ሳይሆን በተጨባጭ እንደሚታየው የመሥራት ችሎታ፣ አቅምና ፍላጐት ኖሮት ሥራ ባለማግኘት ምክንያት ጭምር ሊሆን ይችላል ሊሆን ስለሚችል ሕጉ ይህን ሁኔታ ሊያገናዝብ ይገባል የሚል ሀሳብ ከልዩ ልዩ ክፍሎች ተነስቶ ነበር፡፡ ሆኖም አንድ ሰው ለመሥራት እየቻለ ነገር ግን ሥራ ለማግኘት ባለመቻሉ ምክንያት ቀለብ የመጠየቅ መብት እንዲኖረው በቤተሰብ ሕጉ እንዲካተት ማድረግ ሥራ ፈጣሪነትን የማያነሳሳ፣ ጥገኝነትን የሚያበረታታና ለአፈጻፀምም ስለሚያስቸግር እንዲካተት አልተደደተገም፡፡ የቀለብ ሰጭው አቅምና የአካባቢው ባህል ቀለብ ለመስጠትም ሆነ መጠኑንና አፈፃፀሙን ለመወሰን ከግንዛቤ መወሰድ ስለሚኖርበት ሕጉ ይህን ባገናዘበ ሁኔታ እንዲቀረጽ ተደርጓል፡፡

## አንቀጽ /202-214/ ስለቀለብ ግዴታ አፈፃፀም

ስለቀለብ መስጠት ግዴታ አፈፃፀም በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 813 እና በተከታዮቹ ድንጋጌዎች ከጡረታ ጋር በተያያዙ የሰፈሩ አገላለጾች በአጠቃቀም ላይ የተለየ ትርጉም ሊሰጣቸው ይችላል፡፡ በመሆኑም 'የጡረታ ገንዘብ' በሚል የሰፈረው ቃል 'የቀለብ

www.abyssinialaw.com

ገንዘብ’ እንዲሁም ’ሀብት’ የሚለው ’አቅም’ በሚል ቃል ተተክቶ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 202 እንዲሰፍር ተደርጓል፡፡

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 814 ቀለብ የመስጠቱ ሁኔታ ሊሻሻል ስለሚችልበት ሁኔታ የሰፈረው ድንጋጌ የቀለቡን ገንዘብ ብቻ ነው፡፡ ግዴታው ቀለብ ተቀባዩን በመኖሪያ ቤት በመውሰድ እንዲፈፀም ማድረግ የሚቻል በመሆኑ የቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 203 ይህንኑ ሁኔታ ባጠቃለለ መልኩ ሰፍሯል፡፡

የቀለቡ ገንዘብ ተቀባዩ በሚኖርበት ቦታ መፈፀም እንዳለበት የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 815 ይደነግጋል፡፡ የቀለብ ተቀባዩ መኖሪያ ቀለቡን ለማቅረብ ምቹ የማይሆንበት ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም ከተቀባዩ መኖሪያ ይልቅ የሰጭው መኖሪያ ለተቀባዩ አመቺነት የሚኖረው ከሆነ ቀለብ መስጫ ቦታው የተቀባዩን መኖሪያ ብቻ መሠረት ያደረገ ሊሆን እንደማይገባ ስለታመነበት የፍ/ብ/ሕግ 815 ተሻሽሎ በቤተሰብ ሕጉ አንቅጽ 204 የሰፈረ ሲሆን ቀለቡ በተቻለ መጠን ለቀለብ ተቀባዩ በሚያመች ቦታ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

የቀለብ ገንዘብ፣ ሊተላለፍ ወይም በዕዳ ሊያዝ የማይችል ስለመሆኑ፣ በሶስት ወራት ውስጥ ካልተጠየቀ ውዝፍ ሊከፍል የማይችል ስለመሆኑ፣ ቀለብ ተቀባይን ከሰጭ ቤት በማኖር ቀለብ የመስጠት ግዴታን መወጣት የሚቻል ስለመሆኑ፣ ስለቀለብ ሰጭዎች ቅደምተከተልና አፈፃፀም፣ የጉዲፈቻ ልጅ እንዲሁም ወላጆች ቀለብ ስለሚጠይቁበት ሁኔታ እንዲሁም የቀብራ ኪሣራ ከቀለብ ሰጭ ስለሚጠየቅበት ሁኔታ ከፍ/ብ/ሕግ ቁ. /816-825/ በሰፈሩት ድንጋጌዎች በተወሰኑት ላይ ከተደረገ የቃላት ለውጥ በቀር የጽንሰ ሀሳብም ሆነ የይዘት ለውጥ የሚያስፈልጋቸው ባለመሆኑ በቤተሰብ ሕጉ ከአንቀጽ /202-214/ ባሉት ድንጋጌዎች እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ በእናት ወይም በአባት በአንድ በኩል የተወለዱ እህትማማቾችና ወንድማማቾች ከአንድ እናትና አባት ከተለወዱት ተለይተው መታየት የማይገባቸው በመሆኑ ይህንን በተመለከተ ስለቀለብ ሰጭዎች የክፍያ ተራ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 821 በፊደል /3/ የሰፈረው ድንጋጌ ተሰርዟል፡፡

ቀለብ የመስጠት ግዴታ መሠረት ያደረገው አንድ ሰው መሥራት ባለመቻሉ ምክንያት በችግር ላይ መውደቁን ነው፡፡ ችግረኛው ሊረዳ ስለሚችልበት ዘዴና ሁኔታ በአስገዳጅነት መልኩ በሕግ የተቀመጡትን መሠረታዊ ሁኔታዎች ስምምነት በማድረግ ለመለወጥ እንደማይቻል በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 825 ድንጋጌ የሰፈረው ቀጣይነት ሊኖረው ስለሚገባ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 214 እንዲሰፍር ተደርጓል፡፡

## ምዕራፍ 12

## አካለ መጠን ስላልደረሱ ሰዎች

### ክፍል 1

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

በዚህ መዕራፍ ሥር «አካለ መጠን ስላልደረሱ ሰዎች» የተመለከቱት ድነጋጌዎች በፍ/ብ/ሕጉ አንደኛ መጽሐፍ ስለሰዎች ከሚደነግገው ከምዕራፍ 2 የተወሰዱ ናቸው፡፡

www.abyssinialaw.com

የቤተሰብ ሕጉ ከፍ/ብሔር ሕጉ ተነጥሎ ራሱን የቻለ ሕግ ሆኖ በኮድ መልክ የሚወጣ በመሆኑና አካለመጠን ስላልደረሱ ሰዎች የተዘረዘሩት ጉዳዮች ከቤተሰብ ሕጉ ጋር ተያያዥነት ስላላቸው በዚህ ምዕራፍ ተጠቃልለው እንዲደነገጉ ተደርጓል፡፡

<u>አንቀጽ /215-218/ አካለመጠን ስላልደረሱ ሰዎች ጠቅላላ ሁኔታዎች</u>

አካለመጠን ያልደረሱ ሰዎችን በተመለከተ በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 198 የተሰጠው ትርጓሜ እንዲሁም አካለመጠን ያልደረሱ ሰዎች ችሎታ የሌላቸው ስለመሆኑ በቁጥር 199 የሰፈረው ድንጋጌ፣ የጽንሰሃሳብ ለውጥ አልተደረገባቸውም፡፡ ይሁን እንጂ ድንጋጌዎቹን ይበልጥ ግልጽ እንዲሆኑ ለማድረግ አስፈላጊ የቃላት ማሻሻያ የተደረገባቸው ሲሆን በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 198 ጾታን በተመለከተ የሰፈረው ቃል «ጾታ» ሳይለይ ተብሎ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 215 እንዲሰፍር ተደርጓል፡፡

በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 199 አካለ መጠን ያልደረሰ ሰው ችሎታ ስለማጣቱ በርዕሱ የሰፈረው አገላለጽ ቀደም ሲል የነበረን ችሎታ ስለማሳጣት የተደነገገ እንደሆነ የሚያመለክት በመሆኑና አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ችሎታ የሚገደብበት ሁኔታ ከዚህ በተለየ ምክንያት በመሆኑ ርዕሱ «አካለ መጠን ያልደረሰ ሰው ችሎታ የሌለው ስለመሆኑ» በሚል ተሻሽሏል፡፡

በዚህ ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር 1 « ስለሰውነቱ አስተዳደር» የሚለው አገላለጽ በእግሊዘኛው ቅጂ "... for the proper care of his person" የሚለውን ቃል በቀጥታ በመተርጎም የተወሰደ ነው፡፡

የአሳዳሪው ሥልጣን የልጁን መልካም አስተዳደግና ደህንነት ከማስጠበቅ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ይኸው ማሻሻያ ታክሎ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 216 ንዑስ ቁጥር 1 እንዲሰፍር ተደርጓል፡፡

በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 199 ንዑስ ቁጥር /2/ ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ሰው የገንዘብ ጥቅሞቹን እና «የንብረቱን አስተዳደር በተመለከተ እንደራሴው መሆኑን ያመለክታል፡፡ «የገንዘብ ጥቅሞች» የሚለው ቃል በእንግሊዘኛው ቅጂ "pecuniary interests" በሚል ተተርጉሟል፡፡ የገንዘብ ጥቅሞች ንብረት ነክ ጥቅሞችን የማይጨምር በመሆኑ በአፈጻጸም ረገድ ጠበብ ያለ ትርጉም ይኖረዋል፡፡ ንብረት የሚለው ቃል ገንዘብንም ስለሚጨምር ሞግዚቱ አካለመጠን ያላደረሱ ሰዎችን ንብረት ነክ ጥቅሞቹንና የንብረቱን አስተዳደር በተመለከተ እንደሚወክል ተገልጾ ተሻሽሎ ሰፍሯል፡፡

አካለመጠን ያላደረሱ ሰዎች እድሜ በልደት ጊዜ በሚከናወን ምዝገባ፣ ሰነድ ከሌለም በፍ/ቤት በፀደቀ ጽሁፍ /Acts of notoriety/ ሊረጋገጥ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 200 ሰፍሯል፡፡ በምዝገባ ሰነድ ወይም በጽሁፍ ላይ ክርክር ሲያጋጥም ጉዳዩ በምን መልክ መፍትሔ እንደሚያገኝ ከቁጥር /201 - 203/ ባሉት ድንጋጌዎች በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ የጋብቻንም ሆነ የልደትን ጉዳይ በፍ/ቤት በተረጋገጠ ጽሁፍ ለማረጋገጥ እንዲቻል የሰፈሩት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት የሌላቸው በመሆኑና በዕድሜ ላይ የሚነሳውን ክርክር ለመወሰን የተደነገጉት ሥርዓቶች በተንዛዛ ሁኔታ የተቀረፁ በመሆናቸው ከቁጥር 200-203 የተዘረዘሩትን ጉዳዮችን በማሻሻል በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 217 እና 218 እንዲጠቃለሉ ተደርጓል፡፡

www.abyssinialaw.com

የቤተሰብ ሕጉን በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ ልደት፣ ጋብቻ፣ ፍቺና ሞትን የሚመዘግብ ተቋም ማቋቋም ያስፈልጋል፡፡ አካለ መጠን ያልደረሰ ሰው ዕድሜ ሊረጋገጥ የሚገባው በክብር መዝገብ ሹም ጽ/ቤት በሚደረግ ምዝገባና የልደት የምስክር ወረቀት ይሆናል፡፡

የአንድ ሰው ዕድሜ በክብር መዝገብ ሹም ጽ/ቤት ሳይመዘገብ በመቅረቱ ወይም በሌሎች ምክንያቶች በልደት የምስክር ወረቀት ማረጋገጥ የማይቻልበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡

እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ሲያጋጥም አሳማኝነት በሚኖራቸው ሰነዶች /የክትባት ወረቀት፣ የጥምቀት ማስረጃ፣ የቀበሌ መታወቂያ፣ የትምህርትና ሌሎች አሳማኝ ማስረጃዎች / ዕድሜ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

በሌላ በኩል የአንድን ሰው ዕድሜ በሰነድ ማረጋገጥ የማይቻል ሆኖ ሲገኝ በምስክር የሚረጋገጥበት ሁኔታ ሊከለከል አይገባም ሆኖም በሰነዶችም ሆነ በምስክሮች ብቃት ላይ ክርክር ሊነሳ የሚቻልባቸው በርካታ ምክንያቶች በመኖራቸው አወዛጋቢ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ከልደት የምስክር ወረቀት ውጭ ዕድሜን በፍ/ቤት በኩል እንዲረጋገጥ ማድረግ ይኖርበታል ዕድሜን በተመለከተ ከላይ በተጠቀሱት አማራጮች ብቻ ማረጋገጥ የሚቻል መሆኑን በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 217 የተደነገገ ሲሆን ከዕድሜ ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ክርክሮችን ለመወሰን ለልጆች ደህንነትና መልካም አስተዳደግ የሚበጁ መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚገባ በአንቀጽ 218 ተመልክቷል፡፡

## ክፍል 2

## እካለ መጠን ያልደረሰን ሰው ስለሚጠብቁ ተቋሞች

### ንዑስ ክፍል 1 ስለአሳዳሪና ስለሞግዚት

በዚህ ክፍል የተመለከቱት ድንጋጌዎች በፍ/ብ/ሕጉ ከቁጥር /204 - 264/ የሰፈሩትን የሚመለከት ሲሆን አካለመጠን ያልደረሰ ሰው አስተዳደግና አኗኗር እንዲሁም የንብረት ግንኙነት የሚወከልበትን /የሚጠበቅበትን/ ሕጋዊ ሥርዓት የሚያጠቃልል ነው፡፡

### አንቀጽ 219 የወላጆች ስልጣን

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 204 መሠረት አባትና እናት አካለመጠን ያልደረሱ ልጆቻቸውን የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት ሥልጣን በአንድነት የሚኖራቸው ጋብቻው ፀንቶ አብረው በሚኖሩበት ጊዜ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ አባትና እናት በፀና ጋብቻ የተሳሰሩ መሆናቸው እየታወቀ በልዩ ልዩ ምክንያት አብረው የማይኖሩበት አጋጣሚ ሊኖር የሚችል በመሆኑና በእንግሊዘኛው ቅጂ አብረው ለማይኖሩበት ሀረግ ያልተካተተ መሆኑን በመገንዘብ ይኸው ሀረግ እንዲወጣ በማድረግ ሌላው በቀጥታ ተወስዶ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 219 እንዲሰፍር ተደርጓል፡፡

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ 220 ወላጆች የአሳዳሪነትና የሞግዝትነት ብቃት ስለሚያጡበት ሁኔታ

በፍ/ብ/ሕጉ ቁጥር 205 አንደኛው ወላጅ የአሳዳሪነቱን ሥልጣን ስለሚይዝበት ሁኔታ የሰፈረው ድንጋጌ በርዕሱ ላይ የአንዱ 'አለመገኘት' የሚለው ቃል 'የአንዱ ብቁ አለመሆን' በሚል አገላለጽ ከመለወጡ በቀር ድንጋጌው በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 220 ተካትቷል፡፡

በፍቺ ጊዜ የልጁ አሳዳሪና ሞግዚት የሚመረጠው በቤተዘመድ ሽምግልና ዳኞች እንደሆነ በፍ/ብ/ሕጉ ቁጥር 206 ተመልክቷል፡፡ በቤተሰብ ሕግ የፍቺ ምክንያቶችና የአፈጻጸሙ ከፍ/ብ/ሕጉ በተለየ አኳኋን የተደነገገ በመሆኑና የቤተዘመድ ሽምግልና ጉባኤ ሚና ከእርቅ ጋር በተያያዘ ጉዳይ ላይ ብቻ የተገደበ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 206 በሰፈረው ድንጋጌ ላይ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡

በቤተሰብ ሕጉ በምዕራፍ 4 ሥር በተለይም ፍቺ በተጋቢዎች ስምምነት ወይም በአንደኛው ተጋቢ ወይም በሁለቱ በሚቀርብ ጥያቄ በፍ/ቤት በኩል ሊፈፀም እንደሚቻል ተደንግጓል፡፡ የፍቺ ጥያቄ ለፍ/ቤት ቀርቦ ከታዬ በኋላ ፍ/ቤቱ የፍቺ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ስለልጆቻቸው አጠባበቅ ስለአኗኗራቸውና ስለንብረታቸው አስተዳደር ተገቢውን ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

ጋብቻው በተጋቢዎች ስምምነት በፍቺ የሚፈርስ ከሆነ የልጁን ሞግዚትና አስተዳዳሪ እንዲሁ በስምምነት ሊወሰኑ ይገባል፡፡ ሁለቱም ተጋቢዎች ሳይስማሙ ቢቀሩ ጉዳዩ በፍ/ቤት በኩል ሊወሰን የሚገባው በመሆኑ የፍ/ብ/ሕግ የቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 221 በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 206 ከሰፈረው በተለየ ሁኔታ ተደንግጓል፡፡

አንቀጽ /221 - 223/ የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት ሥልጣን ስለመወሰን

አካለ መጠን ላልደረሰ ልጅ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት በኑዛዜ ሊመረጥ ወይም ቀሪ ሊሆን ስለሚችልበት ሁኔታ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 207፣ 208 እና 209 የሰፈሩት ድንጋጌዎች ማሻሻያ የማያስፈልጋቸው በመሆኑ በቤተሰብ ሕጉ ከአንቀጽ /221 - 223/ ባሉት ድንጋጌዎች እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

አንቀጽ /223 - 229/ የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት ሥልጣን ሊሰጣቸው ሰለሚገባ ሰዎች አመራረጥና ቅደምተከተል

ከልጁ እናትና አባት ውጭ የሞግዚትነትና አሳዳሪነት ሥልጣን ሊይዙ የሚገባቸው ሰዎች በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 210 በቅደም ተከተል ተዘርዝረዋል፡፡ ድንጋጌው በአባትና በእናት ወገን ልዩነት ያደርጋል፡፡ አካለ መጠን ላልደረሰ ልጁ በአሳዳሪነት ወይም በሞግዚትነት ሊመረጡ የሚገባቸው ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች፣ እንዲሁም አጉትና አክስት መሆናቸውን ማመልከት በቂ በመሆኑ በወንድና በሴት አያት ወገን የተቀመጠው ቅደም ተከተል እንዲሰፍር አልተደረገም፡፡ በሌላ በኩል አካለመጠን የደረሱ የልጁ ወንድምና እህቶች ይህንኑ ስልጣን ከመያዝ የሚከለክላቸው ምክንያት ባለመኖሩ የልጁ ወላጆች በሌሉ ጊዜ የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥልጣን ሊሰጣቸው እንደሚገባ ታምኖበታል፡፡ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 210 ድንጋጌ ተሻሽሎ በቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 224 ሰፍሯል፡፡

www.abyssinialaw.com

የልጁን አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ለመምረጥ በቀደምትነት የልጁ ጥቅም መታየት ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም በምዕራፍ 12 በክፍል 1 በጠቅላላ ድንጋጌዎች ሥር ውሳኔ ሰጭ አካላት የሚሰጡት ውሳኔ ለልጆች ደህንነትና መልካም አስተዳደግ በሚጠቅም መልኩ መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚገባ የሰፈረው ድንጋጌ በዚህ ረገድም ተፈፃሚነት ስለሚኖረው በድንጋጌው የሰፈረው ቅደም ተከተል በአስገዳጅነት ሊወሰድ የሚችል አይደለም፡፡

የልጁን ጥቅምና ደህንነት ለማስጠበቅ የሚያስችል ምክንያት ሲያጋጥም በአሳዳሪነትና ሞግዚትነት ሊመረጡ ከሚችሉት ሰዎች ውጭ ያሉ የልጁ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመዶች በሚያቀርቡት ጥያቄ መነሻነት ቅደም ተከተሉ ሊለወጥ የሚችልበት ሁኔታ መኖሩን የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 221 ያመለክታል፡፡ ጥያቄው በመጀመሪያ የሚታየውና ውሳኔ የሚያገኘው በቤተዘመድ ጉባኤ እንደሆነ የሚደነግገው ቃል ተፈፃሚነት ስለሌለው እንዲወጣ ተደርጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ጥያቄው ለባለጥቅሞቹ መቅረብ እንደሚገባ የተመለከተ ቢሆንም ባለጥቅሞቹ ቅደም ተከተሉ የሚመለከታቸው ሰዎች በመሆናቸው የአገላለጽ ለውጥ በማድረግ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 225 እንዲካተት ተደርጓል፡፡ ለልጁ አሳዳሪና ሞግዚት መሆን የሚችሉ ዘመዶች ያለመኖራቸው ሲረጋገጥ በፍ/ቤት በኩል ሊመረጡ ስለሚችሉበት ሁኔታ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 212 የሰፈረው ድንጋጌ ማሻሻያ ሳያስፈልገው የቃላት ለውጥ በማድረግ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 226 ተካትቷል፡፡

አካለመጠን ላልደረሱ ልጆች ከሥጋ ወይም ከጋብቻ ዘመዶቹ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት የሚሆን ሰው በፍ/ቤት ስለሚመረጥበት ሁኔታ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 213 የተመለከተው ድንጋጌ፣ ለበጐ አድራጐት ድርጅት የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ስልጣን በፍ/ቤት በኩል ሊሰጠው የሚችል ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 214 የሰፈረው ድንጋጌ ማሻሻያ ሳያስፈልጋቸው በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 227 እና 228 እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

በሌላ በኩል በሕጋዊ ወይም በሌሎች ምክንያቶች አሳዳሪ ወይም ሞግዚት የሆነው ሰው ይህንኑ ሥራውን ለማከናወን ያለመቻሉ ሲረጋገጥ እንደሞተ የሚገመት መሆኑን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 215 ተመልክቷል፡፡

አንድ ሰው በሕግ ግምት ሞቷል ለማለት የሚቻለው በመጥፋቱ ምክንያት የመጥፋቱ ውሳኔ እንዲሰጥ ለፍ/ቤት ቀርቦ በመታየት ላይ እያለ የቀረቡት ማስረጃዎች መሞቱን የሚያረጋግጡ መሆናቸው ሲታወቅ እንደሆነ የፍ/ብ/ሕጉ ቁጥር 161 በግልጽ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ውጭ የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥልጣኑን ለመወጣት የማያስችሉ ሌሎች ምክንያቶች ሊኖሩ የሚችሉ በመሆናቸውና በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 215 የሰፈረው የሕግ ግምት ሰውየው ያለመኖሩን ወይም የሌለ መሆኑን ለማመልከት የተፈለገ በመሆኑ በዚህ አኳኋን ማሻሻያ በማድረግ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 229 ተካትቷል፡፡

<u>አንቀጽ /230 - 234/ ስለሞግዚት አመራረጥ</u>

የአሳዳሪነት ሥልጣን የተሰጠው ሰው የሞግዚትነት ሥልጣን ያለው ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 216 የሰፈረው ድንጋጌ፣ አባትና የእናት የአሳዳሪነቱን ስልጣን ይዘው ሞግዚት ለመሾም የሚችሉ ሰለመሆናቸው በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 217 የተመለከተው

www.abyssinialaw.com

ሁኔታ፣ የልጁ አሳዳሪና ሞግዚት በፍርድ ቤት በሚመረጥበት ጊዜ አሳዳሪውና ሞግዚቱ የተለያዩ ሰዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ በፍ/ብ/ሕግ 218 የተመለከተው ድንጋጌ፣ በቁጥር 217 የሞግዚትን ብዛት በተመለከተ አንድ የሚለውን ቃል እንዲሰረዝ ከማድረግ በስተቀር ሌሎች ማሻሻያ ሳያስፈልጋቸው በቤተሰብ ሕጉ ከአንቀጽ /230 - 232/ ባሉት ድንጋጌዎች እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡

አካለ መጠን ላልደረሰ ልጅ በሞግዚትነት ወይም በአሳዳሪነት ሊመረጡ ወይም ሊሾሙ የሚችሉ ሰዎችን ማንነትና በምን ሁኔታ እንደሚመረጡ በቅደም ተከተል ሕጉ ያመለከተ በመሆኑና ተጨማሪ ሞግዚት ማድረግ የሚከለክል ሁኔታ ባለመኖሩ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 219 ተጨማሪ ሞግዚት በሚል የሰፈረው ድንጋጌ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

አካለ መጠን ባልደረሰው ልጁና በሞግዚቱ መካከል የጥቅም ግጭት ሲፈጠር ምትክ ሞግዚት በፍ/ቤት በኩል ሊመረጥ የሚችል ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 220 የሰፈረው ድንጋጌ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 233 እንዲካተት የተደረገ ሲሆን ይህንን ጥያቄ የቤተዘመድ ምክር ጉባኤ እንዲያቀርብ በሚደነግገው ክፍል ላይ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡ የቤተዘመድ ጉባኤ በተቋምነቱ ሊቀጥል አንደማይገባ በሌሎች ጉዳዮች ላይ አቋም የተወሰደ በመሆኑ የምክር ጉባኤ አባላት ሊሆኑ የሚችሉ ወገኖችን ዝርዝር በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 241 የሰፈረውን በመውሰድ ምትክ ሞግዚት እንዲሾም ጥያቄ የማቅረቡ መብት በዝርዝር ለተመለከቱት ሰዎች የተሰጠ መሆኑን በሚያመለክት አገላለጽ ተደንግጓል፡፡

አካለመጠን ያልደረሱት ከአንድ በላይ የሆኑ ልጆች በአንድ ሞግዚት በሚወከሉበት ጊዜ የጥቅም ግጭት ሲፈጠር ምትክ ሞግዚት መምረጥ ስለሚቻልበት ሁኔታ በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 221 የሰፈረውን ድንጋጌ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 234 ተወስዷል፡፡

## <u>አንቀጽ 235 - 237/ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ስለሚኖርበት ግዴታና ግዴታው ስለሚቀርበት ሁኔታ</u>

የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት ሥልጣንና ሥራ ስለሚጀመርበትና ስለሚቋረጥበት መንገድ፣ እንዲሁም ይኸው ሥልጣን እስካልተሻረ ወይም እስካልተለወጠ ድረስ ሥራውን በገዛ ፈቃዱ ማቋረጥ እንደማቻል በፍ/ብ/ሕጉ ከቁጥር /221-223/ ባሉት ድንጋጌዎች ላይ መጠነኛ የቃላት ማስተካከያዎች ከመደረጉ በስተቀር የጽንሰሃሳብ ማሻሻያ ሳያስፈልጋቸው በቤተሰብ ሕጉ ከአንቀጽ /234 - 236/ ባሉት ድንጋጌዎች እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥልጣን እንዲቀር ጥያቄ ስለሚቀርብበት ሁኔታ በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 224/1/ የሰፈረው ድንጋጌ የአገላለጽ ችግር የሚታይበት ሲሆን በአማርኛውና በእንግሊዘኛው ቅጂ መካከል ልዩነት በመኖሩ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡ የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥልጣኑን ለማከናወን የማያስችሉ ከበድ ያሉ ችግሮች ሲያጋጥሙ ችግሩም በኑሮ ላይ እንቅፋት የሚያስከትል ከሆነ ይህንኑ በመግለጽ ሥልጣኑ እንዲቀር ለፍ/ቤት ጥያቄ ማቅረብ እንደሚቻል የእንግሊዘኛው ቅጂ በግልጽ የሚያመለክት በመሆኑ ድንጋጌው በዚህ መልክ ተሻሽሎ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 238/1/ ሰፍሯል፡፡

www.abyssinialaw.com

## አንቀጽ 238 የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥልጣን ለማከናወን ስለማይችሉ ሰዎች

የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራ የልጆችን የዕለት ከዕለት አኗኗር፣ ጤና፣ ትምህርትና የኢኮኖሚ አቋም እንዲሁም ሥነ ምግባር መከታተልና ቁጥጥር ማድረግ የሚጠይቅ በመሆኑ ይህንኑ አብይ ተግባር ለማከናወን የማያስችሉ ሁኔታዎች ሊያጋጥሙ ይችላሉ:: የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራ እንዳይዙ በሕግ ስለተፈቀደላቸው ሰዎች የፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 225 ከሰፈረው ዝርዝር መካከል ዕድሜው ስልሳ አምስት ዓመት የሞላው ሰው አካለመጠን፣ ያልደረሱ አራት ልጆች ያለው ሰው፣ እንዲሁም በሥራ ላይ ያለ ወታደር በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 238 በቀጥታ እንዲካተቱ ተደርጓል::

በሌላ በኩል ሴቶች የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራ ለማከናወን እንደማይችሉ በፍ/ብ/ሕጉ የሰፈረውን ድንጋጌ የእኩልነትን መርህ የማያስጠብቅ በመሆኑ ተሰርዟል::

## አንቀጽ 239 ሥልጣኑ ቀሪ እንዲሆን የተደረገ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ስላለበት ኃላፊነት

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 226/1/ የሞግዚትነት ሥልጣኑ የተሻረ ወይም ተቃውሞ ያቀረበ ሰው ምትክ ሞግዚት እስኪሾም ድረስ ሥራውን የማከናወን ግዴታ እንዳለበት ተደንግጓል:: በዚህ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር /2/ ሞግዚትነቱ በሹመት የተሰጠው ሰው ተመሣሣይ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን የሚያመለክት ሲሆን ድንጋጌው ማሻሻያ ሳያስፈልገው በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 239/1/ ተወስዷል::

አንድ ሰው የሞግዚትነት ሥልጣን ከሚያገኝባቸው መንገዶች አንዱ በሹመት እንደሆነ የሚታወቅ በመሆኑና በንዑስ ቁጥር 1 በሰፈረው ድንጋጌ የሚሸፈን ስለሆነ ንዑስ ቁጥር 2 ትርጉም የሚሰጥ አይደለም:: ይሁን እንጂ የንዑስ ቁጥር 2 የእንግሊዘኛው ቅጂ ከአማርኛው በተለየ አገላለጽ የተቀመጠ ሲሆን ምትክ ሞግዚት እስኪሾም ድረስ በስልጣኑ ላይ ተቃውሞ የቀረበበት ሞግዚት ሥራውን ማቋረጥ እንደሌለበት ያመለክታል:: በመሆኑም በእንግሊዘኛው ቅጂ የሰፈረው አገላለጽ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 239/2/ ተካትቷል::

የሞግዚት አስተዳደር ቀሪ ስለሚሆንበት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 227፣ ችሎታ የሌለው ሰው የሞግዚትነት ሥልጣን የማይሰጠው ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 228፣ በፍርድ የተከለከሉ ሰዎች የሞግዚትነት ሥልጣን ለማከናወን የማይችሉ ስለመሆናቸው በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 229 የወንጀል ተግባር ፈጽሞ የግል ነፃነትን የሚያሳጣ ቅጣት የተላለፈበት ሰው የሞግዚት ሥራ ለመፈፀም ብቃት የሌለው ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 230፣ በአስተዳደርና በአያያዝ ጉድለት የአሳዳሪነት ስልጣን በፍ/ቤት ስለሚሻርበት ሁኔታ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 231፣ የንብረት አስተዳደር ጉድለት በመፈፀም የሞግዚትነት ሥልጣን ስለሚሻርበት ሁኔታ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 232፣ የተመለከቱት ድንጋጌዎች የጽንሰሃሳብ ለውጥ ወይም ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸው ሆኖ ባለመገኘቱ መጠነኛ የቃላት ማስተካከያ ተደርጎባቸው በቤተሰብ ሕጉ ከአንቀጽ /240 - 245/ በቀጥታ ተካተዋል::

የአሳዳሪቱ ወይም የሞግዚትነቱ ሥራ በሹመት ተየሰጠው አሳዳሪና ሞግዚት ሌላ ሰው ተተክቶ ሥልጣኑን እስኪረከበው ድረስ የተሰጠውን ሥራ በጊዜው የማከናወን

www.abyssinialaw.com

ግዴታ እዳለበት የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 226/2/ ይደነግጋል፡፡ ሆኖም የእንግሊዘኛው ቅጂ አገላለጽ ከላይ በተለየ መልኩ የሰፈረ ሲሆን ድንጋጌው በሹመት ላይ ተቃውሞ የተነሳበትን አሳዳሪ ወይም ሞግዚት እንደሚመለከት በግልጽ ተመልክቷል፡፡

ስለሆነም በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 226/1/ ከሰፈረው ድንጋጌ አገላለጽ ጋር አግባብነት የሚኖረው የእንግሊዘኛው ቅጂ በመሆኑ በንዑስ ቁጥር /2/ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡

የወንጀል አድራጐት ፈጽሞ የተቀጣ ሰው ለሞግዚትነት ወይም ለአሳደሪነት ሥራ ተገቢ እንዳልሆነ በፍ/ብ/ ሕጉ ቁጥር 230 የሰፈረው አርዕስት ብቁ ያለመሆን በሚል ተሻሽሎ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 243 ተወስዷል፡፡

የልጁ እናትና አባት ወይም የቤተዘመድ ጉባኤ አማካሪዎች የሰጡትን ደንብና የንብረት አስተዳደር ሥርዓት ሳይፈጽም የቀረ ሞግዚት በፍ/ቤት ውሳኔ ሊሻር የሚችል ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 232 ተመልክቷል፡፡ የቤተዘመድ ጉባኤ በቤተሰብ ሕጉ እንዲካተት ያልተደረገ ሲሆን ልጁን በሞግዚትነት ለማስተዳደር ሥልጣን የሚሰጡት ሰዎች ከእናትና አባት በተጨማሪ ሌሎች በመኖራቸው ምክንያት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 232 'ሥልጣን የተሰጠው ሰው' የሚል ማሻሻያ ታክሎበት ድንጋጌው በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 245 እንዲካተት ተደርጓል፡፡

ወላጆች ከአሳዳሪነት ወይም ከሞግዚትነት ስለሚሻሩበት ሁኔታ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 233 የሰፈረው ድንጋጌ ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆችን የሚያመለክት መሆኑን ከመግለጽ በስተቀር ማሻሻያ ሳያስፈልገው በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 246 ተወስዷል፡፡

የሥጋ እና የጋብቻ ዝምድና በእነማን መካከል ያለ ስለመሆኑ በቤተሰብ ሕጉ በዝርዝር የተመለከተ ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 234/1/ በሥጋ እና የጋብቻ ዘመዶች አማካኝነት አሳዳሪ ወይም ሞግዚት እንዲሻር ጥያቄ ሊቀርብ እንደሚችል በሰፈረው ድንጋጌ ላይ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 247/1/ ሞግዚት ወይም አሳዳሪ እንዲሻር ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው በማንኛውም ያገባኛል በሚል ሰው እንደሆነ በሚያመለክት አገላለጽ ተተክቷል፡፡

የአሳደሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥልጣን እንዲሻር ከመወሰኑ በፊት ፍ/ቤቱ የሚሽረውን ሰው አስተያየት ሊጠይቅ እንደሚገባና ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ስለሚወሰድ የጥንቃቄ ርምጃ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 234/2/ የሰፈረው ድንጋጌ በሁለት ንዑስ አንቀጾች ተለይተው መስፈር ስላለባቸው መጠነኛ የቃላት ለውጦችን በማድረግ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 247/2/ እና /3/ በቅደም ተከተል እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 234/3/ ምትክ ሞግዚት ስለሚሾምበት ሁኔታ የሰፈረው ድንጋጌ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 248/3/ የሚሸፈን በመሆኑ ተሰርዟል፡፡

የቤተዘመድ ጉባኤ በተቋምነት የሚቀጥል ባለመሆኑ አካለመጠን ላልደረሰ ልጅ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ሲሾምም ሆነ ሲሻር ፍ/ቤቱ የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥልጣን ሊሰጣቸው የሚችሉትን ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆችና አካለመጠን የደረሱ ወንድምና እህቶችን ምክር መጠየቅ እንደሚኖርበት በማመልከት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 235/1/ የሰፈረው ድንጋጌ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 248/1/ ሰፍሯል፡፡

ፍ/ቤቱ አካለመጠን ያላደረሰውን ልጅ ሀሳብ እንደአስፈላጊነቱ ሊሰማ እንደሚችልና ፍ/ቤቱ የልጁን ጥቅም በሚያስጠብቅ ሁኔታ ውሳኔ መስጠት እንደሚገባ በፍ/ብ/ሕግ

www.abyssinialaw.com

ቁጥር 235 /3/ የሰፈሩት ድንጋጌዎች ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸው ባለመሆኑ ባሉበት እንዲወሰዱ ተደርጓል፡፡ በመርህ ደረጃ አሳዳሪነት ወይም ሞግዚትነት በነፃ ሊከናወን እንደሚገባ የሚታመን ቢሆንም ሥራው ረጅም ጊዜ የሚፈጅ ከሆነ የተወሰነ ጊዜና ጉልበትን የሚጠይቅ አገልግሎት እንደሆነ ይታወቃል፡፡

በመሆኑም አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ ጋር የሥጋም ሆነ የጋብቻ ግንኙነት ኖረም አልኖረም የአበል ክፍያ እንደሚጠየቅ ከታመነበት በተመሣሣይ አኳኋን መታየት የሚገባው ጉዳይ ነው በዚህም ረገድ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 236/2/ የሰፈረው ድንጋጌ ማሻሻያ ተደርጐበት በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 249/2/ ሥር እንዲሰፍር ተደርጓል፡፡

በሌላ በኩል የአበል አከፋፈሉ ምቹ በሆነ መንገድና ጊዜ ሊጠየቅና ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባው ጉዳይ በመሆኑ በዓመት እንደሚከፈል በንዑስ ቁጥር /3/ የሰፈረው ድንጋጌ በቤተሰብ ሕጉ አልተወሰደም፡፡ ስለአበሉ መጠን የተመለከተው ሁኔታ ማሻሻያ የሚያስፈልገው ባለመሆኑ ባለበት እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡ የአሳደሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራ ለወራሾች የማይተላለፍ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁ.237/የአሳደሪው ወይም የሞግዚቱ ወራሾች ስላላቸው ግዴታ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 238፣ የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥልጣን ስለመኖሩ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከዳኞች ሊጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁ.239/1/ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ማሻሻያ የሚያሰፈልጋቸው ባለመሆኑ በቤተሰብ ሕጉ በአንቀጽ 251 እና 252 ተካትተዋል፡፡ የአሳደሪነት ወይም የሞግዚትነት ማስረጃ በውል ቤት የሚሰጥበት አሰራር ባለመኖሩ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 239/2/ የሰፈረው ድንጋጌ ተሰርዟል፡፡

ተጨማሪ ሞግዚትን በተመለከተ በፍ/ብ/ሕጉ የሰፈረው ድንጋጌ በቤተሰብ ሕጉ እንዲካተት ባለመደረጉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 240 የተመለከተው ምትክ ሞግዚትን ብቻ እንደሚመለከት ተጠቅሶ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 253 ተወስዷል፡፡

የቤተዘመድ ምክር ጉባኤም ሆነ ተጠባባቂ ሞግዚት በፍትሐብሔር ሕጉ በተመለከተው አኳኋን በተቋምነት ሊቀጥሉ እንደማይገባ ስለታመነበት በምዕራፍ 2 ንዑስ ክፍል 2 ከቁጥር /241-264/ የሰፈሩት ድንጋጌዎች እንዲወጡ ተደርጓል፡፡

## ክፍል 3

## የአሳዳሪውና የሞግዚቱ ሥልጣን

### ንዑስ ክፍል 1 አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ አስተዳደግና ጥበቃ

የአሳዳሪው ተግባር አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ አስተዳደግና ጥበቃ መከታተልና መቆጣጠር በመሆኑ ስለልጁ 'ሰውነት አጠባበቅ' የሚለው ቃል ተሻሽሏል፡፡

www.abyssinialaw.com

አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰውን ልጁ አስተዳደግና ጥበቃ ሥራ በሚያከናውንበት ጊዜ ልጁ ከአሳዳሪው ፈቃድ ውጭ ለመልካም አስተዳደግ ተቃራኒ በሆነ ሁኔታ ከመኖሪያ ቦታው በሚርቅበት ጊዜ ወይም የዕጽም ሆነ የሌላ አደገኛ ሱስ ተጠቃሚ ሲሆን አግባብነት ያላቸውን የመንግስት ተቋማትን እገዛ ማግኘት እንደሚገባ ታምኖበታል። በመሆኑም አሳዳሪው የመንግስት ተቋማትን እገዛ መጠየቅ እንደሚችል የሚደነግግ ሁኔታ በቤተሰብ  ሕጉ አንቀጽ 254 እንዲካተት ተደርጓል።

አካለመጠን ያላደረሰውን ልጅ መኖሪያ ቦታ አወሳሰን በተመለከተ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 265 የተመለከተው ድንጋጌ እንዲሁም የልጁን ጤና አጠባበቅ በሚመለከት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 266 የሰፈረው ሁኔታ ከአገላለጽ ለውጥ በቀር ማሻሻያ ሳያስፈልጋቸው በብተሰብ ሕጉ አንቀጽ 255 እና 256 ተካተዋል።

አሳዳሪው የልጁን መልካም አስተዳደግ ለመምራትና ለመቆጣጠር እንዲቻለው የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 267/2/ ቀላል የሰውነት ቅጣቶችን መፈፀም ይፈቅዳል።

የሰውነት ቅጣት መፈፀም እንደሚቻል መደንገጉ በመርህ ደረጃ ተቀባይነት የሚኖረው አስተሳሰብ አይደለም በአንፃሩ አሳዳጊው የልጁን መልካም አስተዳዳግ ለመምራት ቁጥጥር ማድረግ እንደሚኖርበት ይታመናል። በዚህም ረገድ የሚደረግ ቁጥርና ክትትል ተገቢ የሆነ የዲሲፕሊን ርምጃ መውሰዱን ሊያጠቃልል እንደሚገባ ታመኖበት የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 267/2/ ማሻሻያ ታክሎበት ድንጋጌው በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 257 ተወስዷል።

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 268 አካለመጠን ስላልደረሰው ልጅ ግንኙነትና ደብዳቤ የሚመለከተው ድንጋጌ የልጁን ማህበራዊ ግንኙነት የሚያጠቃልል በመሆኑ ድንጋጌው በዚህ አገላለጽ ተስተካክሎ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 258 ተካትቷል።

አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ጠቅላላ ትምህርትና የሞያ ሥልጠና እንዲያገኝ የማድረግ ግዴታ እንደሚኖርበት የፍ/ብ/ሕጉ አንቀጽ 269/1/ ይደነግጋል። ይኸው ድንጋጌ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 259 ተወስዷል። ይህንኑ ትምህርት ለማግኘት የሚያስችለው ውል እንዲያደርግ ንዑስ ቁጥር /2/ የሚጠይቅ ቢሆንም ከላይ በንዑስ ቁጥር /1/ የሚሸፈነን በመሆኑ እንዲሰረዝ ተደርጓል።

አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ከሚያገኘው ገቢ ለልጁ አስተዳደግ ተገቢ የሆነውን መጠን ተቀብሎ ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚችልና መግለጫ ለመስጠት እንደማይገደድ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 270 የሰፈረውን ድንጋጌ ማሻሻያ ሳያስፈልገው በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 260 ተወስዷል።

የልጁ አሳዳሪ ከአባትና እናት ውጭ በሚሆንበት ጊዜ ለልጁ አስተዳደግ የሚበቃውን የገንዘብ መጠንም ሆነ አከፋፈሉን በተመለከተ የቤተዘመድ ጉባኤ እንደሚወስን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 271 ተመልክቷል።

ይሁን እንጂ የቤተዘመድ ጉባኤ በቤተሰብ ሕጉ ያልተካተተ በመሆኑ እንዲህ ዓይነቱ ጉዳይ በፍ/ቤት በኩል ታይቶ እንደሚወሰን በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 261 ሰፍሯል። ፍ/ቤቱ ሊከፍል የሚገባውን የገንዘብ መጠንና ጊዜ አብሮ እንደሚወስን ተመልክቷል።

አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ዝቅተኛው የሥራ ቅጥር ዕድሜ 14 እንደሆነ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕግ የተደነገገ በመሆኑ በሥራው ውጤት የተገኘ ገቢን በተመለከተ

www.abyssinialaw.com

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 272 የተመለከተው ድንጋጌ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 262 የተወሰደ ሲሆን ለአሳዳሪው ሊሰጥ ከሚገባው ውጭ ያለውን ተራፊ ገንዘብ ለዕለት ጉዳይ ሥራዎች ወጪ ማድረግና መገልገል የሚችልበት ሁኔታ የሚፈቀድ በመሆኑ በሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ሊጠቀምበት እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡

አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ በኑዛዜም ሆነ ያለኑዛዜ ንብረት በውርስ ሊያገኝ የሚችል በመሆኑ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 273 ከዚህ አኳያ ተሻሽሎ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 263 ተወስዷል፡፡

አሳዳሪው አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ ኑሮ አስፈላጊ ለሆነ ወጪ ከልጁ ገቢ የተወሰነ መጠን መጠቀም የሚችል በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 274/1/ አሳዳሪው አካለመጠን ያላደረሰውን ልጅ የሀብት ገቢ ለሌላ ሰው ሊያስተላልፍ ወይም ውል ሊገባላቸው እንደማይችል መደንገጉ የአፈፃፀም ችግር የሚያስከትል ከመሆኑም በተጨማሪ የእንግሊዘኛው ቅጂ ከዚህ በተለየ አገላለጽ ወደፊት ገቢ የሚሆነውን የሚያመለክት በመሆኑ የእንግሊዘኛው ቅጂ አግባብነት ያለው በመሆኑ ተወስዷል፡፡ በዚህም መሠረት አሳዳሪው ግዴታ ሊገባ የማይችለው ባልደረሱ ገቢዎች ላይ እንደሆነ ተገልጾ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 264 ተሻሽሎ ተደንግጓል፡፡

ከአሳዳሪው ላይ ገንዘብ የሚጠይቁ ሰዎች አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ ገቢ ሊጠ ይቁ የማይችሉ ስለመሆናቸው በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 274/2/ የሰፈረው ድንጋጌ ግልፁን ነገር መግለፅ በመሆኑ ባለበት እንዲቀጥል ማድረጉ የሚያስገኘው ጠቀሜታ ባለመኖሩ እንዲሰረዝ ተደርጓል፡፡

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 275 አባትነትን ስለማወቅ የሰፈረው ድንጋጌ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 134 የተካተተ በመሆኑ ተሰርዟል፡፡

አካለመጠን ላልደረሰ ልጅ አባትና እናት የአሳዳሪነት ሥልጣን በጋራ እንደሚኖራቸው በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 219 የተደነገገ ሲሆን የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 275 በዚህ አኳኃን ማሻሻያ ተደርጐበት አባትና እናት የአሳዳሪነቱን ሥራ በመመካከርና በመግባባት ሊያከናውኑ እንደሚገባ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 265/1/ ተመልክቷል፡፡ በሁለቱ መካከል አለመግባባት የሚፈጠር ቢሆን ጉዳዩ ለቤተዘመድ ዳኞች ታይቶ ውሳኔ እንደሚሰጥ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 277 ይደነግጋል፡፡

በአባትና እናት መካከል የተፈጠረው ያለመግባባት ውጤት የማያስገኝ ከሆነ በሽምግልና መታየቱ ጠቀሜታ ሊኖረው የሚችል ቢሆንም ሽምግልናው ውጤት ካላስገኘ ጉዳዩ በፍ/ቤት ታይቶ ሊወሰን የሚገባ መሆኑ ተጠቅሶ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 277/1/ የሰፈረው ድንጋጌ ተሻሽሎ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 265/2/ ተካቷል፡፡

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 278 ለቤተዘመድ ምክር ጉባኤ ስለሚቀርብ አቤቱታ የሰፈረው ድንጋጌ በጉባኤው ላይ በተወሰደው አቋም መሠረት እንዲካተት አልተደረገም፡፡

የልጁ አባትና እናት አሳዳሪ ሆነው በሚሰጡት ውሳኔ ላይ ተቃውሞ ሊቀርብ እንደማይችል የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 279 ይደነግጋል፡፡ ሆኖም አባትና እናት በፍቺ ወይም ሌላ ጋብቻ በመፈፀማቸው ወይም በሌላ ምክንያት ተለይተው በሚኖሩበት ጊዜ አንደኛው ወገን አሳዳሪ ሆኖ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ አቤቱታ ሊቀርብ እንደሚችል በዚሁ ድንጋጌ በፊደል /ሀ/ እና /ለ/ ተመልክቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

በመሆኑም እናትና አባት ከፍቺ ውጭ አብረው ለመኖር የማያስችላቸው ሌሎች ምክንያቶች መኖራቸውን ከግንዛቤ በማስገባት አንደኛው ወገን የሰጠው ውሳኔ ተቃውሞ ሊቀርብበት የሚችለው አባትና እናት ተለያይተው በመኖራቸው ምክንያት የአሳዳሪነቱን ሥራ በጋራ ማከናወን አለመቻላቸው ሲታወቅ መሆኑ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 266 ተደንግጓል።

አሳዳሪነቱ የልጁ ወላጅ ባልሆነ ወገን በሚከናወንበት ጊዜ የልጁን አስተዳደግ በተመለከተ በሚደረግ ውሳኔ ላይ አቤቱታ ወይም ተቃውሞ ለፍ/ቤት ሊቀርብ የሚችልበት ድንጋጌ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 267 እንዲካተት ተደርጓል።

## <u>ንዑስ ክፍል 2</u>

## <u>አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ንብረት ስለማስተዳደር</u>

### <u>አንቀጽ 268 አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ንብረት ነክ በሆኑ ጥቅምች በሞግዚት የሚወከል ስለመሆኑ፣</u>

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 280 ሞግዚቱ በብሔራዊ ሥራዎች አካለመጠን ላልደረሰ ልጅ ወኪል/እንደራሴ/ መሆኑን የተመለከተ ሲሆን በእንግሊዘኛው ቅጂ ሞግዚቱ የፍተሐብሔት ጉዳዩችን እንደሚወክል ይደነግጋል።

ይሁን እንጂ በአሳዳሪው በኩል የሚከናወኑ ሥራዎች የፍትሐብሔር ጉዳዩች እንደመሆናቸው መጠን የሞግዚቱን ሥልጣን በተለየ ሁኔታ በግልጽ መወሰን ያሰፈልጋል።

አካለመጠን ያልደረሰን ልጅ አስተዳደግና አጠባበቅ የሚመለከቱ ሥራዎች በአሳዳሪው የሚከናወን ተግባር ሲሆን ከዚህ ውጭ ንብረቱንና ከገንዘብ ጋር የተያየዙ ጥቅሞችን ለማስተዳደርና ለማስከበር የሚችለው በሞግዚቱ አማካኝነት እንደሆነ ይታወቃል። በመሆኑም ድንጋጌው ይህንኑ በሚያንፀባርቅ ሁኔታ ተሻሽሎ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 268 ተካትቷል።

### <u>አንቀጽ 269 የንብረት ቆጠራና የዋጋ ግምት</u>

ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ሀብትና ንብረት በሚያስተዳድርበት ጊዜ የንብረቱን ዓይነትና ዋጋውን የሚያሳይ ንብረት ቆጠራ ማድረግ እንደሚኖርበት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 281 ተመልክቷል። የንብረት ቆጠራ ሥራውን በጀመረ በአርባ ቀናት ውስጥ እንደሚደረግ የተመለከተ ሲሆን የጊዜ ገደቡ በቂ ሊሆን እንደማይችል በመገመት ወደ ስልሣ ቀናት ከፍ እንዲል ተደርጎ ድንጋጌው በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 269 ተካትቷል።

በሌላ በኩል የንብረት ቆጠራው የሚካሄደው በቤተዘመድ ምክር ጉባኤ የተመረጡ በቂ ምስክሮች ባሉበት እንደሆነ የተመለከተ ቢሆንም የቤተዘመድ ጉባኤ ሚና በቤተሰብ ሕጉ እንዲፀባረቅ ያልተደረገ በመሆኑ የምስክሮች ቁጥር ሶስት እንዲሆንና በአመራር ረገድ ብርቱ ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባ በሚያመለክት አገላለት እንዲሰፍር ተደርጓል።

www.abyssinialaw.com

ሞግዚቱ አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ ሊጠይቀው ስለሚገባ ዕዳ ወይም ንብረት የሰፈረውን ድንጋጌ ባለበት ተወስዷል፡፡

<u>አንቀጽ 270 አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ ስለሚተላለፈ የውርስ ሀብት</u>

ሞግዚቱ አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ የውርስ ሀብት ከመቀበሉ በፊት የንብረቱን ዝርዝርና ዋጋ የሚያሳይ የንብረት ቆጠራ ማድረግ እንደሚኖርበት ከዚሁ ንብረት የሚገባው ድርሻ ካለ ቆጠራው በሚካሄድበት መዝገብ ማሳወቅና ማስመዝገብ እንደሚገባው የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 282 ያመለክታል፡፡

የምስክሮች ቁጥር ተወስኖ ሊቀመጥ የሚገባ በመሆኑ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 271 ቆጠራው ሲካሄድ ከሞግዚቱ ጋር መገኘት የሚገባቸው ሶስት ምስክሮች እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

በሌላ በኩል ሞግዚቱ አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ የውርስ ንብረት የሚጠይቀውን ድርሻ በቆጠራው መዝገብ ማስፈሩ በቂ ስለማይሆን በቆጠራ ወቅት እንዲታወቅ ማድረግ እንደሚኖርበት ተደንግጓል፡፡

በንብረት ቆጠራው ጊዜ ሞግዚቱ ለሚፈጽመው ግድፈት ወይም ስህተት ተጠያቂ እንደሚሆን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 282/3/ የሰፈረው ድንጋጌ የእንግሊዘኛው ቅጂ ከአማርኛው በተለየ አገላለጽ የሰፈረ ሲሆን ሞግዚቱ ተጠያቂ የሚሆነው የቆጠራው ገንዘብ በማይኖርበት ጊዜ እንደሆነ ያመለክታል፡፡

በመሆኑም የሞግዚቱ ተጠያቂነት ቆጠራውን በሚያከናውንበት ጊዜ በተፈጠረ ስህተት ወይም ጉድለት ብቻ ሳይሆን ቆጠራው ሳይከናወን በመቅረቱም ጭምር ሊሆን እንደሚገባ ታምኖበታል የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 282/3/ ማሻሻያ ተደርጎበት በቤተሰብ ሕጉ አንቀት 270/3/ ሰፍሯል፡፡

<u>አንቀጽ 271 የሞግዚቱ ንብረት አካመጠን ካልደረሰው ልጅ ንብረት ጋር ሊቀላቀል የማይገባ ስለመሆኑ</u>

ሞግዚቱ የግል ንብረቱንም ሆነ ጥሬ ገንዘቡን አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ ንብረትና ገንዘብ ጋር መቀላቀል እንደማይኖርበት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 283 የሰፈረው ድንጋጌ ማሻሻያ ሳያስፈልገው በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 271 ተወስዷል፡፡

<u>አንቀጽ 272 የገንዘብ ሰነዶችና ውድ ዕቃዎች ስለሚቀመጡበት ሁኔታ</u>

ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ሀብትና ንብረት በሚያስተዳድርበት ጊዜ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ የሚጠበቅበት በመሆኑ የገንዘብ ሰነዶችን፣ ዋጋ ያላቸውን ዕቃዎችና አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን በተለየ ሁኔታ መያዝ እንደሚገባው የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 284 ይደነግጋል፡፡

ድንጋጌው በአገላለጽ ረገድ ማሻሻያ የሚያስፈልገው በመሆኑ ከእንግሊዘኛው ቅጂ ጋር በማመሳከር ሊጠበቁና ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸው የገንዝብ ሰነዶችና ውድ ዕቃዎች እንዲሁም ጠቃሚነት ያላቸው ጽሁፎች በመሆናቸው አጠባበቁ ሊጠፉ ወይም ሊባክኑ

www.abyssinialaw.com

በማይችሉበት ሁኔታ መሆን እንደሚኖርበት ተገልጾ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 272 ተደንግጓል፡፡

ሞግዚቱ አካለመጠን ያላደረሰውን ልጅ ሀብትና ንብረት ዝርዝር የሚያመለክት የንብረትና የዋጋ መዝገብ ሶስት ምስክሮች ባሉበት ማዘጋጀት እንደሚኖርበት በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 270 የተመለከተ በመሆኑ አባትና እናት ያልሆነ ሞግዚት ሊፈጽም ስለሚገባው ሁኔታ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 285 የተመለከተው ድንጋጌ ተሰርዟል፡፡

<u>አንቀጽ 273 በሞግዚቱ አስተዳደር ላይ ፍ/ቤት ስለሚኖረው ሥልጣን</u>

ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ አባት ወይም እናት በማይሆንበት ጊዜ የቤተዘመድ ምክር ጉባኤ የልጁን ሀብትና ንብረት በመልካም ሁኔታ ለመጠበቅ የሚያስችል ትዕዛዝ መስጠት እንደሚችል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 286 ተመልክቷል፡፡

ለጉባኤው የተሰጠው ስልጣን ለፍ/ቤት ቢተላለፍ የልጁን ጥቅም በበለጠ ሊያስጠብቅ እንደሚችል ታምኖበታል፡፡ በመሆኑም እንዲህ ዓይነቱ መመሪያ ለሞግዚቱ እንዲሰጥ ጥያቄ ለማቅረብ አግባብነት የሚኖራቸው የልጁ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች አካለመጠን ያልደረሱ እህቶችና ወንድሞቹ መሆናቸው ተጠቅሶ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 273/1/ ተደንግጓል፡፡

ፍ/ቤቱ ለሞግዚቱ መመሪያ በሚሰጥበት ጊዜ ከግንዘቤ ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸው ሁኔታዎች ተለይተው መስፈር ስለሚኖርባቸው በንዑስ ቁጥር /2/ በዝርዝር እንዲመለከቱ ተደርጓል፡፡ በዚህ መሠረት ሞግዚቱ በንብረት አስተዳደርና አጠባበቅ ረገድ ሊከተል የሚገባው መመሪያ ከልጁ ንብረትና ሀብት እንዲሁም ከሞግዚቱ ሀብትና ችሎታ ጋር በተያያዘ የሚነሱ በመሆናቸው ፍ/ቤቱ መመሪያ በሚሰጥበት ወቅት እነዚህን ሁኔታዎች ከግምት ማስገባት እንደሚኖርበት ተመልክቷል፡፡

<u>አንቀጽ 274 አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ በስጦታ ወይም በውርስ ስለሚተላለፍ ንብረት</u>

አካለመጠን ላልደረሰ ልጅ በስጦታ ወይም በኑዛዜ ንብረቶች በሚተላለፉበት ጊዜ ሞግዚቱ ሊከተል ስለሚገባው አሰራር በሰጪው በኩል መመሪያ ሊተላለፍ እንደሚችል የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 287 ይደነግጋል፡፡

አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ከኑዛዜ ውጭ ንብረት በውርስ ሊተላለፍለት የሚችል በመሆኑ የቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 274 ይህንኑ እንዲያካትት ተደርጓል፡፡

<u>አንቀጽ 275 ስለንግድና ሌሎች መሰል ድርጅቶች</u>

የልጁ እናት ወይም አባት ያልሆነ ሞግዚት አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ የንግድ፣ የኢንዱስትሪ ወይም ሌሎች ሥራዎችን በሚያስተዳድርበት ጊዜ የንብረቶችን አስተዳደር ይዞ የሚቀጥል ስለመሆኑ ወይም የማይቀጥል ከሆነ የንብረቱን ሂሣብ አጣርቶ ሊያቀርብ የሚገባ ስለመሆኑ የቤተዘመድ ምክር ጉባኤ ትዕዛዝ መስጠት እንደሚችል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 288 ተመልክቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

ለቤተዘመድ ጉባኤ የተሰጠው ሥልጣን ለፍ/ቤት የተላለፈ በመሆኑ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የልጁ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ወይም አካለመጠን ያደረሱ ወንድምና እህቶች ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ እንዲሰጥ ጥያቄ ማቅረብ የሚችሉ ስለመሆናቸው በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 275/1/ ተመልክቷል፡፡ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ ከግምት ውስጥ ስለሚያስገባቸው ጉዳዩች በሰፈረው ድንጋጌ ላይ ማሻሻያ አልተደረገም፡፡

## አንቀጽ 276 ስለ አንዳንድ ሀብቶች ሽያጭ

ከማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ውጭ ያሉ ለሽያጭ መዋል የሚችሉ ተንቀሳቃሽ የሆኑ ግዙፍ ንብረቶችንና ሰነዶችን ሞግዚቱ መሸጥ እንደሚችል የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 289 ይፈቅዳል፡፡ ድንጋጌው ተንቀሳቃሽ ከሆኑ ንብረቶችና ሰነዶች ውጭ ያሉ ለሽያጭ አገልግሎት የሚውሉ የገንዘብ ሰነዶችን አክሲዮኖችን የማያጠቃልል በመሆኑ የቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 276/1/ እነዚህን ሁኔታዎች ባካተተ መልክ ተደንግጓል፡፡ ሞግዚቱ ሽያጩን ሊያካሄድ ወይም ሊከለከል ስለሚችልበት ሁኔታ በንዑስ ቁጥር 2 የሰፈረውን ድንጋጌ በተመለከተ ለቤተዘመድ ምክር ጉባኤ የተሰጠው ሥልጣን ለፍ/ቤት የተላለፈ በመሆኑ ከዚህ አኳያ ታይቶ ተሻሽሎ ተቀርጿል፡፡

## አንቀጽ 277 ስለአምጪው እንዲከፈል ስለሚያዙ ሰነዶች

አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ የሚተላለፉ ለአምጪው እንዲከፈል የሚያዝዙ ሰነዶችን ሞግዚቱ በሶስት ወራት ውስጥ እንዲሸጡ ወይም በልጁ ስም በሰነድ እንዲለወጡ ማድረግ እንደሚገባው የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 290 ይደነግጋል፡፡ ይኸው ድንጋጌ የቃላትና የአገላለጽ ለውጥ ተደርጎበት በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 277 ተወስዷል፡፡

ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ዕዳዎች መክፈል፣ ገቢ ካፒታል መቀበል፣ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ከብር አምስት መቶ በላይ የሆነን ካፒታል ሥራ ላይ ማዋል አንዳለበትና ይህንኑ ግዴታ ሳይወጣ በመቅረቱ ሊከፈል ስለሚገባው ወለድና ኪሣራ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 291፣292፣293 እና 295 የተመለከቱት ድንጋጌዎች በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 278፣279፣ 280 እንዲሁም 281 የተወሰዱ ሲሆን ካፒታልን በሥራ ላይ ለማዋልም ሆነ የጊዜ ገደቡን ለመወሰን ለቤተዘመድ ምክር ጉባኤ የተሰጠው ሥልጣን ለፍ/ቤት እንዲተላለፍ ከመደረጉ በቀር በድንጋጌዎቹ ላይ የተደረገ ማሻሻያ የለም፡፡

ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ሀብትና ንብረት የማስተዳደርና የመቆጣጠር ሥልጣኑን በሚያከናውንበት ጊዜ አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ የሚገዛቸውን ሀብቶች ለመወሰን ፈቃድ ማግኘት አይጠበቅበትም፡፡ በመሆኑም የሚገዙ ሀብቶችን አስቀድሞ ስለመወሰን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 294 የተመለከተው ድንጋጌ እንዲሰረዝ ተደርጓል፡፡

## አንቀጽ 282 አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ገቢዎች ለአስተዳደሩ ስለሚውልበት ሁኔታ

አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ሞግዚትና አሳዳሪ የተለያዩ ሰዎች በሚሆኑበት ጊዜ ሞግዚቱ ከሚያስተዳድረው ንብረት ገቢ ለልጁ አስተዳደግና ትምህርት የሚውል የተወሰነ ገንዘብ ለአሳዳሪው ሊሰጥ እንደሚገባ ይታመናል፡፡

www.abyssinialaw.com

በዚህ ረገድ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 296 የተመለከተው ድንጋጌ ገቢን ብቻ መሠረት ያደረገ ሲሆን ገቢው በቂ በማይሆንበት ጊዜ የልጁ ንብረት ለአስተዳደሩና ለትምህርቱ ውጪ መሆን ይገባዋል። አከፋፈሉን በተመለከተ በዚሁ ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር /2/ እና /3/ የቤተዘመድ ምክር ጉባኤን ውሳኔ መሠረት በማድረግ የተቀረፀ ሲሆን ለልጁ አስተዳደግና ትምህርት ወጪ የሚሆነው ገንዘብ በየወሩ ተከፋይ መሆን ይኖርበታል። የጊዜ ገደቡ በአሳዳሪውና በሞግዚቱ ስምምነት ወይም በፍ/ቤት ትዕዛዝ ሊለወጥ የሚችልበትን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ይኸው አስተሳሰብ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 282 እንዲሰፍር ተደርጓል።

<u>አንቀጽ 283 ስለኪራይ ውሎች</u>

ሞግዚቱ ያደረጋቸው የኪራይ ውሎች ልጁ አካለመጠን ከደረሰ ከሶስት ዓመት በኃላ ለመፈፀም እንደማይገደድ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 297 ተመልክቷል።

ሆኖም ውሉ አስቀድሞ በቤተዘመድ ምክር ጉባኤ ተፈቅዶ የተደረገ ከሆነ ድንጋጌው አሰገዳጅነት እንደማይኖረው ይገልጻል። ለጉባኤው ተሰጥቶ የነበረው ሥልጣን ለፍ/ቤት እንዲተላለፍ ከመደረጉ በቀር የይዘት ለውጥ ማድረግ ሳያስፈልግ ተወስዷል።

<u>አንቀጽ 284፣ 285 በውርስ ወይም በስጦታ ስለሚገኝ ሀብት</u>

አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ በውርስ ወይም በስጦታ የሚተላለፍ ንብረትና ሀብት ሞግዚቱ መበቀል እንደሚኖርበት የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 298/1/ እና 299/1/ ይደነግጋሉ። በሌላ በኩል ግን በውርስ የተገኘውን ሀብት ሞግዚቱ አልቀበልም ለማለት የሚችለው ዕዳውን የማይሸፍን በመሆኑ ምክንያት የቤተዘመድ ምክር ጉባኤ ፈቃድ ሲኖር እንደሆነ፣ ስጦታንም ቢሆን ላለመቀበል የሚችለው የገንዘቡ መጠን ከብር 500 በታች በመሆኑ ምክንያት ጉባኤው ሲፈቅድ እንደሆነ ተመልክቷል።

ይሁን እንጂ የውርሱን ዕዳ የማይሸፍን ውርስም ሆነ አስፈላጊ ያልሆነን ስጦታ ላለመቀበል ፈቃድ መጠየቅ ሳያስፈልግ በሞግዚቱ ውሳኔ ብቻ ሊከናወን የሚችል በመሆኑ፣ የስጦታውን መጠን በገንዝብ መጠን ከመወሰን ይልቅ አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ በማመዛዘን መወሰን የሚቻል በመሆኑ ድንጋጌዎቹ በዚህ አኳኃን ተሻሽለው በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 284 እና 285 እንዲቀረጹ ተደርጓል።

አነስተኛ ከሆኑ ስጦታዎች በቀር አካለመጠን ባልደረሰ ልጅ ስም ሞግዚቱ ስጦታ ማድረግ እንደማይቻል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 289/2/ የሰፈረው ድንጋጌ የልጁን ንብረት ከማስጠበቅ አኳያ የጐላ ጠቀሜታ የሚኖረው በመሆኑ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 286/2/ ተወስዷል።

<u>አንቀጽ 286 የዋስትና ግዴታ</u>

ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት ለሌላ ሰው ዕዳ በዋስትና ማስያዝ እንደማይቻል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 300 የሰፈረው ድንጋጌ ማሻሻያ ሳያስፈልገው ባለበት እንዲወሰድ ተደርጓል።

<u>አንቀጽ 288 ስለ ግልግል</u>

www.abyssinialaw.com

ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ በመወከል ከብር ሶስት መቶ በላይ የሆኑ ጉዳዩችን በግልግል ለመጨረስ የሚችለው የቤተዘመድ ምክር ጉባኤ ፈቃድ ሲኖር እንደሆነ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 301 ይደነግጋል፡፡ የድንጋጌው ዓላማ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ጥቅም ለመጠበቅ ቢሆንም ሞግዚቱ ከሚያከናውነው ሰፊ ሥልጣንና ተግባር አኳያና ባሁኑ ወቅት ካለው የገንዘብ ዋጋ አንፃር የገንዘቡ መጠን ከብር 300 ወደ ብር 1000 ከፍ እንዲል፣ ከዚህ መጠን በላይ የሚገመትን ጉዳይ በግልግል ለመጨረስ የፍ/ቤትን ፈቃድ ማግኘት እንደሚኖርበት በማመን በድንጋጌው ላይ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡

- በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 302 ሞግዚቱ አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ ጋር ውል ለማድረግ የቤተዘመድ ምክር ጉባኣን ፈቃድ ማግኘት የሚገባው ስለመሆኑ፣
- በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 303 አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ ስም ሞግዚቱ የብድር ውል ለመዋዋል የቤተዘመድ ምክር ጉባኤ የሚያስፈልገው ስለመሆኑ፣
- በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 304 ውሳኔ በሚጠይቁ አስፈላጊ ሥራ ዕድሜው ላይ አስራ አምስት ዓመት
  ከሆነው ልጅ ጋር ሞግዚቱ መመካከር እንደሚኖርበት፣
- በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 503 አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ በዕለት ጉዳይ ሥራዎች ላይ ውሎችን ማድረግ ስለሚፈቅድበት ሁኔታ፣
- በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 306 በዕለት ጉዳይ ሥራዎች ስለሚሸፈኑ ጉዳዩች፣
- በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 307 አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ለሚያደርጋቸው ውሎች ሞግዚቱ ለሶስተኛ ወገኖች ዋስ ስለመሆኑ፣
- በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 308 አካመጠን ያልደረሰ ልጅ ኑዛዜ ስለሚያደርግበት ሁኔታ

የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከሌሎች የቤተሰብ ሕጉ ድንጋጌዎች ጋር እንዲስማሙ ለማድረግ የሚያስችሉ ማስተካከያዎች ከመደረጉ በቀር የጽንስ ሀሳብ ለውጥ ሳያስፈልጋቸው በቤተሰብ ሕጉ ከአንቀጽ /288-294/ ተወስዷል፡፡

በዚህም መሠረት አካለመጠን ካላደረሰው ልጅ ጋር ውል ለመዋዋል፣ በስሙ ለመበደር ሞግዚቱ የፍ/ቤትን ፈቃድ ማግኘት እንደሚኖርበት በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 290 እና 291 ተመልክቷል፡፡ አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ አስራ አራት ዓመት ሲሞላው የሥራ ቅጥር መፈፀም የሚችል በመሆኑ ከፍተኛ በሆኑ ጉዳዩች ላይ ሞግዚቱ ከልጁ ጋር መመካከር እንደሚኖርበት ተመልክቷል፡፡

የፍ/ቤትን ፈቃድ የሚያስፈልግ ማንኛውም ሥራ ወይም ከብር ሶስት መቶ በላይ የሚያስገባ ግዴታ የእለት ጉዳይ ሥራ ሊሆን እንደማይችል በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 292 ሰፍሯል፡፡ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ነዛዜ ማድረግ የሚችልበትን ዕድሜ ከአስራ አምስት ወደ አስራ ስድስት ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡ ምክንያቱም ኑዛዜ ከበድ ያለ ውጤት የሚያስከትል ሕጋዊ ድርጊት በመሆኑ ይህ የሚከናወንበት ዕድሜ ከፍ ማድረግ አስፈልጓል፡፡

የጋብቻ ዕድሜ ከመድረሱ ከሁለት ዓመት በፊት ባሉት ጊዜያት አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ጋብቻ ስለሚፈጽምበት ሁኔታ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 7/2/ የተደነገገ በመሆኑ በፍ/ብ ሕግ ቁጥር 309 የሰፈረው ድንጋጌ እንዲካተት አልተደረገም፡፡

<u>አንቀጽ 295 ንብረት ለማስተዳደር ሞግዚቱ ስለሚያደርገው ወጪ</u>

www.abyssinialaw.com

ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት በሚያስተዳድርት ጊዜ በግሉ ያወጣው ሊተካለት እንደሚገባ በፍ/ብ/ ሕግ ቁጥር 310 የሰፈረው ድንጋጌ ማሻሻያ ሳያስፈልገው ተወስዷል።

<u>አንቀጽ 296 ሞግዝቱ ለሚያስተዳድረው ንብረት ሪፖርት ማቅረብ የሚኖርበት ስለመሆኑ</u>

ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት በሚያስተዳድርበት ጊዜ ስለ ንብረቱ አስተዳደር የሂሣብ ሪፖርት ማቅረብ እንደሚኖርበት የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 311/1/ ይደነግጋል። ሪፖርቱ የሚቀርበው ለቤተዘመድ ምክር ጉባኤ እንደሆነም ተመልክቷል።

ይሁን እንጂ በጉባኤው ምትክ የሚመለከታቸው የልጁ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች፣ እህትና ወንድሞቹ በመሆናቸው ጥያቄ ሲቀርብ ለእነዚሁ ወገኖች መቅረብ እንደሚገባውና ጥያቄ ባይቀርብም ሪፖርቱ ተዘጋጅቶ መቀመጥ ስለመኖርበት የቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 296 በዚህ አኳኃን ተሻሽሏል።

<u>አንቀጽ 297 ስለማጣቀስ</u>

የልጁ እናትና አባት ሞግዚት በሚሆኑበት ጊዜ በመካከላቸው ያለመግባባት ሲኖር ወይም ተለያይተው በመኖራቸው ምክንያት ሊቀርብ ስለሚችል አቤቱታ አሳዳሪነትን በተመለከተ በቤተሰብ ሕጉ ከአንቀጽ /265-267/ የሰፈሩት ድንጋጌዎች በሞግዚቱ ላይ ተፈፃሚ ስለመሆናቸው በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 312 በተደነገገው አኳኃን ሰፍሯል።

## <u>ክፍል 4</u>

## <u>አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ለመጠበቅ የተመለከቱትን ደንቦች መጣስ ስለሚያስከትለው ውጤት</u>

### <u>ንዑስ ክፍል 1 አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ሥራዎች</u>

አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ለመጠበቅ የወጡትን ድንጋጌዎች በመጣስ የሚፈፀም ድርጊት ስለሚያስከትለው ቅጣት በሚል የሰፈረው አገላለጽ የሚያመለክተው የወንጀል አድራጉትን በመሆኑ ’’ውጤት’’ በሚል ቃል ተተክቷል።

አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ ጋር የሚደረጉ ውሎች የሚያስከትሉትን ውጤት፣ አካላመጠን ያልደረሰው ልጅ ከውል ውጭ ለሚያደርጋቸው ኃላፊነትና አለአግባብ ለመበልፀግ ስለሚፈፀሙ ድርጊቶች ከፍ/ብ/ሕግ ቁጥር /313-318/ በተመለከቱት ድንጋጌዎች ላይ በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ የተደረገ ማሻሻያ ባይኖርም በተወሰኑት ላይ መጠ

www.abyssinialaw.com

ነኛ የቃላትና የአገላለጽ ለውጥ ተደርጐባቸው በቤተሰብ ሕጉ ከአንቀጽ /298-303/ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

በዚህ ክፍል በንዑስ ክፍል /1/ የተካተቱት ጉዳዩች አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ስለሚፈጽማቸው በሕግ የተፈቀዱ ከሥልጣኑ በላይ የሆኑትን ሥራዎች/ድርጊቶች/ በመሆኑ ድንጋጌዎቹ በዚህ አኳኃን ማስተካከያ ተደርጐባቸዋል፡፡

የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 314/2/ አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ከሥልጣኑ በላይ የፈፀማቸው ውሎች በስህተት በተሰጠ ፈቃድ እንደተደረገ ተቆጥሮ ፈራሽ እንደሚሆን ይደነግጋል፡፡ ፈቃድ የተሰጠው በስህተትም ሆነ በሌላ ምክንያት አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ የፈፀመው ውል በሕግ ከተፈቀደለት ስልጣን በላይ ከሆነ ፈራሽ እንደሚሆን በዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር /2/ በግልጽ የተመለከተ በመሆኑ ስህተትን በሚመለከት የሰፈረው አገላለጽ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 399 እንዲካተት አልተደረገም፡፡ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 315 አካለመጠን ካልደረሰ ልጅ ጋር በቅን ልቦና የማፈፀሙ ውሎች ፈራሽ እንደማይሆኑ የሰፈረው ድንጋጌ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 300 በሁለት ንዑሳን አንቀጾች እንዲከፈል ከመደረጉ በቀር ድንጋጌው በቀጥታ ተወስዷል፡፡

አካለመጠን የደረሰው ልጅ ከሥልጣኑ ውጭ የተዋዋለው ውል ፈራሽ በሚሆንበት ጊዜ የተቀበለው ገንዘብ ካለ በቅን ልቦና ለተዋዋለው ወገን የሚመልሰው ውሉ እንዲፈርስ ክስ በቀረበበት ጊዜ በእጁ የቀረው /ያለው/ መጠን ብቻ እንደሆነ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 316/1/ ስለመክፈል በሚል ርዕስ ሥር ተደንግጓል፡፡ የዚህ ድንጋጌ ዓይነተኛ ዓላማ አካለመጠን ካልደረሱ ልጆች ጋር ከሥልጣን ውጭ የሚደረጉ ውሎች የገንዘብ ቅጣት የሚያስከትሉ መሆናቸውን ለማመልከት ነው፡፡

ይሁን እንጂ የድንጋጌው አገላለጽ ግልጽነት የጐደለው በመሆኑ ርዕሱ 'ስለሚመለስ ገንዘብ' በሚል ተስተካክሎ እንዲቀረጽ የተደረገ ሲሆን በውሉ መፍረስ ምክንያት ሊመለስ የሚገባው ለልጁ ጥቅም ያልዋለ ቢሆንም ክስ በቀረበበት ጊዜ በልጁ እጅ /ብልጽግና/ የሚገኝ ከሆነ ሊመለስ እንደሚችል በሚገልጽ ሁኔታ ማስተካከያ ተደርጐ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 301/1/ ሰፍሯል፡፡

አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ከውል ውጭ በሚደርስ ኃላፊነትና ያለአግባብ ስለመበልፀግ በሚመለከቱ ሕጐች ተጠያቂ ሊሆን እንደሚችል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 317 የሰፈረው ድንጋጌ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 302 ተካትቷል፡፡

## <u>ንዑስ ክፍል 2 የሞግዚቱ ሕጋዊያን ድርጊቶች</u>

በዚህ ንዑስ ክፍል የተመለከቱት ድንጋጌዎች ሞግዚቱ በሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ በመወከል ለሚያከናውናቸው ሥራዎች የሚኖርበትን ኃላፊነት የሚወስኑ ናቸው፡፡ በመሆኑም በፍ/ብ/ሕጉ እንግሊዘኛ ቅጂ የሰፈረው አገላለጽ የሞግዚቱን ሕጋዊያን ድርጊቶች የሚመለከት በመሆኑ ይኸው ቃል እንዲወስድ ተደርጓል፡፡

### <u>አንቀጽ 304 በደንብ የተፈፀሙ ሥራዎች</u>

www.abyssinialaw.com

ሞግዚቱ በሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ በመወከል ለሚሰራቸው ሥራዎች በልጁ ስም በወኪልነት ደረጃ ተጠያቂ እንደሚሆን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 319/2//3/ የሰፈረው ድንጋጌ የሞግዚቱንም ሆነ የልጁን የተጠያቂነት ወሰን የሚያመለክቱ በመሆናቸው በቀጥታ የተወሰዱ ሲሆን በንዑስ ቁጥር /1/ የሰፈረው ሁኔታ በንዑስ ቁጥር /2/ የሚሸፈን በመሆኑ ተሰርዟል፡፡

<u>አንቀጽ 305 ሕጋዊያን ድርጊቶችን ስለመተላለፍ</u>

ሞግዚቱ በሕግ ከተሰጠው ሥልጣን ውጭ ለሚያከናውናቸው ሥራዎች ወኪል የሆነ ሰው ከሥልጣኑ ውጭ በሰራው ስራ ሊጠየቅ የሚችልበት አግባብ ባለው የውክልና ሕግ መሠረት ተጠያቂ እንደሚሆን የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 320/1/ ይደነግጋል፡፡ ድንጋጌው የአገላለጽ ለውጥ ተደርጐበት በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 305 ተወስዷል፡፡

በሌላ በኩል ሶስተኛ ወገኖች የሞግዚቱን ክፉ ልቡና ማስረዳት እንደሚኖርባቸው በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 312 በንዑስ ቁጥር /3/ የሰፈረው ድንጋጌ በማንኛውም ጉዳይ ተፈፃሚነት የሚኖረው አጠቃላይ መርህ በመሆኑ ተሰርዟል፡፡ ስለ ሞግዚቱ ኃላፊነት በቤተሰብ ሕጉ የሰፈሩት ድንጋጌዎች በምትክ ሞግዚት ላይም አግባብነት የሚኖራቸው በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 322 የሰፈረው ድንጋጌ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 307 ተወስዷል ተጨማሪ ሞግዚት በቤተሰብ ሕጉ ያልተካተተ ስለሆነ ይህንኑ በሚመለከት የሰፈረው ቃል ተሰርዟል፡፡

<u>ንዑስ ክፍል 3</u>
<u>በኃላፊነት ሊያስጠይቁ ስለሚችሉ ድርጊቶች</u>

ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት በሚያስተዳድርበት ጊዜ ላደረሰው ጉዳት በኃላፊነት ስለሚጠየቅበት ሁኔታ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 323/1/ የሰፈረው ድንጋጌ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 308 የተወሰደ ሲሆን ለሞግዚቱ መመሪያ የሚሰጡ አካላት ፍ/ቤትና በኑዛዜ ወይም በስጦታ ንብረት የሚሰጡ ሰዎች በመሆናቸው የቤተዘመድ ምክር ጉባኤ የሚሰጠውን ትዕዛዝ ባለማክበሩ የሚለው አገላለጽ መመሪያ በሚል ተወስዷል፡፡

ሞግዚቱ ተንኮል ካልተገኘበት በኃላፊነት እንደማይጠየቅ በንዑስ ቁጥር /2/ የተመከተው ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር /1/ ሥር ተጠቃልሎ የሚታይ በመሆኑ ተሰርዟል፡፡ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 308 ንዑስ ቁጥር /2/ ስለምትክ ሞግዚት የሰፈረው ሁኔታ ከፍ/ብ/ሕጉ አንቀጽ 323/3/ የተወሰደ ነው፡፡

ተጠባባቂ ሞግዚት በቤተሰብ ሕጉ ያልተካተተ በመሆኑ ይህንኑ በተመለከተ በፍ/ብ/ሕግ አንቀጽ 323/3/ እና 324 የሰፈሩት ሁኔታዎች ተሰርዘዋል፡፡

የባልና የሚስት ንብረት ግንኙነትና ዕዳ አከፋፈልን የሚመለከቱ ጉዳዩች በቤተሰብ ሕጉ ምዕራፍ 3 በክፍል /3/ ሥር ባሉት ድንጋጌዎች በዝርዝር የተቀመጡ በመሆኑ በሞግዚትነት ጊዜ ሚስት ባለዕዳ ብትሆን ባል በአንድነት ተጠያቂ እንደሚሆን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 326 የሰፈረው ድንጋጌ፣ እንዲሁም ስለቤተዘመድ ምክር ጉባኤ

www.abyssinialaw.com

በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 327 የተመለከተው ድንጋጌ አስፈላጊ ባለመሆኑ እንዲሰረዝ ተደርጓል።

## ክፍል 5

## አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ችሎታ ማጣት ስለመቅረቱ

አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ችሎታ ማጣቱ ስለሚቀርበት ሁኔታ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 328 የተመለከተው ድንጋጌ የጽንሰ ሀሳብ ማሻሻያ የሚያስፈልገው ባለመሆኑ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 309 እንዲካተት ተደርጓል።

### አንቀጽ 310 በጋብቻ ምክንያት ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ስለመውጣት

የቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 7/2/ በተለየ ሁኔታ በሚፈቅደው መሠረት ከአስራ ስድስት እስከ አስራ ስምንት ዓመት ባለው የዕድሜ ክልል ጋብቻ የሚፈፀም በመሆኑ በዚህ ጊዜ ውስጥ ጋብቻ የሚፈፀም ቢሆን ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ መውጣት የሚቻልበት ሁኔት ይኖራል።

ይህንኑ በሚመለከት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 329 ጋብቻ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ እንደሚያወጣ የሰፈረው ድንጋጌ ከላይ በተገለፀው አኳኋን ተሻሽሎ ተወስዷል።

### አንቀጽ 311 በልዩ ሁኔታ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ስለመውጣት

አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ በአስራ አራት ዓመት ዕድሜው ሥራ መቀጠር የሚችል በመሆኑ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ሆኖ ራሱን ሊያስተዳድርና ሊወክል ይችላል። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ነፃ ለመውጣት የቤተዘመድ ምክር ጉባኤ ውሳኔ አስፈላጊ እንደሆነ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 330/2/ ይደነግጋል። ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ የሚወጣበት ዕድሜ አስራ አምስት እንደሆነ በዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር /1/ ተመልክቷል።

የጉባኤው ስልጣን በፍ/ቤት የተተካ ሲሆን ጥያቄው በፍ/ቤቱ በኩል ተቀባይነት የሚያገኘው የልጁን ጥቅም የሚያስጠብቅ በሚሆንበት ጊዜ እንደሆነ በማመልከት ድንጋጌው ተሻሽሎ ተጽፏል።

አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ዕድሜው አስራ አራት ዓመት የሞላው በመሆኑ ምክንያት ከሞግዚቱ አስተዳደር ነፃ ለመውጣት እንዲችል የሚቀርበው ጥያቄ በፍ/ቤት በኩል ተቀባይነት የሚያገኘው የልጁን ጥቅም የሚያስጠብቁ ሁኔታዎች መኖራቸው ሲረጋገጥ መሆኑን በግልጽ የተመለከተ በመሆኑ የልጁን እናትና አባት ፈቃድ በተመለከተ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 331፣ 332 የሰፈረውን ሁኔታ በተጠናጠል መደንገግ አስፈላጊ ባለመሆኑ እንዲካተቱ አልተደረገም።

### አንቀጽ 313 ውጤቶች

በዚህ ክፍል ከሞግዚት አስተዳደር ሥልጣን ነፃ የወጣ ልጅ አካለመጠን እንዳደረሰ ሰው ስለሚቆጠር ለሞግዚቱ ተሰጥተው የነበሩትን ሥልጣንና ተግባራት ማከናወንም ሆነ

www.abyssinialaw.com

ራሱን ማስተዳደር እንደሚችል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 333 ተመልክቷል፡፡ ድንጋጌው መጠነኛ የቃላት ማሻሻያ ታክሎበት እንዲካተት ተደርጓል፡፡

<u>አንቀጽ 314   የማይሻር ስለመሆኑ</u>

ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ እንዲወጣ የተሰጠ ውሳኔ/ፈቃድ/ ሊሻር የማይችል ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 334/1//2/ ተመልክቷል፡፡ ድንጋጌው ማሻሻያ የሚያስፈልገው ባለመሆኑ በቀጥታ እንዲወሰድ የተደረገ ሲሆን የጋበቻ ዕድሜ ባለመጠበቁ ምክንያት ጋብቻው የሚፈርስ ከሆነ ጉዳዩ በፍ/ቤት በኩል ታይቶ የሚወሰን መሆኑን በሚያመለክት አገላለጽ ተሻሽሏል፡፡

<u>ንዑስ ክፍል 2</u>
<u>የሞግዚትነት ሥራ ሒሳቦችን ስለማስታወቅ</u>

አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ እንዲሆን በመፍቀዱ ወይም ዕድሜው አካለመጠን በመድረሱ ምክንያት የሞግዚትነትን ስልጣኑ ሲያበቃ ሞግዚቱ ሊጠይቅ ስለሚገባው ክፍያ፣ ንብረት ስለሚመልስበት ሁኔታ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 335 እና 336 የሰፈሩት ድንጋጌዎች መጠነኛ የአገላለጽ ለውጥ ተደርጐባቸው በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 315-316 እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

ዕድሜው 18 ዓመት ያልሞላ ልጅ የሞግዚቱን የሥራ ሂሣቦች ሊያፈርስ የሚችል ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 337 የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው ልጁ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ሲወጣ በመሆኑ በዚህ ረገድ ማሻሻያ ተደርጐ ድንጋጌው በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 317 ተወስዷል፡፡

አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ በመወከል ሞግዚቱን በኃላፊነት ለመጠየቅ የሚቻለው ሥልጣኑ በተቋረጠ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ እንደሆነ የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 338 ይደነግጋል፡፡ ይህ ድንጋጌ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 318 እንዲካተት የተደረገ ሲሆን በሥራው አጋጣሚ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት ወስዶ ወይም ያለአግባብ ተጠቅሞ ይህንኑ ንብረት ለማስመለስ የሚቀርብን ክስ የጊዜ ገደቡ እንደማይመለከተው በንዑስ ቁጥር /2/ ተመልክቷል፡፡

አለአግባብ የተወሰደ ንብረት ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማግኘት በማቀድ የሚፈፀም ሲሆን በሞግዚቱ የተወሰደን ንብረት ለማስመለስ የሚቀርብ ክስ አለአግባብ ለመበልፀግና በሌላ በተለያየ መንገድና ዘዴ የሚፈፀሙ አድራጐቶችን የሚያጠቃልል በመሆኑ የአምስት ዓመት ይርጋ ጊዜ የማይመለከተው በሞግዚቱ የተወሰደን ንብረት ለማስመለስ የሚቀርብ ጥያቄን እንደሆነ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 317/2/ ተመልክቷል፡፡

<u>ምዕራፍ 13</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ 319   የተሻሩ ሕጐች

የቤተሰብ ሕግ ከፍትሐብሔር ሕጉ ተነጥሎ ራሱን የቻለ ሕግ /code/ እንዲሆን በመደረጉ ምክንያት በ1952 ዓ.ም. በወጣው የፍ/ብ/ሕግ፣

አንደኛው መጽሐፍ አካለመጠን ስላልደረሱ ሰዎች  ከቁጥር /198 -  338/፣
ሁለተኛ መጽሐፍ ስለሥጋና ጋብቻ ዝምድና ከቁጥር /550 - 826/፣
ያሉትን ድንጋጌዎች እንዲያጠቃልል ተደርጓል፡፡

በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ የተካተቱት የፍ/ብ/ሕጉ ክፍሎች በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት ከተረጋገጡ መብትና ነፃነቶች ጋር ለማጣጣምና ሕብረተሰባችን የደረሰበትን የአስተሳሰብና የዕድገት ደረጃ ለማገናዘብ በሚያስችል ደረጃ ተገቢው ማሻሻያና ማስተካከያ ተደርጐባቸዋል፡፡

የቤተሰብ ሕጉ በሥራ ላይ እንዲውል ሲደረግ ከላይ የተገለፁት የፍ/ብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነታቸው ቀሪ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ከወጣው የቤተሰብ ሕግ ጋር የማይጣጣሙና የሚቃረኑ ሌሎች ሕጐች፣ መመሪያዎችና ልምዶች እንዲሁ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

አንቀጽ 320   በተሻሩ ሕጐች መሠረት ተገኝተው ስለነበሩ መብቶች

የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ከመውጣቱ በፊት በፍ/ብሔር ሕጉ መሠረት ተፈፃሚ የነበሩትን ሕጋዊ ሁኔታዎችና ውጤቶቻቸው ሕጉ በመውጣቱ ምክንያት ተፈፃሚነታቸው አይቀርም፡፡ ተሻሽሎ የወጣው የቤተሰብ ሕግ ወደኃላ ተመልሶ ተፈፃሚ ሊሆን እንደማይችል በመደንገጉ በመሸጋገሪያ ጊዜ ሊፈጥር የሚችለውን ክርክርና ውዝግብ ለመስወገድ ያስችላል፡፡

አንቀጽ 321   ስለምዝገባ

በ1952 ዓ.ም. የወጣው የፍ/ብሔር ሕግ የክብር መዝግብ ስለሚቋቋምበትና ስለሚደራጅበት ሁኔታ በአንደኛ መጽሐፍ /ከቁጥር 47-153/  ስለሰዎች በሚደነግገው ክፍል በዝርዝር የተመለከተ ቢሆንም በሥራ ላይ የሚውልበት ቀን በነጋሪት ጋዜጣ ተወስኖ እስከሚታወጅ ድረስ ተፈፃሚ እንደማይሆን በፍ/ብ/ሕጉ በቁጥር 3361 በመገደቡ ምክንያት ልደት ጋብቻና ሞትን የሚመዘግብ የክብር መዝገብ ሹም ጽ/ቤት እስካሁን ሳይቋቋም ቆይቷል፡፡

የክብር መዝገብ ጽ/ቤት መቋቋም በተለይም በቤተሰብ ሕጉ ጋብቻን ልደትንና ፍቺን በሚመለከት ሊፈጠሩ የሚችሉ አከራካሪ ጉዳዩችን እልባት የሚሰጥ ሲሆን ተሻሽሎ የሚወጣውን የቤተሰብ ሕግ በተሟላ ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

ይህንኑ እውነታ መነሻ በማድረግ የቤተሰብ ሕጉ ድንጋጌዎች የክብር መዝገብ ሹም ጽ/ቤትን መቋቋም መሠረት አድርገው የተዘጋጁ በመሆናቸው ሕጉን ተፈፃሚ ለማድረግ የፌዴራል መንግሥት አካላት የምዝገባ ሕግ የማውጣትና የተቋሙን ማደራጀት ይጠበቅባቸዋል፡፡

www.abyssinialaw.com

የቤተሰብ ሕጉ ወጥቶ በሥራ ላይ እስኪውል ድረስ የተሰጡት ምስክር ወረቀቶች ሕጋዊ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡

አንቀጽ 322 ስለቤተሰብ ጉዳይ ክርክሮች

የቤተሰብ ሕጉ ኃላቀርና አድሎአዊ አስተሳሰቦችንና አሰራሮችን የሚያስወግድ የዜጐችን መሠረታዊ መብትና ነፃነቶች በተሟላ ደረጃ ለማረጋገጥ በሚያስችል መልክ በእኩልነት መርህ ላይ ተመስርቶ የተዘጋጀ በመሆኑ በክርክር ላይ ያሉ የቤተሰብ ጉዳይ ክርክሮች ከፍ/ብ/ሕጉ ይልቅ በተሻሻለው ሕግ መሠረት ውሳኔ እንዲያገኙ ቢደረግ ከፍትሕ አኳያ ጠቀሜታው የጉላ እንደሚሆን ይታመናል፡፡ በመሆኑም ውሳኔ ያላገኙ የቤተሰብ ጉዳይ ክርክሮች በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ መሠረት ታይተው ውሳኔ ያገኛሉ፡፡

አንቀጽ 323 ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የተዘጋጀውን የቤተሰብ ሕግ ተግባራዊ ለማድረግና በተሟላ ደረጃ ለማስፈፀም እንዲቻል የፌዴራል ሕጉ ተፈፃሚ የሚሆንባቸው መስተዳድሮች ዝርዝር የአፈፃፀም ደንቦችን ማውጣት የሚያስችል ሥልጣን እንዲኖራቸው ተደርጓል፡፡